


ጠ/ሚኒስትር ዐብይ
የብሉይ ኪዳንን
ሕግ ይጠቀሙበት

ሌንጮ ባቲ
በጌታቸው ረዳ መንገድ?

የህሊና እስረኛ



ጋዜጠኛ ፍቃዱ ማህተመወርቅ


መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ማዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ማዮን ቁጥር 81 የካቲት 2012 ዓ.ም ዋጋ 20.00


## “ነጻ አውጪ የሆነች ቤተክርስቲያን ነጻነት ልታጣ አይገባም”

‹‹በአንድነት የማያምኑ ሰዎች ስለአንድነት እየተናገሩ ነው››

‹‹በሰይፍና በገጀራ እያስፈራሩ ማተብህን በጥስ መባል ተጀምሯል››

መምህር ምህረትአብ አሰፋ

ልዩ ቃለምልልስ



‹‹የአውሮፕላን ነዳጅ ማከማቻ ገበያን ስንቀላቀል የተለያዩ የአሰራር ችግሮች ገጥመውናል››

አቶ ሒራን ፈለቀ

‹‹ጊዜውን ጠብቆ የኢትዮጵያዊ አንድነት ስሜት መጎልበቱ አይቀርም››



አቶ ሙሉጌታ አረጋዊ

# አልፎዝ ኃ/የተወሰነ የግል ማህበር የገበያ ማዕከል አስገነባ



የካቲት 14 ቀን 2012 ዓ.ም የኢፌዲሪ ፕሬዚዳንት አምባሳደር ሳህለወርቅ ዘውዴ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ ታከለ ኡማ፣ የተለያዩ ሚኒስትሮች፣ አምባሳደሮች፣ ባለሀብቶችና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በሚገኙበት ከኢንፔሪያል ትራፊክ መብራት ወደ ገርጂ በሚወስደው መንገድ ላይ በ3000 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈውና የምረቃ ሥነ ሥርዓቱ የሚከናወነው፤ የአልፎዝ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር ግዙፍ የገበያ ማዕከል ወደ ሥራ እንደሚገባ ተሰማ፡፡

ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ ለ22 ዓመታት በተለያዩ የንግድ ሥራዎች ላይ የተሰማራው አልፎዝ ኃ/የተ/የግ/ማ ከዚህ ቀደም የቡና እርሻን በቦንጋና በጅማ፤ እንዲሁም የእንስሳት ሀብት ልማትና የሥጋ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ በአዳሚ ቱሉ ሲንቀሳቀስ የቆየ ተቋም ነው፡፡

# ደቡብ ግሎባል ባንክ ደንበኞቹን ሸለመ

የደቡብ ግሎባል ባንክ አክሲዮን ማኅበር በወጪ ንግድ ደንበኞች ቀንን ምክንያት በማድረግ የዳይሬክተሮች ቦርድ "በወጪ ንግድ ደንበኞችን የውጭ ምንዛሪን ከማግኘት አኳያ በንግዱ ዘርፍ ላይ ተሰማርተው በትጋት ለሠሩ እውቅናና ሽልማት መስጠቱን በስካይላይት ሆቴል ባዘጋጀው መርሃ ግብር ላይ ገልጿል፡፡ ሽልማት ካገኙት ውስጥ ሙለር ኃ/የተ/የግ/ማ ፣ ሆራ ትሬዲንግ፣ ሌይ ቤንሳ የቡና ላኪዎች፣ አልታ ኮምፒውቴክ፣ አባሃዋ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ለአብነት የሚጠቀሱ ሲሆን በጥቅሉ 36 ድርጅቶች ተሸላሚ ሆነዋል፡፡

# "ጆርኒ ቱ ዴዝ" የተሰኘው የጋዜጠኛ ዳንኤል ገዛኸኝ መጽሐፍ ገበያ ላይ ዋለ

በኢትዮጵያ የነፃ ፕሬስ ታሪክ ወስጥ በርካታ ውጣ ውረዶችን ያሳለፈው የቃልኪዳን መጽሔት እና የሞገድ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የነበረው፤ በበርካታ የነፃ ፕሬስ ውጤቶች ላይ ሰፊ ተሳትፎ በማድረግ የሚታወቀው ጋዜጠኛ ዳንኤል ገዛኸኝ የተጻፈው መጽሐፍ በአማዞን ላይ ለሽያጭ መቅረቡ ታወቀ፡፡

ከ1997 ምርጫን ተከትሎ ወደ የመን በባህር ላይ አደገኛ ጉዞ በማድረግ የተሰደደውና አሁን በስደት አሜሪካን የሚገኘው ዳንኤል ገዛኸኝ ፤ ለ72 ሰዓታት በሰሀራ በረሃና 41 ሰዓት በቀይ ባህር ላይ በሕገወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች አማካይነት ያያውን ስቃይና እንግልት የተረከበት፣ ሲፋን የተባለ በአማርኛ ቋንቋ የታተመ መጽሐፉ ነው፤ ወደ እንግሊዘኛ ቋንቋ ተተርጉሞ፤ "ጆርኒ ቱ ዴዝ" የተሰኘ ርዕሥ ተሰጥት ለኅትመት የበቃው፡፡

ደራሲው ለግዮን መጽሔት እንዳስታወቀው መጽሐፉን በ11 ዶላር ከዘጠና ዘጠኝ ሳንቲም በመግዛት እርሱ ለሚያደርገው የኩላሊት ንቅለ ተከላ kid-ney transplant ኢትዮጵያውያን እገዛ እንዲያደርጉለት ተማፅኗል፡፡

## የኩዊንስ ኮሌጅ ለ3ኛ ጊዜ ችግር ፈቺ ጥናታዊ ጽሑፎችን በባለሙያ እንዲቀርቡ አደረገ

"በትምህርትና ጥራት ላይ የማኅበረሰቡን ችግሮች ይፈታሉ" በማለት በየዓመቱ ዳጎስ ያለ ጥናት የሚያቀርቡት የኩዊንስ ኮሌጅ የተለያዩ መምህራንን፤ የዩኒቨርሲቲ ምሁራንን የመንግሥትና የግል በርካታ ተቋማትና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት ባካተተ መልኩ ከፍተኛ የመንግሥት የትምህርት ሚ/ር ባለሥልጣን በተገኙበት የተለያዩ ጥናታዊ ጽሑፎች ተስተናግደዋል፡፡ በዕለቱ የኩዊንስ ኮሌጅ ዋና ዳይሬክተር የሆኑት አቶ ሞገስ በተለይ በትምህርት ጥራት ላይ እየተስተዋለ የመጣውን ችግር ለመቅረፍ ኮሌጃቸው ጠንካራ የሆነ አቋምን አንግቦ እየሠራ መሆኑን በአፅንኦት ገልፀዋል፡፡

## ቴዲ አፍሮ ዛሬ በመስቀል አደባባይ ከአድናቂዎቹ ጋራ ፍቅር ያዜማል




እውቁ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) ዛሬ የካቲት 14 ቀን 2012 ዓ.ም ታላቅ የሙዚቃ ድግስ ለማቅረብ ዝግጅቱን እንዳጠናቀቀ ተገለጸ፡፡

ብዙዎች በተለያዩ የማኅበራዊ ድረገፆች "ንጉሱ የሚራቀቅበት መድረክ በጥንቃቄ ተዘጋጅቷል በከተማይቱ የሚገኙ የንጉሡ አድናቂዎች በአል እስኪመስል ድረስ ዝግጅቱን አድምቀውት ውለው ያመሻሉ፣ ታላቁ ጥበበኛም ተከታዮቹን በደስታ ጮቤ ያስረግጣል፤ ኢትዮጵያም በልጆችዋ ደስታ ደስ ይላታል›› ሲሉ ሰፊ ቅስቀሳ ያካሄዱበትና ከትላንት ጀምሮ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የመጡ የድምፃዊው አድናቂዎች በዚህ ደማቅ የሙዚቃ ኮንሰርት ላይ ለመታደም ትኬቶቻቸውን በመቁረጥ በጉጉት እየተጠባቁ እንደሆነ የዝግጅቱ አስተባባሪዎች አስተያየታቸውን ለግዮን ሰጥተዋል፡፡

ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) "ኢትዮጵያ" የተሰኘውን አልበሙን ለገበያ ማቅረቡን ተከትሎ ለበርካታ ወራት በአሜሪካና በአውሮፓ ሥራዎቹን ሲያቀርብ የቆየ ሲሆን መስከረም 5 ቀን 2011 በሚሊኒየም አዳራሽ ከዓመታት በኋላ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አድናቂዎቹን በተገኙበት የሙዚቃ ድግስ ማቅረቡ ይታወሳል፡፡

# ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ማይክ ፓምፔዩ በኢትዮጵያ ያደረጉትን ጉብኝት አጠናቀቁ



ለሁለት ቀናት በኢትዮጵያ ያደረጉትን የሥራ ጉብኝት ያጠናቀቁት የአሜሪካው ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ማይክ ፓምፔይ ኢትዮጵያ እያካሄደች የሚገኘውን ለውጥ ለመደገፍ አሜሪካ ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ እንደምታፈስ አስታውቀዋል።
የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ማይክ ፓምፔይ ከኢፌዲሪ ፕሬዝዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ እና ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ገዱ አንዳርጋቸውና ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ጋራ ተገናኝተው በአፍሪካ ቀንድ ሰላምና ደህንነት ዙሪያ መወያየታቸው ታውቋል።
የአፍሪካ አገራት የሥራ ዕድል ፈጠራ እና በአህጉራዊ ምጣኔ ሀብት ላይ ትኩረት ያደረገ መድረክ ላይ በመገኘትም መልዕክት ያስተላለፉት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ማይክ ፓምፔይ የኢኮኖሚ ነፃነት ያለውን ፋይዳ በተመለከተ ገለፃ ያደረጉ ሲሆን፤ የግል ዘርፉን ማጠናከር የሥራ ዕድል ፈጠራን በማሳደግ ብልፅግናን ማረጋገጥ ወሳኝ መሆኑን አስታውቀዋል።
ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ እያካሄዱት ያሉትን ማሻሻያዎች ያደነቁት ፓምፔይ የፕሬዝዳንት ትራምፕ አስተዳደር የአሜሪካና የአፍሪካ የንግድ ትስስርን ለማጠናከር ፍላጎት እንዳለው ለአፍሪካ ኢኮኖሚ ኮሚሽን አድራሻ በተካሄደ የምክክር ጉባዔ ላይ አስታውቀዋል።
ዋሽንግተን ለአፍሪካ አገራት በሰጠችው ነፃ የገበያ ዕድል በርካታ አገራት ተጠቃሚ መሆናቸውን መሥሪያ ቤታቸው ያሳወቀው ማይክ ፓምፔይ፣ በዚህም ኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት ወደ አሜሪካ ገበያ የምትላካቸው ምርቶች እየጨመረ የመጣ መሆኑን፣ በዚሁም የሁለቱ አገራት የጋራ ተጠቃሚነት መረጋገጡን አስታውቋል።
በፈረንጆቹ 2018 በአገራቱ መካከል የ1 ነጥብ 8 ቢሊዮን ዶላር የንግድ ልውውጥ የተካሄደ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ኢትዮጵያ 1 ነጥብ 3 ቢሊየን ዶላር ያላቸውን ሸቀጦች ወደ አሜሪካ ልካለች።
በተጨማሪም አሜሪካ 445 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ያላቸው ምርቶችን ወደ ኢትዮጵያ ልካለች ያለው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ መሥሪያ ቤት ከዚህ በተረፈ የኢትዮጵያ መንግሥት እያደረገው ላለው ማሻሻያ የተለያዩ ድጋፎች እያደረገ ይገኛል። ከዚህ ውስጥ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ለማሳደግ፣ የንግድ ድባቡን ለማሻሻል ለባለሀብቶች ምቹ ሁኔታ መደላደል ለመፈጠር፣ የሥራ ዕድል ፈጠራና በኢትዮጵያ የሚደረገውን ኢንቨስትመንት ለማረበታታት 1.117 ሚሊዮን ዶላር በላይ ድጋፍ አሜሪካ ማድረጓን አስታውቋል።
የአሜሪካ ማግስት ምርጫ ቦርድን ተዓማኒነት ለማሳደግና የሲቪል ማኅበረሰቡን አባላትና የሕብረተሰቡን ተሳትፎ ለማሳደግ እንዲረዳ ለኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ ከ37 ሚሊዮን ዶላር በላይ ድጋፍ ማድረጓን ማይክ ፓምፔይ ከኢትዮጵያ መንግሥት ባለስልጣናት ጋራ ባደረጉት ንግግር ላይ ተገልጿል።

# ቅዱስ ሲኖዶስ ራሱን የኦሮሚያ ቤተክህነት አደራጅ ኮሚቴ ብሎ በሚጠራው ስብስብ ላይ ውሳኔ አሳለፈ



ከየካቲት 9 እስከ 11 ቀን 2012 ዓ.ም ሲካሄድ የቆየው የቅዱስ ሲኖዶስ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የነ ቀሲስ በላይን የኦሮሚያ ቤተክህነት ምስረታ እንቅስቃሴ ዙሪያ በጥልቀት ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል:: በዚህም ህገወጡ ቡድን ከሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች እንዲታቀብ እና እስከሚቀጥለው የግንቦቱ ምላዓተ ጉባኤ ድረስ አቋሙን አስተካክሎ ቤተክርስትያንን ይቅርታ እንዲጠይቅ እስከዚያውም የቡድኑ አባላት ስልጣናቸው እንዲያዝ የሚል ነው:: “ከቤተ ክርስቲያኒቱ ሕግና ደንብ ውጭ በመነሳሳት የኦሮምያ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት እናቋቁማለን በማለት በሕገወጥ መንገድ የሚንቀሳቀሱ እንዲሁም በቅዱስ ሲኖዶስ ተባርኮ ጽላት ተሰጥቶናል በሚል በምድረ አሜሪካ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስም ቤተ ክርስቲያን አቋቁመናል የሚሉት፦ 1. ሊቀ አእላፍ ቀሲስ በላይ መኮንን፣ 2. አባ ገ/ማርያም ነጋሳ፣ 3. መምህር ኃ/ሚካኤል ታደሰ፣ 4. ቄስ በዳሳ ቶላ እነዚህ ግለሰቦች ቤተ ክርስቲያናችን በማታውቀው መንገድ በአመጽ በመነሳሳት ምእመናንን ግራ እያጋቡና እያሳሳቱ መሆኑን እንዲሁም ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ውጭ የክህደት ትምህርት ማስተማራቸው በመረጃ ተደግፎ ለቅዱስ ሲኖዶሱ ጉባኤ የቀረበ በመሆኑ እነዚሁ ከላይ ስማቸው የተጠቀሰ የኦሮምያ ቤተ ክህነት አደራጆች ነን የሚሉ ከድርጊታቸው ተቆጥበው በንስሐ እስኪመለሱ ድረስ ከየካቲት 11 ቀን 2012 ዓ.ም. ጀምሮ ከቤተ ክርስቲያናችን የተሰጣቸው ክህነት ተይዟል። በቤተ ክርስቲናያናችንም ስም ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ እንዳያደርጉና መንፈሳዊ አገልግሎት እንዳይሰጡ ታግደዋል::” በማለት ግለሰቦቹ ከጥፋት ድርጊታቸው ተጸጽተው ለመመለስ ከፈቀዱ ጉዳያቸው በድጋሚ እንዲታይ ቅዱስ ሲኖዶስ በውሳኔው አሳውቋል::ስብስቡ በኦሮሚያ ክልል የከፈታቸው ቅርንጫፍ ፅ/ ቤቶችም እንዲዘጉ ተወስኖል::

# የኮሮና ቫይረስ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ ጥንቃቄ እየተደረገ ነው

የኮሮና ቫይረስ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ ባለድርሻ አካላትና የክልል መስተዳድሮች አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሊያደርጉ እንዲገባ የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ ጤና ኢንስቲትዩት አስታወቀ።
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቶች የሴቶች ወጣቶችና ማኅበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የኢንስቲትዩቱን የድንገተኛ አደጋዎች ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከልን ጎብኝተዋል።
በጉብኝቱ ወቅት የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ኤባ አባተ ገለፃ በሽታው ከጉንፋን ቫይረስ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ቢሆንም በ14 ቀናት ውስጥ ሳል ንጥሻ፣ የትንፋሽ ማጠርና የጉሮሮ ህመም ምልክቶች የሚያሳይ ሲሆን ይህም በሽታው በፍጥነት እንዲዛመት ያደርጋል ሲሉ ለጎብኚዎቹ አስረድተዋል።
ዳይሬክተሩ አያይዘውም ቦሌ ጨፌ ኢቦላ ማዕከል የካ ኮተቤ አጠቃላይ ሆስፒታልና ቅዱስ ጳውሎስ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል አገልግሎት ለመስጠት ቅድመ ዝግጅት ያጠናቀቁ መሆናቸውን ጠቁመው፤ ነገር ግን በሁሉም የአገሪቱ ክፍል የመሸፈን አገልግሎት ሊኖር እንደሚገባ አሳስበዋል።
ቫይረሱ ወደ አገር እንዳይገባ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ጀምሮ የሚመለከታቸው አካላት እና ከ150 በላይ ባለሙያዎች ያካተተ ድንገተኛ ማዕከል በቅንጅት እየሠሩ መሆኑ ተገልጿል።
ሆኖም አንዳንድ ከቻይና ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ መንገደኞች ለምርመራ ፈቃደኛ ባመሆናቸው የፀጥታው ኃይል ድጋፍ ሊያደርግ እንደሚገባም ዶክተር ኤባ አባተ ገልጸዋል።

# መውቀስም ሆነ መወድስ ምክንያታዊ ይሁን !

ሀምሳ ዓመትን የጠባው የማርክሲስት ፖለቲካችን መስመር ለይቶ መጠፋፋትን በደማቁ አስተምሮናል፡፡ ከርዕዮተ ዓለም ባነሱ መርሆዎችና የአካሄደች ልዩነቶች ብቻ መገዳደልን የሙጥኝ እንድንል አስገድደናል፡፡ ‹‹ባላንጣ ነው›› ባልነው ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ (የእናት ልጅም ቢሆን) ጦር ጨብጠንና ዘገር ነቅንቀን እንድንፋለምም ክፉ ውርስ ጥሎብናል፡፡ የሀሳብና ምክንያታዊ ፖለቲካ ለነጠፈባት የዛሬዋ ኢትዮጵያችንም ይህ ልማድ (trend) እግር ተወርች ሆኖብን እንደዘለቀ አይታበልም፡፡ ልዩነት የተፈጥሮ ሕግ አንድ አካል መሆኑን ተረድቶ፤ በሚያግባቡ አጀንዳዎች በጋራ መስራት፤ በሚያነጣጥሉ ጉዳዮች ደግሞ ሠላማዊ ሆኖ መተጋገል ለኢትዮጵያ ፖለቲካ እንደ ሰማይ የራቀ ባህሪ ነው፡፡ ‹‹ጠላት›› የተባለው ወገን የሰራውን በጎ ተግባር ሁሉ በደቦ ማንኳሰስና በጅምላ ማውገዝ ፤ ‹‹ወዳጅ›› የተባለውን ደግሞ የረገጠውን ሁሉ ማወደስና ለቆመበት ሁሉ ማጎንበስ ያልተናጠበን የባህል ምች ነው፡፡

በዚህ የቸከና ፍፁም ሴረኛ በሆነ አካሄድ ለተቀፈደደችው ሀገራችን ታዲያ ጠልፎ አላፊዎች እንጂ አቅፎ አላፊዎች ሲከብሩ አላየንም፡፡ በዚህ ረገድ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ከበዓለ ሲመታቸው በኋላ ሊያነብሩት በፈለጉት ፖለቲካዊ ባህል ውስጥ ይህን የቆየና ሥር የሰደደ ልማድ መስበር ግድ ሆናባቸው ነበር፡፡ ጠ/ሚኒስትሩ በተለያዩ የአደባባይ ዲስኩራቸውና መልዕክታቸው ይህንን ‹‹ለለ አህዱ በከመ ግብሩ›› መርሃቸውን ሁሉም የፖለቲካ ተዋናዮች እንዲገዙት ሳይታክቱ ጥሪ አድርገዋል፡፡ ‹‹ከሴራ ፖለቲካ እንውጣ›› ሲሉም ደጋግመው ጠይቀዋል፡፡ እርሳቸውና መንግስታቸው የቱንም ያህል የህግ የበላይነትን ያለ አድሎና ኢ - ፍትሐዊነት ገቢራዊ ማድረግ ላይ የሚተቹባቸው አያሌ ነገሮች ቢኖሩም ከመጀመርያው ዕለት አንስቶ ሸብረክ ያላሉባቸው ጉዳዮች መኖራቸውን አንስቶ ዋጋ መስጠት ግን ተገቢም አስፈላጊም ነው፡፡

ለዚህ አንዱ ማሳያ የሚሆነው ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰሞኑን ወደ ተባበሩት ዐረብ ኢምሬቶች ያደሩጉት ጉዞ ነው፡፡ በሀገራቱ የነበራቸው ቆይታ በአመዛኙ ሊባል በሚችል ደረጃ ትኩረት ያደረገው በከባቢው በሚኖሩ ዜጎቻችን ህልውናና ኑሮ ላይ መሆኑ ስለሰው የሰጡትን የገደድ (Concern) መጠን ዘልቆ ለመረዳት ዕድል ሰጪ ነው፡፡ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ ከ15 ሺህ በላይ ኢትዮጵያዊንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በተገኙበት በዱባይ ያደረጉት ንግግር ይዘትም ለዚህ ማመሳካሪያ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው፡፡ ‹‹ሠው ሠው›› የሚሸተው ይህ የጠ/ሚኒስትሩ ንግግር በዓረቡ ኣለም ያሉት ወንድም እህቶቻችን ዛሬ ካሉበት የፍርሃት፣ የሰቆቃና የችግር ቆፈን አልፈው ተስፋንና አብርሆትን አሻግረው እንዲመለከቱ አብዝቶ የሚያበረታ ጉልበትም የሚሆን ነው፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያ ካለችበት ድንግዝግዝና አስቸጋሪ ሁናቴ ወጥታም ብዙዎች ልጆቿ ወደሚመኙላት ከፍታ መድረሷ አይቀሬ መሆኑንም የገለፁበት ዐውድ እንዲሁ በሥፍራው ለነበሩ ወገኖቻችን ልብን የሚያሞቅና ዳግመኛ ተስፋን የሚዘራ ነው፡፡

ጠ/ሚነስትር ዐቢይ አሕመድ ከንግግራቸውም በተሻገረ በተግባር በከባቢው የሚኖሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኞች ሥርዓተ አምልኮ የሚፈፅሙበት ስፍራ(ቤተክርስቲያን) ጥያቄ ምላሽ እንዲያገኝ ትልቅ ሚና መጫወታቸውም ሊያስመሰግናቸው የሚገባ ነው፡፡ በጥቅሉ ሲታይ ግን ያሳለፍነው ሳምንት ጠቅላይ ሚኒስትሩና ልዑካቸው ያደረጉ ጉዞ በብዙ መልኩ ለዜጎች ደህንነትና ህይወት ዋጋ የተሰጠበት፤ የሰው ልጅ ከማናቸውም የኢንቨስትመንትና ቁሳዊ ሀብቶች የገዘፈ ትርጉም ያለው መሆኑን ትምህርት ሰጥቶ ያለፈ በመሆኑ ሊበረታታ የሚገባው ሁነኛና ወሳኝ የመንግስት ተግባር ነው እንላለን፡፡ አሳዛኙ ነገር ግን በማርክስና በመስመር ፖለቲካ ለጨቀየው ተዋስያዋችን ይህ ዓይነቱ በጎ እርምጃም ቢሆን ከጭቃ ጅራፍ ሊያመልጥ አለመቻሉን ነው፡፡ ‹‹የጠላነው ሁሉ የተረገመ ይሁን›› በሚለው ያልተፃፈ ሕጋችን ይህ የጠ/ሚኒስትሩም ሆነ የመንግሥት አዎንታዊ ሥራ በተራ የንግግር ፀጉር ስንጠቃዎች እንዲጠለሽየተለያየ ጥረት ሲደረግ ማየት እጅጉን አስተዛዛቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ኢትዮጵያን በመውደድ እና እንድትደርስ በምንሻው የነገ ትልማችን መሃል የተንፈራቀቀም ባይሆን ልዩነት እንደሚኖረን ይገመታል፡፡ ሆኖም ግን ኢትዮጵያ ማለት ከምንም ነገር በፊት ዜጎቿ መሆኗ ላይ መግባባት ካለን መርገማችንም ሆነ ምርቃታችን ቋንቋና ሥርዓት ሊበጅለት ይገባል፡፡ መወቀስም ሆነ መወደስ በምክንያትና ምክንያት ብቻ ይሁን ስንልም ደግመንና ደጋግመን የመርህ ሰውነትን በማስቀደም መሆኑን በመረዳት ድጋፍና ተቃውሟችንን በወጉ ልናራምደው ይገባል እንላለን፡፡

**ግዮን መጽሔት**

**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና**

**ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**

**በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ዋና አዘጋጅ**

ሮቤል ምትኩ

አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ ወረዳ 2

የቤት ቁጥር 475

**ማኔጂንግ ኤዲተር**

ኄኖክ ገለታው

**አዘጋጅ**

ብሩክ መኮንን

ፍቅርተ ተሾመ

ሙሉጌታ አክሊሉ

**አምደኞች**

ፍቅሩ ኪዳኔ (**ከሲውዘርላንድ**)

ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ

ተስፋ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ

መታሰቢያ መልአከ ሕይወት

**ጸሐፊ**

ሠላም ግርማ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**

አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 552/1

አምባቸው ህንፃ 2ተኛ ፎቅ ቢሮ ቁ. 207

ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029

ስልክ ፡ +251 911 227661 +251 912 165606

+251 118 12 2333

ኢ-ሜይል፡

enqu2013@ gmail.com

Ghion2011meg@gmail.com

Facebook

Gihon-meg Fekadu

www. facebook.com/enqu2013

**አታሚ**

ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ

ወረዳ 10 የቤ.ቁ. 066/ሀ

0911223335/ 0911420506

በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም

# ሌንጮ ባቲ በጌታቸው ረዳ መንገድ?

በርካቶች ዕምነት ከአወዛጋቢነቱ ይልቅ አግላይነቱ ያይላል ይባልለታል፡፡ በግላጭ አቋም ይዞ አይናገረው እንጂ ለአንድ ወገን ፖለቲካ ማስተጋቢያነት መዋሉንም የገዛ ሰራተኞቹ አይክዱትም፡፡ የአንድ አካባቢ ልሂቃንን ሰብስቦ ሌላ የማህበረሰብ ክፍልን በፕሮፓጋንዳ አረር ማቃጠልም የቸከ ድርጊቱ ለመሆኑ አባሪዎችን መጥቀስ ከባድ አይሆንም፡፡ ከታሪክ፣ ከተጨባጭ መረጃና ከሥነ አመክንዮ የተፋለሱ "ዘገባዎችን" መስራትም ቆጥሮ ከተረከበው ኃላፊነት መሃል ነው፡፡ መቀመጫውን ኳታር ያደረገው አልጀዚራ የቴሌቪዥን ጣቢያ፡፡ አልጀዚራ ኢትዮጵያን አስመልክቶ በሚያሰራጫቸው አጫጭር ዘገባዎቹም ሆኑ ዘለግ ያሉ ዶክመንተሪዎቹ የተንሸዋረረ ዕይታ ያለው የቴሌቭዥን ጣቢያ ስለመሆኑ ተደጋግሞ ታይቷል፡፡ በአመዛኙ ለኦሮሞ አክራሪ ብሔርተኞች ልሳን ሆኖ እንደኖረም በሚያሰናዳቸው "ኢትዮጵያን የተመለከቱ" ዝግጅቶቹ ማጤን ይቻላል፡፡ ምንም እንኳ ጣቢያው እንዲህ ባለ መሳከርና አድሏዊ አሰራር ውስጥ የተዘፈቀም ቢሆን፣ ድምፅ የሆናቸው የተወሰኑ ወገኖች በመኖራቸው ሚናውን በዜሮ ማባዛት ተገቢ ላይሆን ይችላል፡፡ ወደ ሰሞነኛው ጉዳይ እንመለስ፡፡

አልጀዚራ ከቀናት በፊት በሳምንታዊው "Up Front" በተሰኘ ዝግጅቱ "Is Ethiopia sliding backwards under Abiy Ahmed" በሚል ርዕስ በወሳኝ ነጥቦች ያለ ያተኮረ አጭር መሰናዶ አቅርቦ ነበር፡፡ በዚህ መሰናዶው ኢትዮጵያ ያለችበትን አሁናዊ ሁናቴ በተመለከተ ለሙግቱ ምላሽ እንዲሰጡ በስቱዲዮ የተጋበዙት ደግሞ የጠ/ሚኒስትሩ ከፍተኛ አማካሪ አቶ ሌንጮ ባቲ ናቸው፡፡ አቶ ሌንጮ ለዓመታት ተቃዋሚ ሆነው ብዙ እሮሮ ባሰሙበት የቴሊቪዥን ጣቢያ የመንግሥት ገመና ከታች ሆነው የቀረቡበት እውነታ በራሱ ለውጥ ቢሆንም በዚህ አጭር ቆይታቸው ለተሰኑላቸው ጥያቄዎች የሰጧቸው ምላሾች ግን ግራ አጋቢና አስተዛዛቢ መሆናቸው አልቀረም፡፡ በተለይ የጥያቄዎቹ ይዘቶች ከዚህ ቀደም እርሳቸው "ታገልሉለት" ከሚሉት የነፃነትና የዴሞክራሲ ጉዳይ ጋር በእጅጉ ተዛምዶ የነበራቸው መሆኑ፣ ምላሻቸውን ሳይሆን ያላቸውን ፖለቲካዊ ስብዕና ገፍተን እንድንጠይቅ ያስገደድናል፡፡ አቶ ሌንጮ በዚህ የቴሌቪዥን ቆይታቸው በድፍረት ፈቅደው ከካዷቸው አሊያም ካድበሰበሷቸው እውነታዎች መካከል ሦስቱን አንስተን እንመልከት፡፡

## 1. የፖለቲከኛ እስረኛ የለም!

አቶ ሌንጮ ባቲ በለየለት ፍጽምና የአለቃቸውን የጠ/ሚኒስትር ዐቢይ መንግሥትን ለመከላከል የቀረቡ በመሠለባቸው መድረክ ፈቅደው ከካዱት የፈጠጠ እውነት መካከል አንዱ በሀገሪቱ "አንድም የፖለቲካ እስረኛ የለም" ማለታቸው ነው፡፡ ይህ አቋማቸው ደግሞ ያለፉትን ወራት በ "Human Right Watch" እና "Amnesty International" ተቋማት በተከታታይ ሲወጡ የነበሩ መግለጫዎችን እንኳ ከሁለት ዓመት በፊት ትኩረት ሰጥተው በሚከታተሉበት መጠን እንዳያጤኑ ያደረጋቸው ይመስላል፡፡ ለአቶ ሌንጮ "የፖለቲካ እስረኛ" የሚለው ሐረግ ሳይቀር ከህወሓት/ኢህአዴግ ትውስታቸው ጋር አብሮ ተቀይዷል መሠል፣ ማንጻርያቸውና መከላከያቸው የቀደመውና የቀደመው መንግሥት ብቻ ነበር፡፡ የሰኔ 15ቱን ግድያ ተከትሎ ለወራት በእስር የቆዩትንና ክስ ተመሥርቶባቸው በማረሚያ ቤት የሚገኙት (ምንም ዓይነት ማስረጃ ሳይገኝባቸው) የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ አባላት በአቶ ሌንጮ መረዳት ውስጥ ወይ "አሸባሪ" ናቸው አለያም ረብ የሌላቸው ሰዎች ናቸው፡፡ በዐቃቤ ሕግ መዝገብ በግላጭ "ወጣቶችን ለአባልነት መመልመልና ማደራጀት" የሚል ክስ የቀረበበት የአብን ህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ክርስቲን ታደለ የፖለቲካ እስረኛ ካልተባለ ምን ሊባል እንደሚችል አቶ ሌንጮን ደግሞ መጠየቅ ሳያሻ አይቀርም፡፡

ህወሓት መራሹ የኢህአዴግ መንግሥት በ2006 ዓ.ም መጨረሻ የነፃው ፕሬስ አባላትን ለማሳደድ በፈረበካቸው የ"ጥፋት ወንጀሎች" ላለፉት ስድስት ዓመታት ጉዳዩ ሲንከባለል መጥቶ የሰባት ዓመት እስር ተፈርዶበት በማረሚያ ቤት የሚገኘው የቀድሞዋ ዕንቁና የአሁኗ ግዮን መጽሔት ማኔጂንግ ዳይሬክተር ፍቃዱ ማኅተመወርቅስ የፖለቲካ ዕስረኛ ካልተባለ፣ ምን የዳቦ ስም እንደሚሰጠው የሚያውቁት አቶ ሌንጮ ባቲ ብቻ ናቸው፡፡ ድኅረ ዐቢይ ባለችው ኢትዮጵያ "አንድም የፖለቲካ ዕስረኛ የለም" ብለው ለመናገር ያልተሸማቀቁት አቶ ሌንጮ በህወሓት/ኢህአዴግ ዘመን ግን የበዛ ተቃዋሚ እንደነበሩ ይታወሳል፡፡ ይህም ህወሓት በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ውስጥ በማናቸውም መልኩ ተሳትፎ የነበራቸውን ጋዜጠኞችና ፖለቲከኞች ያስርና ያሳድድ እንደነበረ ከማንም በላይ ለመረዳት የሚያበቃ ግንዛቤ አያጡም፡፡ በ2006 ዓ.ም በዕንቁ መጽሔት ላይ በተፈጠረ "የግብር ማጭበርበር ወንጀል" ሥም በተከፈተ የክስ መዝገብ እርሳቸው ከ "ድል" በኋላ የጠ/ሚኒስትር አማካሪ በሆኑባት ኢትዮጵያ ግዞት ከመጣል በላይ ለአንድ ጋዜጠኛ "የህሊና እስረኛ"ነት ከየት ሊመጣ ይችላል?

## 2. ኢንተርኔት አልተቋረጠም!

ሁለተኛው የአቶ ሌንጮ ዕውነትን አጋድሞ የመሠየፍ ሙከራ የሚነሳው ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ ድኅረ ዐቢይ ባለችው ኢትዮጵያ ያለውን የኢንተርኔት ተደጋግሞ መቋረጥ ከጥራትና ከሽፋን አነስተኛ መሆን ጋር ለማማያዝ የሞከሩበት የለየለት ቅጥፈት ነው፡፡ ይህ በተደጋጋሚ በመንግሥትም ሆነ በኢትዮ ቴሌኮም የታመነ (admit) ዕውነት በአቶ ሌንጮ ምላሽ ውስጥ ተፈቅዶ መካዱ ግን አስገራሚ ነው፡፡ እርሳቸው ይህንን ምላሽ በሚሰጡበት ደቂቃ በምዕራብ ኦሮሚያ አካባቢዎች እኮ የኢንተርኔት ሳይሆን የመደበኛ ስልክ አገልግሎትም ከተቋረጠ ወር አልፎታል፡፡ መንግሥትም አልካደውም፡፡ ብሔራዊ ፈተናዎችንና ፖለቲካዊ ክስተቶችን ተከትሎ በመላው ሀገሪቱም ሆነ በተለዩ አከባቢዎች የኢንተርኔትን ሽፋን በከፊልም ሆነ በሙሉ መዝጋት ለውጡን ተከትሎ ካስተዋልናቸው ዓበይት እውነታዎች መካከል አንዱ ቢሆንም ሽንጣቸውን ገትረው የአለቃቸውን ገመና ለመሸፈን በአልጀዚራ ስቱዲዮ ለተጣዱት አማካሪ ግን ተጨማሪ ምርመራን የሚሻ "አሉባልታ" ነው፡፡

የኢንተርኔት ጥራት አነስተኛ መሆንና የተደራሽነት ችግር፣ ይህንን ያገጠጠ የመንግሥት ነውር ለመሸፈን ምን ያህል በቂ ማመካኛዎች እንደሆኑ ባይታወቅም አቶ ሌንጮ ግን የመሠላቸውን ምክንያት እየደረደሩ ከሚሰነዘረው ወቀሳ ሁሉ ‹‹መንግስታቸውን›› መከላከል የማይነጥፉበት ተግባራቸው ሆኗል፡፡

## 3. ሠላምና መረጋጋት አለ!

አቶ ሌንጮ በዚህ የቴሌቭዥን ቆይታቸው የሰጡት ሌላው አስገራሚ ምላሽ ደግሞ በሀገሪቱ ሠላምና በዜጎች ደህንነት ላይ ያተኮረው የንግግራቸው ክፍል ነው፡፡ በኢትዮጵያ ለውጡን ተከትሎ ከአንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን በላይ ዜጎችን ከቀያቸው ያፈናቀለ ክስተት ቢስተናገድም፤ በርካታ ዜጎች በማንነታቸው ብቻ የጥቃት ዒላማ ሆነው መገደላቸው በግልፅ



ቢታወቅም፤ ህዝቦች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ተዘዋውሮ የመስራትና የመንቀሳቀስ መብታቸው የተገደበ መሆኑ እማኝ የማያሻው ቢሆንም፤ የሞቱ፣ የተሰወሩና የታገቱ ዜጎች የፖለቲካ ተዋስያዋችን አካል መሆናቸው ገና የበረደ ባይሆንም፤ "ሁሉም የኢትዮጵያ ብሔሮች በተድላ ህይወት ውስጥ እየኖሩ ናቸው" ብሎ እንደመሳለቅ ያለ ምላሽ ከአቶ ሌንጮ አንደበት መስማት ግን ያሸማቅቃል፡፡ ሞልተው የፈሰሱ፣ በአመራሩ አቅምና ብቃት ማነስ ብቻ መፈታት ያቃታቸውን ችግሮች ወደ ሌላ አካል ጣት እየቀሰሩ ጠ/ሚኒስትሩንና መንግሥትን ብፁዕ ማድረግስ ከአቶ ሌንጮ ውጪ ለማን የሚቻል ይሆን?

በአጠቃላይ ከፍ ሲል በመንደርደርያችን በጠቀስነው አልጀዚራ የቴሌቭዥን ጣቢያ ተገኝተው ገለልተኛ የሰብዓዊ መብት ተቋማትና የመንግስት አመራሮች ሳይቀሩ ያመኑትን እውነት ዓይናቸውን ጨፍነው ለመካድና የፈለጉት የጠ/ሚኒስትሩ ከፍተኛ አማካሪ አቶ ሌንጮ ባቲ ነገራቸው ኹሉ የቀድሞውን የኮሚዩኒኬሽን ሚኒስቴር አቶ ጌታቸው ረዳን እየመሰለ ነው፡፡ "ጠላት" ደስ አይበለው በሚል ስሌት ብቻ ህዝብ በሞት፣ መፈናቀልና መቁሰል ዋጋ እየከፈልባቸው ያሉትን አያሌ ዓይን ያወጡ እወነቶችን ለመካድና ለማድበስበስ መሞከር ነገ የሚያስተዛዝበው ሌላ ሳይሆን እርሳቸው ራሳቸውን መሆኑን ግን መማር አልቻሉም፡፡ በፖለቲካ አመለካከታቸውና በሙያቸው ምክንያት የግፍ እስረኛ የሆኑ ዜጎች ዛሬም ባልጠፉባት ኢትዮጵያ፣ ሀቅን ፈቅዶ ለመካድ ዓለም አቀፍ ሚዲያ ላይ እስከመሠየም የደረሰው ድፍረት ግን ትናንት የተጣባን ክፉ የአፈቀላጤነት ባህሪ ዛሬም እንዳልተናጠበን ማሳያ ከመሆን የሚዘልል ትርጉም አናገኝለትም፡፡ የአቶ ሌንጮ ቁርጥ ጌታቸው ረዳን ለመምሰል መታተር ደግሞ "ሰው አይውጣላችሁ" ለመባላችን ጉልህ ማሳያ ሆኖ ታሪክ መመዝገቡን ቀጥሏል፡፡

# <<ነጻ አውጪ የሆነች ቤተክርስቲያን ነጻነት ልታጣ አይገባም>>

## <<በአንድነት የማያምኑ ሰዎች ስለአንድነት እየተናገሩ ነው>>

## <<በሰይፍና በገጀራ እያስፈራሩ ማተብህን በጥስ መባል ተጀምሯል>>

## <<ቤተክርስቲያን እንድትጠፋ የሚፈልጉት አካላት ከአንድ አቅጣጫ ብቻ አይደሉም>>

መምህር ምህረትአብ አሰፋ



መምህር ምህረትአብ አሰፋ ተወልደው ያደጉት በቀድሞው ኢሉባቦር ክፍለሃገር መቱ ከተማ ነው፡፡ የልጅነትና ታዳጊነት ዘመናቸውን በፈለገ ሕይወት የካህናት ማሰልጠኛ ኪዳነምህረት ገዳም ውስጥ እንዳሳለፉ ይናገራሉ፡፡ ከድቁና አንስቶ አሁን እስካሉበት የአገልግሎት ደረጃ ስመድረሳቸው የብፁዕ አቡነ ፊልጶስ አሻራ ግዙፍ መሆኑንም በመግለጽ "እየኖርኩ ያለኹት የልጅነት ሕልሜን ነው" ይላሉ፡፡

ወጣቱ የሃይማኖት መምህር ምህረትአብ አሰፋ ከልጅነት የሰንበት ትምህርት ቤት ቆይታቸውና የድቁና አገልግሎታቸው በኋላ ወደ ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ በመግባት በሥነ መለኮት ትምህርት ተመርቀው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥብከተ ወንጌል አገልግሎት መሥጠት ከጀመሩ ዓመታት አልፏቸዋል፡፡

በተለያዩ ጊዜያት (በተለይም ባለፉት ዘጠኝና አስር ዓመታት) ቤተክርስቲያን ላይ የሚደረጉ ጥቃቶችንና ትንኮሳዎችን በግልጽ በመቃወም፣ ሃይማኖታዊ አስተምህሮዎች ላይ ለሚነሱ ጥያቄዎችም ፈጥነው ለምዕመናን ምላሽ በመስጠት የሚታወቁት መምህር ምህረተአብ አሁን ላይ የቤተክርስቲያኒቱን ህልውና ለማስጠበቅ በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ የፊት ተሰላፊ በመሆን "የማንቂያ ደወል" የተሰኘ የስብከት መርሃ ግብር አዘጋጅተው በማስተማር ላይ ይገኛሉ፡፡

ባለፉት ሁለት ዓመታት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ የተጋረጠውን አደጋ አስቀድመው ስለመጠቆማቸው የሚነገርላቸው መምህሩ፣ ከሳምንታት በፊት በአዲስ አበባ መገናኛ አካባቢ በፀጥታ አካላት የተገደሉት ምዕመናን ተከተሎ በዓውደ ምህረቶች ጭምር እንዳያስተምሩ ፖሊስ እስከማስተጓጓል ስለመድረሱ ይናገራሉ፡፡ ካለፈው አንድ ዓመት ተኩል አንስቶ ቤተክርስቲያኗ ላይ እየደረሱ ስላሉ ጥቃቶች፣ ቤተክርስቲያኗን ለመከፋፈል በተግባር እየተደረገ ስላለው እንቅስቃሴና አገሪቱ ስለምትገኝበት ወቅታዊ ሁኔታ የግዮን መጽሔት ጋዜጠኞች ሮቤል ምትኩና ኄኖክ ገለታው ተከታዩን ቆይታ ከእርሳቸው ጋር አድርገዋል፡፡ መልካም ቆይታ!

►

**ግዮን፡- በቅርቡ በአዲስ አበባ በተለምዶ መገናኛ 24 ተብሎ በሚጠራው አከባቢ ከአምልኮ ቦታ ጋር በተያያዘ የሰዎች ሕይወት የጠፋበትና በርካቶች ለአደጋ የተጋለጡበት ሁኔታ ተከስቶ ነበርና እንደ ሃይማኖት መምህርነትዎ የተሰማዎትን ቢነግሩን ?**

መምህር ምህረትአብ፡- የሆነውን ነገር ለመቃወምና ልክ አይደለም ብለህ ለመናገር የሃይማኖቱ ሰው መሆን ብቻ ሳይሆን፣ ሰው መሆንህ ብቻውን በቂ ነው፡፡ ድርጊቱን እንድትኮንን ሰብዓዊነት በራሱ ያስገድድሃል፡፡ ምክንቱም ፖሊስ ከሕዝብ ነው የወጣው፡፡ መንግሥት "ሕዝብን ጠብቅበት" ብሎ በሰጠው መሳሪያ የራሱ ወገን ላይ ተኩሶ መገደል እንደ ሃይማኖት ብቻ ሳይሆን እንደ ሰብዓዊነትም ትክክል ያልሆነ ድርጊት ነው - በመጀመሪያ ደረጃ፡፡

በኹለተኛ ደረጃ ይዞታው የሃይማኖት ነው አይደለም ፤ ሕጋዊነቱ ፀድቆ ይሰጥ አይሰጥ ራሱን የቻለ ጥያቄ ነው፡፡ ነገር ግን እዛ ቦታ ላይ የቃል ኪዳኑ ታቦት አለ፣ እንዴት መጣ? ማን አመጣው? እንዴት ሊሆን ቻለ? ለሚለው ቤተ ክርስቲያን የራሷ መዋቅር ስላላት ቦታው ላይ ችግር አለ ከተባለ ከሚመለከተው ክፍል ጋር ትነጋገራለህ እንጂ ፣ ባዶ እጁን "ኃይል የእግዚአብሔር ነው" እያለ የሚዘምር ወጣት ላይ አትተኩስም፡፡ ምዕመንን በጥይት መግደል በምንም ተዓምር የመጨረሻው አማራጭ መሆን የለበትም፡፡

በመነጋገር መፍታት እየተቻለ፣ ነገሩን በዚህ መንገድ እልባት መስጠት ተገቢ አይደለም፡፡ እነዚህ ልጆች እኮ "የምናመልክበት ቦታ ይሰጠን ፤ እዚህ አካባቢ አቅመ ደካማ አረጋውያን አሉ፣ ወደ ቦሌ መድኃኒዓለም መሄድ ይርቃቸዋል ፤ ለቅዳሴ ለቁርባን እንኳን መድረስ አልቻሉም፤ ስለዚህ የአምልኮ ሥፍራ ያስፈልገናል" ነው ያሉት፡፡ ይሄ ደግሞ መብታቸው ነው፡፡

**ግዮን፡- ከቤተክርስቲያኗ ባሻገር የአንድ አካባቢ ማኅበረሰብ የአምልኮ ቦታ ሲያገኝ መንግሥት ተጠቃሚ የሚሆን አይመስለዎትም ?**

መምህር ምህረት አብ፡- በትክክል፡፡ ወጣቱ የአምልኮ ቦታ ሲያገኝ ከማንም በላይ ተጠቃሚው መንግሥት ነው፡፡ በሥነ ምግባር ትውልዱ ይታነፃል፡፡ ይኸውልህ ደርግ እንደወደቀ ብዙ ፓርቲዎች በሥሩ ተነስተዋል፣ በዋነነት ሁለቱን እናውቃለን፡፡ እነሱ እግዜር የለሾች ሆኑ፤ እግዜር የለሾች ደግሞ ለእግዜር የለሾች መሆን ስላልቻሉ እርስ በርሳቸው በጥይት ተቆላሉ፡፡

"ካህናቱ ሕዝብን ሊያስፈራሩበት ነው የሥነ ምግባር ትምህርት ብለው በትምህርት ካሪኩለም ውስጥ ያካተቱት" በሚል የእግዚአብሔር ትምህርት ከት/ቤት ወጣ፡፡ የእግዚአብሔር ትምህርት ሲወጣ ታዲያ ት/ቤቱ የብልግና ት/ቤት ሆነ፡፡ ምክንያቱም 50 ዓመት ሙሉ ዓለማችን "እግዚአብሔር የለም" ብላ በኮሚኒዝም ርዕዮተ ዓለም ሁሉን እኩል ባለፀጋ አደርጋለሁ ብላ እኩል ድሃ ነው ያደረገችው፡፡ እግዚአብሔር የሌለበት ት/ቤት፣ እግዚአብሔር የሌለበት ቤት፣ እግዚአብሔር የሌለበት አገር ሰላም ይርቀዋል፡፡

ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ባላወቁና ፈሪሃ እግዚአብሔርን ባጡ ቁጥር የሚፈሩት አይኖርም፡፡ ሰው የሚገዛው ሕሊናውና አምላኩ ነው፡፡ ሕሊናውንና አምላኩን የምንገልበት ከሆነ ለራሱም ለአገርም አይጠቅምም፡፡ አሁን እየፈረሱ ያሉት የእምነት ተቋማት ትውልዱን በሥነ ምግባር የሚቀርፁ ፈሪሃ እግዚአብሔር እንዲኖረው የሚያደርጉ ከተለያዩ ሱሶች ርቆ ጥሩ ዜጋ እንዲሆን የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ስለዚህ ማህበረሰቡ እንኳን ባይጠይቅ መንግሥት በራሱ ፍላጎት እንዲህ ዓይነት ቦታዎችን ለትውልዱ መስጠትና ማስረከብ ይኖርበት ነበር፡፡ ወጣቶቹ ምንም ሳያጠፉ ነው የተገደሉት፡፡ የምንፀልይበት፣ የምንቀርብበት፣ የምናመልክበት፣ የምናድርበትና የምንማርበት ሥፍራ ይሰጠን ነው ያሉት፡፡

**ግዮን፡- በተለይም ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ በቤተክርስቲያን ላይ በተለያዩ ቦታዎች እየደረሰ ያለውን ጥቃት ተከትሎ ሥልጣን ላይ የሚገኘው መንግሥታዊ አካል ቤተክርስቲያንን ረስቷታል፣ በመንግሥታዊ መዋቅር ውስጥ ያሉ አንዳንድ አካላትና ሌሎች የተደራጁ ቡድኖችም ቤተ ክርስቲያቱን የማዳከምና የማጥፋት ተልዕኮ አንግበው እየተንቀሳቀሱ ነው የሚሉ ስሞታዎች ይሰማሉ፡፡ ታዝበውታል?**

መምህር ምህረትአብ፡- ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እንድትጠፋ የሚፈልጉት አካላት ከአንድ አቅጣጫ ብቻ ናቸው ብሎ መደምደም አይቻልም፡፡ ከብዙ አቅጣጫ ቤተክርስቲያኗን ለማጥፋት የሚደረግ እንቅስቃሴ መኖሩን ታዝበናል፡፡ ይህቺ ቤተክርስቲያን የአገር ባለውለታ ናት፡፡ ዓድዋ ዘምታ፣ ፀሎተ ማርያም ደግማ፣ ካህነቱን አስቀድማ፣ ታቦቱን ይዞ ኢትዮጵያ ነፃ ያወጣች ናት፡፡ ግን ዛሬ ላይ ይህቺ ኢትዮጵያን ነፃ ያወጣች ቤተ ክርስቲያን ነፃነቷን እያጣች ነው፡፡ ነፃ አውጪ ነፃነቱን ሊያጣ አይገባም፡፡

> **ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ቅዱስ ያሬድንና ሌሎችንም ብትመለከት ደካማም ጠንካራም ጎን አላቸው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ኖህ ሰክሮ ወደቀ ያለን እኮ ኖህን እግዚአብሔር ሊያሳጣው ፈልጎ አይደለም፡፡ "ብርቱዎች፣ ጀግኖችና ጎበዞችም ይወድቃሉ" የሚለውን እውነታ እንድንማርበት ነው**

ኦሮምኛው፣ አማርኛው፣ ትግርኛው ቋንቋው ሁሉ እንዳይጠፋና ዛሬ እንዲደርስ ለአገርም ለቋንቋም ዋጋ ከፍላለች፡፡ ለባህላችን ዋጋ ከፍላለች፡፡ ባለውለታህን መርሳት የለብህም፡፡ አሁን ያለው ነገር "እንዴት መጣ?" ስንል በመጀመሪያ ደረጃ ቤተ ክርስቲያኒቷ እንደበደለቻቸው የሚያስቡ ሰዎች አሉ፡፡ ለምሣሌ አንድ ንጉሥ ኦርቶዶክስ ሆኖ 50 ዓመት ወይም 40 ዓመት ገዝቶ ከሆነ ጠንካራም ደካማም ጎን ይኖረዋል፡፡ የበደለውም የጠቀመውም ግን እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሳይሆን እንደ ግለሰብ ነው፡፡

መውደቅና መነሳት ፤ ሃጢአትና ፅድቅ የብሔር፣ የአንድ ሃይማኖት ጉዳይ ሳይሆን አዳማዊነት ወይም ሰው የመሆን ጉዳይ ነው፡፡ አሁን ትልቁ እያስቸገረን ያለው ጅምላ ጭፍጨፋ ነው፡፡ ጅምላ ጭፍጭፋ በጦር መሳሪያ ብቻ አይደለም፣ በንግግርና በአስተሳሰብም አለ፡፡ አንድ የኦሮሞ ንጉሥ በድሎ ከሆነ "ኦሮሞ ሁሉ" ካልን ጅምላ ጭፍጨፋ ነው፡፡ "ትግሬ ሁሉ፣ አማራ ሁሉ" ስንል ጅምላ ጭፍጨፋ ነው፡፡ ባል ሲበድል ሴቶች ሁሉ "ወይ ወንድ" ካሉ ጅምላ ጭፍጨፋ ነው፡፡

**ግዮን፡- በአገሪቷ አሁን ላይ የሚታየው ጽንፍ የያዘ ብሔርተኝነት ቤተክርስቲያኒቱ ላይ በቀጥታ ተፅዕኖ አሳድሯል ብለው ያስባሉ?**

መምህር ምህረትአብ፡- እሱ በግልፅ የሚታይ ነገር እኮ ነው፡፡ በቀዳሚነት የጎሳ መነጽርን ከዓይናችን ላይ አውጥተን ሰው የመሆን መነጽር ልናደርግ ይገባናል፡፡ ሰው ሲሞት "የእዚህ ጎሳ ወይም ብሔር ሰው ሞተ" ከማለት ይልቅ "ክቡሩ የሰው ልጅ ሞተ" ብለን መቆጨት አለብን፡፡ በዚህ ሂደት እምነቱ ኦርቶዶክስ ሆኖ ብሔሩ አሮሞ የሆነ አንድ ሰው በአንድ አጋጣሚ በደል ቢያደርስ "የዛሬ 100 ዓመት እኮ ኦሮሞዎች እንዲህ አድርገውናል" ማለት ስህተት ነው፡፡

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ቅዱስ ያሬድንና ሌሎችንም ብትመለከት ደካማም ጠንካራም ጎን አላቸው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ኖህ ሰክሮ ወደቀ ያለን እኮ ኖህን እግዚአብሔር ሊያሳጣው ፈልጎ አይደለም፡፡ "ብርቱዎች፣ ጀግኖችና ጎበዞችም ይወድቃሉ" የሚለውን እውነታ እንድንማርበት ነው፡፡ በዚህ ስሌት እየተጓዙ "የኦርቶዶክስ ንጉሥ በድሎናልና ይህቺን ቤተክርስቲያን ጥሏት" ማለት ሃይማኖቷን አሳንሶ ከግለሰቦች ድካም ጋር ማያያዝ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ተገቢ አይደለም፡፡

በእንዲህ ዓይነት መጥፎ ዘር የተዘራባቸው ሰዎች አሉ፡፡ "ቤተክርስቲያኗ መሬትህን ነጥቃኸለች ፤ መስቀል ወረደ ብርሃን ወረደ በሚል ኦርቶዶክስ እያስፈራራች የመሬት ወረራ አድርጋብሃለች" እያሉ የሚቀሰቅሱና ►

የሚሰብኩ ምንም ባላወቁ ሕፃናት አዕምሮ ላይ ጥላቻን የሚዘሩ ሰዎች አሉ፡፡ ሀቁ ግን ቤተክርስቲያን የመሬት ወረራ አድርጋ አለማወቋ ነው፡፡ ሰው ከእርሻው ላይ መሬቱን ቆርሶ ቢሰጥ፣ ለመንፈሳዊ ግልጋሎት ቢያውል ተጠቃሚው ሕብረተሰቡ ነው፡፡ አሁን ቤተክርስቲያኒቱ የተሸከመችውን ሸክም እኮ መንግሥት አይችለውም ነበር፡፡ በየፀበሉ ሥፍራ እኮ በሚሊየን የሚቆጠር በሽተኛ ነው ተኝቶ ያለው፤ ይሄ ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ሸክም ነው፡፡ በፀበሏ ፈውስና ተዓምራቶችን ታደርጋለች፣ ነፍሱ የሚደገፍበትን ነገር ታደርጋለች፣ በሰንበቴው፣ በማህበራዊ ኑሮዎች አስተሳስራ ሕዝቡን አንድ አድርጋ ሰላምን፣ አንድነትን ፍቅር በመስበክ ለሕዝብ ትልቅ ጥቅም እየሰጠች ነው፡፡ የወሰደችውን መሬት ለባለፀጋ ወይም ለፋብሪካ ጥቅም አይደለም ያዋለችው ፤ መልሳ ሕዝብን ነው እያገለገለችበት ያለችው፡፡

ግን እነዚህ ጥላቻ የተዘራባቸውና "መሬትህን ነጥቃለች" የተባሉ ሰዎች አሁን ሄደው ቤተክርስቲያንን ቢያቃጥሉ አይፈረድባቸውም፡፡ ምክንያቱም የሚያደርጉት ሁሉ መሬታቸውን ያስመለሱ እየመሰላቸው ስለሆነ ነው፡፡ ሰው ደግሞ የዘራበት ቦታ ላይ ነው ምርቱን የሚያጭደው፡፡

**ግዮን፡- ይሄን ለመቅረፍ ምን መደረግ አለበት?**

*መምህር ምህረትአብ፡-* ወደ እሱ እየመጣኹ ነው፡፡ በቀዳሚነት እንዲህ ዓይነቱን አመለካከት ነው ማጥራት ያለብን፡፡ እውነታውን በደንብ ማወቅ፣ ሃይማኖቱን መረዳት ይገባል፡፡

ሌላው "የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ስታጠምቅህ የነበረው የሥላሴን ልጅነት ልትሰጥህ ሳይሆን የእገሌን ብሔር ልትሰጥህ ነው" የሚል ቅስቀሳም እየተደረገ ነው፡፡ አብሮ ሲያስቀድስ "ኦርቶዶድስ ተዋሕዶ ነኝ" ሲል የነበረው "በጥምቀት የሥላሴን ልጅነት ሳይሆን ለካስ የእከሌን ብሔር እንድወርስ ነው ያደረጉኝ፡፡ ያነፁኝም ከብሔር እንጂ ከአዳማዊ ሃጢአት አይደለም" እንዲል ቋንቋውንና ያጠመቀውን ካህን እንዲጠላ ነው እየተደረገ ያለው፡፡

ይህንን ጥፋት ለማስቆም እነዚህ መጥፎ ዘር በቤተክርስቲያኒቷ ላይ የሚዘሩት ሰዎች የጥላቻ ስብከታቸውን እንዲያቆሙ ማድረግ ይገባል፡፡ በምንም መንገድ ቢሆን የጥላቻ ዘር መዘራት የለበትም፤ አስተሳሰቡን ካላጠፋነው ድርጊቱን አናጠፋውም፡፡ አሁን እንዲህ የሚያደርጉ ሰዎችን ማሰርና መግደል ሳይሆን ያለብን ክፉውን አስተሳሰብ ማከምና መዋጋት ነው፡፡ በቴሌቭዥን ጣቢያዎች እኮ እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ቀርበው እየተናገሩ ነው ያሉት፡፡ "ያማኝ አከበረኝ የነገረኝ ገደለኝ ነው" እንደሚባለው አንድ ሰው በአላዋቂነት የተናገረውን ነገር ሚዲያ ላይ ማቅረብ አሳዛኝ ነው፡፡

ቤተክርስቲያኒቷ ላይ ግልፅ ጦርነት እየተደረገ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱን መጥፎ አስተሳሰብ በህዝብ ላይ የሚዘሩት ሰዎች በህግም ሊጠየቁ ይገባል፡፡ በዋናነት ግን ጥላቻ እንዳይዘራ ጥንቃቄ ማድረጉ ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባል፡፡

**ግዮን፡- እንዲህ ዓይነት የጥላቻ ንግግሮችን ግለሰቦቹ በየሚዲያዎቹ እየተገኙ ለማስተጋባታቸው መዋቅሩ፣ አደረጃጀቱ፣ ሕገ መንግሥቱ በአጠቃላይ አሁን ኢትዮጵያ**



**ላይ ገቢራዊ ሆነው የምናቸው ነገሮች ጠቅመዋቸዋል ይባላል፡፡ ስለዚህ የተሳሳቱ ትርክቶቹን ለማስቆምና ቤተክርስቲያንም እንደ ተቋም ለመታገልና ህልውናዋን ለማስጠበቅ ከመንግሥት ጥገኝነት የተላቀቀ ሥራ መሥራት አለባት የሚሉ ድምጾች ይሰማሉ? ምን አስተያየት አለዎት?**

*መምህር ምህረትአብ፡-* እንግዲህ የእግዚአብሔር ድርሻ አለ፣ የሰው ድርሻ አለ፡፡ "ቀኝህን ሲመቱህ ግራህን ስጥ" የሚለው ለመቼ ነው የሚሠራው? "አንድ ምዕራፍ ትሄድ ዘንድ ላስገደደህ ኹለተኛ ምዕራፍ ጨምረህ ሂድለት" የሚለውስ ለመቼ ነው? የሚለውን መረዳት ይገባል፡፡

አሁን በችግር ውስጥ አይደለም ያለነው፤ ልክ ክርስትና ከባርነት እንደጀመረበት ሥርዓት ማለቴ ነው፡፡ በዛ ዘመን የሮም ቤተመንግሥት ባዛንታይን ለመድረስ 400 ዓመት ፈጅቶበታል፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ ግን ከነገሥታቱ ስለጀመረ ብዙ ሰማዕትነት፣ ብዙ መገደልና ደም መፍሰስ አልነበረም፡፡ ከታች ሲጀምር ወደ ላይ ለመሄድ ይከብዳል፤ ከላይ ሲጀምር ግን ወደታች ለመውረድ ብዙ ይቸግራል፡፡ ነገሥታቱ ሁሉ ሃይማኖት ያላቸውና ፈሪሃ እግዚአብሔር የነበራቸው ስለነበሩ ኢትዮጵያ ውስጥ ክርስትናን ለመቀበል እንደሌላው ዓለም ብዙ ደም አልፈሰሰም፡፡

አሁን ግን ቤተክርስቲያኒቱ ላይ በሚደርሰው ሁሉ ቸልተኝነትና ዝምተኝነት ከበላይ አካላት እንመለከታለን፡፡ ከባርነት የጀመረው የጥንታዊ ሮማውያን መከራ፣ አስሩ የሮማ ቄሳሮች በክርስቲያኖች ላይ ያደረጉት የጅምላ ጭፍጨፋና ክር ማሰር ወንጀል የሆነበት "የክርስቶስ ነኝ" ማለት ኩነኔ በመሆኑም በምድር ወይም በካታካምፖ ውስጥ እየተደበቁ ክርስትናን ያስፋፉ ነበር፡፡ በግሪከኛ "ኢህቱል" (ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር) የሚል ትርጉም ስለሚሰጥ በመስቀል ፈንታ የዓሳ ምልክት ያደርጉ ነበር፡፡ ግን ክርስቲያኖቹ በዓሳው ምልክት ይግባቡ ነበር፡፡ እስከ መስከሚያኖስ መውደቅ እስከ ቆስጠንጢኖስ መነሳት አራተኛው መቶ ክ/ዘመን ድረስ በዚህ ሥቃይ ውስጥ ያለፉት ከላይ(ከመንግሥት) ጫና ስለነበረ ነው፡፡

ከላይ ስትደገፍ በነፃነት ታመልካለህ፡፡ ከላይ ጀምሮ ግን ወሳኝ ቦታዎች ላይ ያሉት "ፀረ ክርስቲያን ፀረ ኦርቶዶክሶች" ከሆኑ ቤተ ክርስቲያን ማድረግ ያለባት ነገር አለ፡፡ "እኔ ኖሬ ሌላው አይኖረው ፤ በሌላው ሬሳ ላይ ቆሜ ዕድሜዬ ይርዘም" ማለት ፍትሓዊ አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ፀሐይን ሲያወጣ ለሁሉም ነው፤ ምንም ያምልክ ምን፡፡ እግዚአብሔር ባኖረው ላይ አንተ ፈፅሞ መፍረድ አትችልም፡፡ አንተ ያመንከውን ይዘህ መከተል ብቻ ነው ያለብህ ፤ የሚፈርደው እርሱ ነው፡፡

እግዚአብሔር የነፃነት አምላክ ነው እንጂ በኃይል ቢሆን ሁሉን በአንድ ቀን ያመጣው ነበር፡፡ ማንኛውም ሰው የፈለገውን ይከተል ሌላው መንካት ግን የለበትም፡፡ አንድ ሰው የራሱን እምነት እንድከተል ሰብኮ ካሰመነኝ እከተለዋለሁ፣ እኔም ካሰመንኩት ይምጣ፡፡ ይሄ አካሄድ ይፈቀዳል፡፡ ከዛ ውጪ "ባያሳምንህም እኔ ያመንኩትን ማመን አለብህ" ብሎ ማስገደድ ግን አይቻልም፡፡ አሁን እየሆነ ያለው ይኼ ነው፡፡

**ግዮን፡- ይሄን "እምነትን በኃይል የማስቀየር" ድርጊትና እንቅስቃሴን በተመለከተ ለአንባቢያን በዝርዝር ሊገልፁልን ይችላሉ?**

*መምህር ምህረትአብ፡-* መልካም፡፡ አሁን በቅርብ ጊዜ ውስጥ ባሌ አካባቢ ምዕመኑን በኃይል ክር እንዲፈታ የተገደዱበትን ሁኔታ ብዙዎቻችን በቪዲዮ ተመልክተናል፡፡ ክርስቲያኖችን በሰይፍና ገጀራ እያስፈራሩ ማተብህን አውልቅ የሚባልበት ጊዜ ላይ ደርሰናል፡፡ በተባለው አካባቢ ሰዎችን አሰልፈው ኃይልን በመጠቀም እምነት የማስለወጥ ዘመቻ ሲደረግ ታይቷል፡፡

"ማተብህን አውልቅ" ማለት እግዚአብሔር የሰጠህን ነፃነት መቀማትና መግፈፍ ማለት ነው፡፡ ከነውርነቱ ባሻገር ወንጀልም ነው፡፡ እኔ ያመንኩትን ካላመንክ ብሎ ሰውን ለመግደል መነሳት፣ ከአካባቢው ማሰደድ ተገቢ አይደለም፡፡ ነገሮች ወደ እዚህ አቅጣጫ ሲመጡ መጀመሪያ "በሕግ አምላክ" ነው የምትለው፡፡ "ኑሩበት" ብሎ እግዚአብሔር በሰጠን ምድር ላይ እንዳንኖር እያደረጉን ነው ብለን በቅድሚያ ወደ መንግሥት ወደ ሕግ መጮህ ነው ያለብን፡፡

መንግሥት ታዲያ እኛ ስንገደል፣ ቤተክርስቲያን ስትቃጠል ዝም ብሎ የሚያይ ከሆነ የበደሉ ሰዎች ለፍርድ ቀርበው ፍትሕ የማያገኙ ከሆነ ቤተክርስቲያኒቱ ዝም ብላ የምትነድበት፣ 40 እና 50 የተማረው መሪ ጌታ ብዙ ተማሪ መፍራት እየቻለ ሲገደል ቆመን የምናይበት፣ ከ600 እና 700 ፍየል ቆዳ አባቶቻችን ብራና ወጥረው፣ ቀለም በጥብጠው የፃፏቸውና የቱሪስት መስህብ ሳይቀር የሆኑ መጽሓፍቶቻችን ሲወድሙ፣ ጽላቶች ሲዘረፉና ታሪኳ ሲጠፋ ቁጭ ብለን የምናይበት ምንም ምክንያት ሊኖረን አይችልም፡፡

ቅርብ ጊዜ አንድ ሊቀጳጳስ ከመድኃኒዓለም ቤ/ክርስቲያን ሲወጡ አንዲት ልጅ "ጫማዬን ሦስት ቀን ሳላደርገው ሰረቁብኝ፤ እንዴት ጫማዬ ይሰረቃል? ሃይማኖቴን ነው የምቀይረው" በማለት እያለቀሰች ስትነግራቸው "ተረጋጊ እንደው ብሎ ብሎ መድኃኒዓለም የአንቺን ጫማ ይጠብቅ? መድኃኔዓለም አንቺን ይጠብቃል፤ አንቺ ደግሞ ጫማሽን ጠብቂ" የሚል ምክር ለገሷት፡፡ ምን ማለቴ ነው የሰው ድርሻ አለ፣ የእግዚአብሔር ድርሻ አለ፡፡ እኛ ወደ ችግር ስንሄድ እግዚአብሔር አይጠብቀንም፤ ችግር ወደ እኛ ሲመጣ ግን እግዚአብሔር ይጠብቀናል፡፡ አንድ ሾፌር ሰክሮ እያሽከረከረ "እግዚአብሔር ይጠብቀኛል" ማለት አይችልም፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር

ለፈጠረው ማንነት ክብረት አልሰጠምና።

ጣልያን ስትመጣ እኮ የዘመትነው ለህልውናችንና ለማንነታችን ነው። ዛሬም ቤተክርስቲያናችን ህልውናዋና ማንነቷ ሲነካ ከላይ እስከ ታች ራሷን ማስከበር ይጠበቅባታል። ይሄ "ቀይ መስመር ነው፤ ቤተክርስቲያን እንዳታቃጥሉ፣ ምዕመናን አትንኩ፣ እግዚአብሔር የሰጠንን መብት አትውሰዱብንም" ማለት ያስፈልጋል። ታስረህ፣ ተገድደህና ምንም ነገር ማድረግ በማትችልበት አስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ እምነትህን ካድ ስትባል አልክድም ማለት ደግሞ ሰማዕትነት ነው።

ግን የመጀመሪያው አማራጭ እያለና የቤተክርስቲያንን መብት ማስከበር እየተቻለ ዝም ብለው ሲጫወቱበት ማየት ተገቢ አይደለም። ቤተክርስቲያን የማንንም አትነካም፣ የእርሷን መብት ማስከበርና ማስጠበቅ የሚኖርበት ጊዜ ላይ ነን። እዚህ ጋር ክርስቲያኖች አብረን መፀለይ መቻል አለብን። ወደ እግዚአብሔር እንከሳለን፤ ከእርሱም መልስና ፍርድ እንጠብቃለን፣ ከመንግሥት ደግሞ ፍትህን እንፈልጋለን። ቤተክርስቲያን በፀሎት በሱባዔ እንባ እያነባች ነው፤ 'ርግጠኛ ነኝ እግዚአብሔር መልስ ይሰጣል።

**ግዮን፡- ጥቂት ግለሰቦች "የኦሮሚያ ቤተ ክህነትን እናደራጃለን" የሚሉትን እንቅስቃሴ እንዴት ይመለከቱታል?**

መምህር ምህረትአብ፡- ሁላችንንም የሚያሳምነንና የሚያግባባን ቤተክርስቲያን ደቡብ ላይ ሄዳ ሰው አማርኛ ወይም ግዕዝ ካልሰማ፤ በማይሰማውና በማይገባው ቋንቋ ቆሞ ይገልገል የሚል አቋም የለኝም እኔ። ቤተክርስቲያን በወላይትኛ የሰለጠነ ካህን (የሚሰብክ፣ የሚቀድስ) አቁማ እነዛ ምዕመኖቿ አገልግሎት እንዲያገኙና እንዲድኑ ማድረግ መቻል አለበት።

በኦሮሚያ ክልል አማርኛ የማይሰሙና ኦሮምኛ ብቻ የሚነገሩ ካሉ የካህናት ማሰልጠኛ ከፍታና አገልጋዮችን መልምላ በኦሮምኛ ቋንቋ አሰልጥና ሄደው እንዲያስተምሩ ፤ እንዲሰብኩ ፤ እንዲቀድሱ ማድረግ አለባት። በትግርኛ የሚቀድስ ካህን አሰልጥኖ የትግራይ ሕዝብ እንዲጠቀም ማድረግ ወንጀል አይደል። ቋንቋ እንደአጠቃላይ ዓላማን ማስፋፊያ እንጂ መጣያ አይደለም። ክርስቶስ እስከ 72 ቋንቋ ለሐዋርያት ገልጾላቸዋል፤ ቋንቋዎቹን ወንጌል እንዲያስፋፉበት ነው የሰጣቸው። የቋንቋ መብዛት መለያያ አይሆንም። የባቢሎን ሰዎች በሙሉ አንድ ቋንቋ ቢናገሩም እግዚአብሔርን አሳዝነዋል፣ በድለዋል። ሐዋርያት ሁለት ላይ ስትመጣ ደግሞ በ72 (በብዙ) ቋንቋ እግዚአብሔርን አስደስተዋል፣ አምላክን አመስግነዋል።

ትልቁ ቋንቋ በሰማይም በምድርም የታወቀው፣ ሁሉም ሰው የሚናገረውና ዓለምን የሚያግባባው "ፍቅር" ነው። ሠው ትልቁን ፍቅር ከጣለ ትንሹ ቋንቋ ያጣላዋል። እኛ ያጣነው ፍቅር ነው፣ ምናልባት የቋንቋ አንድነት የሚጠቅመን የምንጠላውንና "የእገሌ ብሔር" የምንለውን እስክንገልና እስክናጠፋ ነው። ያንን ካጠፋን እና ሐሳባችንን ካሳካን በኋላ እንደገና እርስበርሳችን መጣላት እንጀምራለን።

"በቋንቋዬ ልማር፣ ልቀድስ፣ ልስበክ" ማለት ሰው ሳይሆን እግዚአብሔር የሠጠህ መብት ነው። ነገር ግን ቋንቋን ሽፋን በማድረግ "ይሄንን ክልል ገንጥዬ እወጣለኹ" ማለት አንዷት ቤተክርስቲያንን መከፋፈልና የመንፈስ ቅዱስን ሐሳብ መቃወም ነው። እንዲህ ዓይነቱ አካሄድ በፍፁም ትክክል አይደለም። ያለውን የአሰራር ክፍተት አርማ ቤተክርስቲያን በዚህ ጉዳይ ላይ በከፍተኛ ሁኔታ መዝመት አለበት።

ከዚህ ውጭ "የኦሮሚያ ቤተ ክህነት አቋቁማለኹ" ማለት ወይም ቤተክርስቲያንን መክፈል አይቻልም። ነገ ደግሞ ይሄን አይቶ አንዱ የደቡብ፣ ሌላው የአማራ "ቤተክህነት አቋቁማለሁ" በማለት ቤተክርስቲያንን ለመበጣጠስ ሙከራ ማድረጉ አይቀርም። ቤተክርስቲያን ስትከፋፈል ደግሞ አገር ትከፋፈላለች ትጠፋለች። "ኦርቶዶክስ አገር ናት" የሚባለው እኮ ዝም ብሎ አይደለም። ለምሳሌ አቡነ ሚካኤል ከጎንደር ተነስተው ኢሉባቦር ሄደው፣ ኪያምቤ ተራራ ላይ ተይዘው በጣልያን ዘመን የሞቱት "አገሬና መሬቴ ሁሉ የእኔ ነው" በማለታቸው ነው።

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን የሚያውቃት እንደ ኢትዮጵያዊነቷ ነው። ሐዋርያት 8 ላይ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ተጠመቀ እንጂ አማራው ጃንደረባ ወይም ጉራጌው ጃንደረባ ተጠመቀ አይይልም። ትልቁ መጽሐፍ ቅዱስ እንኳ በብሔር ከፋፍሎ ያልጠራንን ከየት አምጥተን ነው? ዛሬ "የኦሮሞ ቤተክህነት" ምናምን እያልን ከፋፍለን ልንመሰርት የምንፈልገው። እግዚአብሔር ኢትዮጵያን የሚያውቃት እንደ ኢትዮጵያ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ "እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች" የተባለች ሀገር በተነገረላት ትንቢትና በተቀመጠችበት ቦታ ሳትገኝ ስትቀር ይኼ ሞት ነው፤ ውርደት ነው።

ሁላችንም ማወቅ ያለብን ከአንድነት ኪሳራ ከመለየት ትርፍ እንደሌለ ነው። አንድ ማለት የሚሊዮኖች መነሻ ነው፤ መነሻችን ምንም ይሁን መድረሻችን ግን አንድነት መሆን አለበት። ስለዚህ "እንፈርሳለን ፤ እንበታተናለን" የሚል መፈክር ቀርቶ "አንድ ነን" እንኳ ለማለት ፈርተንና ተጠንቅቀን ነው መሆን ያለበት። ስስት ስለሆነ ማለቴ ነው። በንጉሡ ጊዜ አንድ ኢትዮጵያዊ ወደ ውጭ ሲሄድ "ኢትዮጵያዊ መጣ" በሚል ሁሉም ሰው ይጨነቅ ነበር። እርስ በርስ መገዳደልና መለያየት ከጀመርን በኋላ ዛሬ ስንሄድ ግን የተናቅን ሕዝቦች ሆንን። ወደ እኛም የሚመጣ የለም፣ ብንሄድም ደግሞ የሚያከብረን የለም። ለሁሉም ነገር አንድነት ያስፈልጋል።

አሁን ትልቁ ችግር በአንድነት የማያምኑ ጥቂት ሰዎች ተነስተው ስለአንድነት ይናገራሉ፤ እነሱ ይፈራሉ። ስለአንድነት የሚያምኑ ብዙ ሰዎች ደግሞ አይናገሩም። ስለዚህ ይህቺ አገር እየተጎዳች ያለችው በሀሰተኞች ንግግር ብቻ ሳይሆን እውነትን በያዙ ሰዎች ዝምታም ጭምር ነው።

**ግዮን፡- በቅርቡ በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት "የማንቂያ ደወል" የስብከት መርሃ ግብር አዘጋጅታችሁ ለማከናወን ስትንቀሳቀሱ (በተለይም እርሶ) ፖሊሶች ለማስተጓጓል ሞክረዋል የሚባል ነገር በማኅበራዊ ሚዲያዎች ተገልጿል? እስኪ የነበረውን ሁኔታ በዝርዝር ቢነግሩን?**

መምህር ምህረትአብ፡- እኛ እየተገፋች ያለችውን ቤተክርስቲያን፤ እየተገደለ ያለውን ምዕመን ነው በትምህርት እያፅናናን ያለነው። ሕዝበ ክርስቲያኑ ተገደለ እንጂ ሄዶ አልገደለም፤ እኔም ፖለቲካ ፓርቲ አቋቁሜ "እከሌ ይውረድ እከሌ ይውጣ" አላልኩም። የፀናው ለእምነቱ ነው። በሚያለቅሰበት፣ በሚፅናናበት በሰማዕቱ ቤት እንጂ ሌላ ቦታ አይደለም የተገኘሁት። እንደዛም ሆኖ ይሄ ህዝብ የሞቱትን ሰማዕታት ያለ ፖሊስ የቀበረ ጨዋ ሆኖ በደሉን ለእግዚአብሔር ሰጥቶ እየዘመረ የገባ ሕዝብ ነው።

"ለምን ተሰብስበህ አመለክ"፤ "ለምን ተሰብስበህ ዘመርክ"፤ "ለምን የሞቱትን አነሳህ" ማለት አይቻልም። ሞተንም፣ ስም አትጥሩ ተብለንም ይሆናል እንዴ? ይሄ ወንጀል አይደለም መብታችንን ነው የተጠቀምነው። ከዛ ውጭ በስብከት ውስጥ ፖሊስ ጣልቃ ገብቶ "ይሄን ስበኩ ያንን ተው" ማለት አይችልም። ቤተክርስቲያን የራሷ ሕግ አላት፣ ያንን ጠብቀን ነው የምናገለግለው። የፀጥታ አካላት ሌላ ፍላጎት ሊኖራቸው ይችላል። እኔ ግን ሁሌም የቤተክርስቲያኒቱን ሕግና ሥርዓት ጠብቄ ነው የምጓዘው። ምንም ይሁን ምን ይህቺ ቤተክርስቲያን የተጋረጠባትን ፈተና ከመናገር፣ ወንጌልን በዓውደ ምህረቶች ከመስበክ፣ ሕዝብን ከማንቃት ወደ ኋላ አልልም።

**ግዮን፡- ሰኞ የካቲት 9 ቀን በተጀመረው የቅዱስ ሲኖዶስ ጉባዔ ላይ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ በእርሶ ላይ የፀጥታ ኃይሎች የሚያደርሱትን ወከባ አስመልክቶ "ልጆቼን አትንኩ" የሚል መልዕክት አስተላልፈው ነበር። ምን ተሰማህ?**

መምህር ምህረትአብ፡- ጥሩ ነው። አባቶቻችን የሕዝብ እረኞች ናቸው። ከላይ ከአባቶች ዘንድ ያለውን ቁርጠኝነት ስታይ ትበረታለህ። የማስተማር ፍቃዱን ሙሉ ሰጥቶ፣ አስተምሮ፣ አስመርቆ ወደ ዓለም የሰደደን ቅዱስ ሲኖዶስ ነው። ይሄን በእምነት የጀመርነውን አደራ በፅናት ነው የምንጨርሰው። የእግዚአብሔር ሀሳብ ሩቅ አይተው ቅርብ ላይ ለሚመለሱ ሳይሆን መጥተው እስከመጨረሻው ለሚጓዙ ነው። ማርቲን ሉተር ኪንግ ራሱ "የሚሞትለት ዓላማ የሌለው ሰው ለመኖር ብቁ አይደለም" ብሏል።

ሃይማኖት የምንሞትለት ነው። ለመኖር አይደለም ለመሞትም ጨክነናል። ቅዱስ ሲኖዶስ የሆነውን ድርጊት በይፋ ማውገዙ የበለጠ አበርትቶናል፣ የበለጠ እንድንጀግን አድርጎናል። የዛሬ ስምንትና ዘጠኝ ዓመት አከባቢ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ችግር ሲፈጠር መልስ የሰጠንበት ሁኔታ ነበር። ያኔ የመንግሥት አካላት ቅዱስ ሲኖዶሱ ጋር መጥተው "እከሌ እከሌ" የሚባሉ ሰዎችን አሳልፋችሁ ስጡን ብለው የእኔን ስም ጠቅሰው ጠይቀው ነበር።

ያኔ አባቶች ያሉት "መጀመሪያ መውሰዱን ከእኛ ጀምሩ። የማስተማር ፍቃዱን የሰጠናቸው እኛ ነን" ብለው ነበር የመለሷቸው። ያን ጊዜ አባቶች "ኃላፊነቱን እኛ አንወስድም፣ በራሱ ጊዜ ነው ይሄን ያደረገው" ቢሉ የእኔ ልብ ብቻ ሳይሆን የብዙሃን ልብ ይሰበር ነበር። አባቶች የቆምነው ለቤተክርስቲያን የምናስፈፅመው የቤተክርስቲያንንና የቅዱስ ሲኖዶስን ዓላማ መሆኑን ተረድተው አሁንም ወጥ አቋም ይዘው መልዕክት ማስተላለፋቸው ከዚህ የበለጠ እንድንሄድ ያደርገናል።

**ግዮን፡- እናመሰግናለን።**

ምልከታ

# የጋራ እና የተናጠል ሉዓላዊ መብቶች



መታሰቢያ መልአከህይወት

አንድ አገር ዘለቄታ ወዳለው ብልጽግና እና ሥልጣኔ ለመሸጋገር ግድ የራስዋን ሉዓላዊ መብት ላይ ብቻ ሳይሆን አትኩራ መስራት ያለባት የሌሎችን ሉዓላዊ መብትና የጋራ ሉዓላዊ ናቸው ተብለው የሚታመኑ መብቶችንም ጭምር ነው፡፡

ለምሣሌ የዓባይ ወንዝን የመጠቀም መብትን በእኔ እይታ እንደ የጋራ ሉዓላዊ መብት መታየት አለበት፡፡ በተለይ ግብፆች ዓባይ ግድብ ላይ እንኳን ግዙፍ ግድብ ተገድቦ ምንም ነገር ባይሰራ እንኳን መባነናቸው አይቀርም፡፡ እኛ ደግሞ ግብፆች በዓባይ ግድብ ላይ አንድ ነገር በተባለ ቁጥር በጣም የሚያሳስባቸው አንድ ለናቱ የሆነ ወንዛቸው መሆኑን መገንዘብ አለብን፡፡

ኢትዮጵያ የዓባይ ቁልፍ ባለቤት መሆንዋ ብቻ ሳይሆን ግብጽ በማንኛውም የፖለቲካ መድረክ የኢትዮጵያን ፖሊሲ ለመከተል ትገደዳለች፡፡ እስከ አሁን ባለው ሁኔታ ግብጽ የመካከለኛውን ምስራቅ ፖሊሲ የስበት ማዕከል ተደርጋ ትወሰድ ነበር፤ አሁን ይህ ሁኔታ በተወሰነ መልኩ ቀስ በቀስ ወደ ኢትዮጵያ መንሸራተቱ አይቀርም፡፡

አንዳንድ የመንግስት ባለስልጣናት ግብጽ ዓባይ ሲሞላ በቦታው በመገኘት መታዘብ እንደምትፈልግ ያቀረበችውን ጥያቄ “ሉዓላዊነትን ይጋፋል” በማለት ውድቅ እንዳደረጉት ሠምቻለሁ፡፡ ይህ አስተሳሰብ በፍፁም የተሳሳተ ነው፡፡ ዓባይ ወንዝ የጋራ ሉዓላዊ መብታችን በመሆኑ ግልጽነት በተሞላው መንገድ እየተግባባን ብንጠቀምበት ለሁላችንም ይበጃል እንጂ እስቲ አስቡት ግብፆች ጦርነት እንግጠም ቢሉና ጦርነት ቢነሳ ማን ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

እኔ ጠቅላይ ሚኒስትር ብሆን ግብፆች እነሱን ለመጉዳት ምንም ሀሳብ እንደሌለን ለማሳመን እዚያው ግድቡ ጋር ቆንስላ ጽሕፈት ቤት እንዲከፍቱ እፈቅዳላቸው ነበር፡፡ ባይሆን ግብፆች ማድረግ ያለባቸው ኢትዮጵያ ውስጥ የዓባይ ተፋሰስን ለመንከባከብ የሚወጣውን ወጪ የድርሻቸውን እንዲያዋጡ መጠየቁ በብዙ መልኩ ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም ዓባይን እንደ እድር ላም እንየውና የእድር ላምን ዕድርተኞቹ ተሰብስበው ወተቷን ብቻ ሳይሆን ማለብ ያለባቸው የላሚቷን ጤንነት፣ ምግብ፣ ጽዳት በጋራ የመፈፀም ኃላፊነትም አለባቸው፡፡

እኔ በግሌ አሁን እየተገነባ ባለው የአባይ ግድብ ተፋሰስ ወይም “The Blue Nile System” ወይም “The Blue Nile Basin” ተብሎ የሚታወቀው የመሬት አካል በጣም የሚያሳስበኝ ጉዳይ የተፋሰሱ የመሬት አካሎች የተፈጥሮ ሚዛን ክፉኛ መናጋቱ ነው፡፡ አልፎ አልፎ የበጋው ወቅት እየተራዘመ በሚሄድበት ጊዜ የግድቡ አስተዳዳሪዎች ኃይል ማመንጨት የማይችሉበት ደረጃ ላይ ሲደርሱ ከስር ያለውን የውሃ ማስተንፈሻ ወይም “Bottom outlet” (ውሃ ወደ ሱዳን የግድ መሄድ ስላለበት) ሊከፍቱት የሚገደዱበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡ ከስር ያለው የውሃ ማስተንፈሻ ወይም “Bottom outlet” ውሃ እንዲወጣ በሚደረግበት ጊዜ የውሃው የተፈጥሮ ፍሰቱ እንዳይቋረጥ ተብሎ የሚለቀቅ በመሆኑ ምንም ዓይነት ኃይል ሳያመነጭ ውሃ ባከነ ማለት ነው፡፡ በተጨማሪ ከስር ያለው ማስተንፈሻ በሚከፈትበት ወቅት መጠኑ ከፍተኛ ውሃ ከግድቡ ስለሚወጣ ክረምቱ እስኪመጣ ድረስ ግድቡ የሚይዘው የውሃ መጠን በከፍተኛ ደረጃ ስለሚወርድ ያንን ውሃ ለመተካት ሌላ አስቸጋሪ ሁኔታ ተፈጠረ ማለት ነው፡፡ በኔ እምነት ዓባይን የመሙላት ድርድር ዘላለማዊ ሆኖ የሚቀጥል ይመስለኛል፡፡ የግድቡ ውሃ መጠን በጣም የሚቀንስበት አንዱ ጉዳይ ደግሞ በተራዘመ የበጋ ወቅት ምክንያት በሚፈጠር ትነት ነው፡፡

ዓባይ እንደ ኮንጎ ወንዝ ዓይነት ከፍተኛ የውሃ መጠን ያለው ወንዝ ቢሆን ኖሮ ይህ ችግር አይኖርም ነበር፡፡ ምክንያቱም የኮንጎ ተፋሰስ አልፎ አልፎ ዓመቱን ሙሉ ዝናብ የሚያገኝበት ዓመታት አሉ ፤ የተፋሰሱ የውሃ መጠን በዓባይ ከሚያልፈው ውሃ በአስራ አራት እጥፍ ይበልጣል፡፡

የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ አንድ ስጋት አለኝ፡፡ ዓባይ ተገድቦ አልቆ ውሃ ከሞላ በኋላ የውሃው ከፍታ ከባህር ወለል በላይ ስድስት መቶ ሜትር ገደማ ይደርሳል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ ከ600 መቶ ሜትር በታች የሆኑ ተፋሰሶች አሉ፡፡ ታዲያ ዓባይ ግድብ ውስጥ የተራቀመው ውሃ ሾልኮ ምድር ውስጥ ሊኖር በሚችል ዋሻ አልፎ ወደ ሌላ ተፋሰስ ውሃ ቢባክንስ ??? በሌላ አነጋገር “underground river” ቢፈጠርስ?

ሌላው የዓባይ ተፋሰስን የተጎሳቆለ የተፈጥሮ መልክአምድር መልሶ እንዲያገግም ማድረግ ምናልባትም ዓባይን ለመገደብ ከወጣው ወጪ በላይ የሚጠይቅ ይመስለኛል፡፡ የዓባይ ተፋሰስ እንዲያገግም ካልተደረገ የዓባይ ግድብ ልክ እንደ ተከዜ ግድብ ኃይል ለማመንጫነት ሳይሆን ለውሃ ማቆር ፕሮግራም እንዳይሆን ያሰጋል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው በተራዘመ የበጋ ወቅት ምክንያት ኢትዮጵያ ኃይል ሳታመነጭ በስረኛው የግድቡ የውሃ ማስተንፈሻ ለረጅም ጊዜ ብዙ የውሃ መጠን የሚለቀቅ ከሆነ የዓባይ ግድብ የግብፆች የውሃ ባንክ ሆነ ማለት ነው፡፡

በአንድ ወቅት የተባበሩት መንግሥታት ባወጣው ጥናት ላይ ለማየት እንደቻልኩት አሁን በዓለማችን እጅግ አሳሳቢ የሆነው የከባቢ አየር ሙቀት የመጨመሩ ምክንያት፣ በኢትዮጵያ የክረምት ወቅት የውቅያኖስ ጠለል በተወሰነ ደረጃ ሙቀት የሚጨምር በመሆኑ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣው እርጥበት ያዘለ ንፋስ የሚይዘው የእርጥበት መጠን እስከ 20 % የሚጨምር ሲሆን ይህ ለብዙ ሜዳማ አገሮች መቅሰፍት ሲሆን ለኢትዮጵያ ግን እንደ በረከት ሊቆጠር ይችላል፡፡ ምክንያቱም አሁን የሰራናቸውና ወደፊት የምንሰራቸው ግድቦች የሚያገኙት የውሃ መጠን በዚያው ልክ የሚጨምር በመሆኑ ነው፡፡

ብዙ ሰዎች ከቤታቸው በላይ የውሃ ማጠራቀሚያ ታንከር ሰቅለው ውሃ እንዲጠራቀም ያደርጉና ያ የተጠራቀመው ውሃ ወደታች እየወረደ ለቤተሰቡ አባላት ጥቅም ይሰጣል፡፡ ዓባይ ግድብ ጀርባ የሚጠራቀመው ውሃም ከፍታው ከባህር ወለል በላይ ወደ ስደስት መቶ ሜትር ከፍታ ላይ ያለ በመሆኑ ለግብፆች ልክ እንደ ውሃ ታንከር ውሃ ይዞ ወደ እነሱ እንደሚለቀቅላቸው ያውቃሉ፡፡ በተጨማሪ በክረምት ወቅት ወደ ሱዳን እየሄደ ችግር የሚፈጥረው ጎርፍ ተጠራቅሞ፣ ግድቡ ውስጥ ቆይቶ በበጋ ወቅት ስለሚለቀቅላቸው በእጅጉ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ያውቃሉ፡፡ እነሱ እንደ ችግር የሚያዩት የውሃውን አለቃቀቅ የምትቆጣጠረው ኢትዮጵያ መሆንዋን ነው፡፡

ሰሞኑን ከቤተመንግሥት ባለስልጣናት እንደሰማሁት ኢትዮጵያ በምንም መልኩ ኃይል ስታመነጭ ውሃ ወደ ሱዳን እንደማትልክ ሲሆን ይህ አባባል ልክ ይሆናል ለማለት ያስቸግራል፡፡ ውሃ ኃይል ሳያመነጭባቸው የሚለቀቅባቸው ሁለት መንገዶች አሉ፡፡

አንደኛው ከፍተኛ መጠን ያለው ውሃ ወደ ግድቡ የሚገባ ከሆነና ግድቡ ውሃውን መያዝ የማይችልበት ደረጃ ላይ ሲደርስ በግድቡ ጎን በኩል የተሰራ የውሃ ማስተንፈሻ ወይም (spill way) ውሃ ኃይል ሳያመነጭ እንዲፈስ ይደረጋል፡፡

ኹለተኛ ከፍተኛ የውሃ እጥረት ሲፈጠርና ወደ ተርባይኖች ውሃ መግባት ሲያቅተው ከግድቡ የግድ ውሃ በተወሰነ መልኩ ዓመቱን ሙሉ መውጣት ስላለበት ከግድቡ የታችኛው ክፍል የተሰራው ማስተንፈሻ ወይም (Bottom outlet) እንዲከፈት ይደረግና ውሃ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡ አሁንም በዚህ አካሄድ ምንም ዓይነት ኃይል ማመንጨት አይቻልም፡፡ ይህ ደግሞ የሚደረገው ዓለም አቀፍ ሕጎች የሚያዙ በመሆኑና በወንዙ የታችኛው ክፍል ያለን ብዝሃ ሕይወት ችግር እንዳይገጥመው በማሰብ ነው፡፡

እዚህ ላይ በጣም የሚያሳስበው የበጋው ወቅት እየተራዘመ ከሄደና ምናልባት ደግሞ ድርቅ የሚከተል ከሆነ ግድቡ የያዘውን ውሃ በከፍተኛ መጠን ሊያጣ የሚችል መሆኑ ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ በግሌ እንደ አንድ ችግር ነው የማየው፡፡

እንደ ቻይናው “ስሪ ጎርጀስ ዳም” ወይም እንደ ብራዚሉ “ኢታፑ” ግድብ በወንዙ መነሻ የሚቀልጥ የበረዶ ክምር በመኖሩና ብራዚል ውስጥ ደግሞ ጥቅጥቅ ካለው የአማዞን ደን ከፍተኛ ውሃ የሚገኝ በመሆኑ በዓባይ ግድብ ላይ ሊከሰት የሚችለው የውሃ እጥረት በእነዚህ አገሮች ብዙም አይስተዋልም፡፡ በመሆኑም ከላይ እንደተጠቀሰው በዓባይ ተፋሰስ እጅግ ከፍተኛ ተፈጥሮን የመንከባከብ ሥራ ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡

ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ የመሬት መንሸራተት ነው፡፡ ዓባይ ተገድቦ ውሃ ሲሞላ እስከ አሁን ውሃ ያልነካው የዓባይ ሸለቆ እና በውሃው መካከል የሚፈጠሩ ደሴቶች በቋሚነት ውሃ ጋር ግንኙነት ሲኖራቸው እየረጠቡ ወደ ጭቃነት ተለውጠው ሊናዱ ይችላሉ፡፡ በዚህን ጊዜ ከባድ ሱናሜ ይነሳል ፤ በእርግጠኝነት ኢንጅነሮቹ ይህንን ጉዳይ ከግምት ውስጥ እንዳስገቡት እምነት አለኝ፡፡ ደሴቶቹና ሸለቆው ድንጋያማ ከሆነ ግን ይህ ችግር አይኖርም፡፡

እኛ ኢትዮጵያውያን እንደ ዓባይ ግድብ ዓይነት ታሪካዊ ሥራ እና የብሔር ፖለቲካ አንድ ላይ ለማስኬድ እየሞከርን ራሳችንን አላስፈላጊ ውጥረት ውስጥ ባንከት መልካም ነው፡፡ የብሔር ፖለቲካን ሙሉ በሙሉ ከታች ላሉት ማህበረሰቦች ትተን ሙሉ ትኩረታችንን ልማት ላይ እና ከድህነት ጋር በሚደረግ ትግል ላይ ብናውለው በእርግጠኝነት ውጤታማ እንሆናለን፡፡

በመጨረሻም የዓባይ ግድብ በቂ ጥናት ተደርጎ በቂ ዝግጅት እና ገንዘብ ተመድቦ የተጀመረ ግድብ ሳይሆን የፖለቲካ ውሳኔ ሁላችንም እናውቀዋለን፡፡ መሆን የነበረበት ግን ሌሎች በአቅማችን ስር ያሉ ብዙ ገንዘብ የማያስወጡ ግድቦችን እየሰራን አቅም ከፈጠርን በኋላ ነበር ወደ ዓባይ ግድብ መዞር የነበረብን፡፡ በተጨማሪም የኤሌክትሮ ሜካኒክ ሥራውን ለመስራት ውል የተሰጠው ሜቴክ ከግብፆች ጋር ጤነኛ ያልሆነ ግንኙነት እንደነበረው መረጃው አለኝ፡፡ ዓባይ ግድቡ ሲገነባና ውሃ ሲሞላ ገና ብዙ ብዙ ፈተናዎች የሚኖሩት ግድብ ነው፡፡ አንዳንዴ ከአቅም በላይ የሆነን ስራ ለመስራት መሞከር ተንገዳግዶ መውደቅን ያስከትላል፡፡ በመሆኑም እንዲህ ዓይነት ውሳኔዎች ለፖለቲከኞች ወይም ለካድሬዎች ሳይሆን መተው ያለበት በሙያው ጥልቅ እውቀት ላላቸው ምሁራኖች ነው፡፡

# የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃ አዋጅ



ሳሙኤል ግርማ

ሀገራት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እያደገ የመጣውን የጥላቻ ንግግር እና የሀሰተኛ መረጃ ለመቆጣጠር በማሰብ ህጎችን ተግባራዊ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ያክል ቤልጂየም እ.ኤ.አ በ 1981 የጥላቻ ንግግርን ለመቆጣጠር ተግባራዊ ያደረገችው ህግ ጥፋተኞች እስከ አንድ አመት እስራት እና እስከ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ዩሮ እንደሚቀጡ ይደነግጋል፡ ፡ በፊንላንድም ቢሆን አጥፊዎች በገንዘብ ወይም እስከ አራት አመት በሚደርስ እስር ሊቀጡ እንደሚችሉ የፊንላንድ የወንጀል ህግ ቁጥር 11 ይደነግጋል ፡፡ ኢትዮጵያም ዘግይታም ቢሆን በ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አማካኝነት የካቲት 5 ቀን 2012 ዓ.ም. የጥላቻ ንግግርና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመቆጣጠር በማሰብ አስር አንቀፆች ያሉት አዋጅ አስተዋውቃንለች፡፡

እስቲ ይህ አዋጅ አላማ ብሎ የያዛቸው ነጥቦችን እንመልከት ፣ በቀዳሚነት አዋጁ ሰዎች ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብታቸውን ሲጠቀሙ ግጭት ወይም ሁከትን የሚቀሰቅስ ወይም ብሄርን፤ ሀይማኖትን፤ ዘርን፣ ጾታን ወይም አካል ጉዳተኝነትን መሰረት በማድረግ በግለሰብ ወይም በተለየ ቡድን ላይ ጥላቻ ወይም መድልዎ የሚያስፋፋ ንግግር ከማድረግ እንዲቆጠቡ ማድረግን ያልማል፡ ፡ በመቀጠልም ደግሞ መቻቻልን፣ የዜጎች ውይይትና ምክክርን፣ መከባበርና መግባባትን ማበረታታትና ዲሞክራሲያዊ ስርዐት ማጎልበትን ፤ አላማው አድርጎ አስቀምጧል፡፡ በ ሶስተኝነት አላማ አድርጎ ህጉ ያስቀመጠው ፡ የጥላቻ ንግግርን፣ የሃሰተኛ መረጃና ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች የውሸትና አሳሳች መረጃዎችን ስርጭትና መበራከትን ለመቆጣጠርና መግታት ነው፡፡

አዋጁ አንቀፅ 2 ስር የተለያዩ የቃላት ትርጉም ያስቀመጠ ሲሆን ፤ ከዚህ ውስጥ የጥላቻ ንግግር ማለት ምን እንደሆነ በግልፅ ደንግጓል፡፡ የጥላቻ ንግግር ማለት በአንድ ሰዉ ወይም የተወሰነ ቡድን ላይ ያነጣጠረ፣ ብሄርን፡ብሄረሰብንና ህዝብን፣ ሀይማኖትን፤ ዘርን፣ ጾታን ወይም አካል ጉዳተኝነትን መሰረት በማድረግ ጥላቻን፣ መድሎን ወይም ጥቃትን የሚያበረታታ ንግግር ነው፡፡ በተጨማሪም ሃስተኛ መረጃ ማለት ውሸት የሆነና የመረጃውን ውሸት መሆኑን በሚያውቅ፣ ወይም መረጃውን የሚያሰራጨው ሰው ካለበት አጠቃላይ ሁኔታ አንጻር የመረጃውን ሃሰተኝነት ሊያውቅ ይገባ ነበር የሚያስብል በቂ ምክንያት እያለ የሚሰራጭ ሁከት ወይም ግጭት የማስነሳት፣ ወይም ጥቃት እንዲደርስ የማድረግ እድሉ ከፍ ያለ ንግግር ነው፡፡ ንግግር” ማለት ደግሞ በቃል፣ በጽሑፍ፣ በምሥልና ሥዕል፣ በቅርጻ ቅርጽ እና በሌሎች ተመሳሳይ መንገዶች መልእክትን የማሰራጨት ተግባር እንደሆነ ከአዋጁ እንገነዘባለን ፡፡

በአጭሩ የጥላቻ ንግግርንና የሃሰት መረጃን በብሮድካስት፣ በህትመት ወይም በማህበራዊ ሚድያ በጽሁፍ፣ በምስል፣ በድምጽ ወይም በቪድዮ ማሰራጨት የተከለከለ ነው በማለት የአዋጁ አንቀፅ 4 እና 5 ይደነግጋሉ ፡ ፡ ብሮድካስት ማድረግ” ማለት በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን ሥርጭት ማድረግ ነዉ፡ ፡ ማህበራዊ ሚዲያ ማለት ሰዎች መልዕክት ለመለዋወጥ ፤ ትስስር ለማዳበር፤ ሀሳብ ለመጋራት የሚጠቀሙበት በኢንተርኔት አማካኝነት በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ ለሆኑ ሰዎች መረጃ የሚደርስበት፣ ወይም ማህበራዊ መስተጋብር የሚስተናገድበት መንገድ ነዉ፡ ፡ የህትመት ሚድያ” ማለት ለህዝብ ስርጭት የተዘጋጀ ማንኛውም የህትመት ወጤት ነው፡፡

ስለ የወንጀል ተጠያቂነት

ሰዎች ይህንን አዋጅ ተላልፈው ሲገኙ የሚጠብቃቸው የቅጣት አይነት እና መጠን በህጉ አንቀፅ 7 ስር ተደንግጎ እናገኘዋለን ፡ ፡ ማንኛውም ሰው የጥላቻ ንግግርን በብሮድካስት፣ በህትመት ወይም በማህበራዊ ሚድያ በጽሁፍ፣ በምስል፣ በድምጽ ወይም በቪድዮ ያሰራጨ እንደሆነ እስከ ሶስት አመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም ከብር 100,000 ያልበለጠ መቀጮ እንደሚቀጣ ህጉ ያስገነዝበናል፡፡ በተጨማሪም በጥላቻ ንግግሩ ምክንያት በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥቃት የተፈጸመ እንደሆነ ቅጣቱ እስከ አምስት አመት የሚደርስ ጽኑ እስራት እንደሚሆን ህጉ ያስቀምጣል፡፡

ሀሰተኛ መረጃን በተመለከተ ደግሞ ማንኛውም ሰው የሃሰት መረጃን በብሮድካስት፣ በህትመት ወይም በማህበራዊ ሚድያ በጽሁፍ፣ በምስል፣ በድምጽ ወይም በቪድዮ ያሰራጨ እንደሆነ እስከ አንድ አመት በሚደርስ በቀላል እስራት ወይም ከብር 50,000 ባልበለጠ መቀጮ ይቀጣል ሲል ህጉ ያስቀምጣል፡፡

የጥላቻ ንግግር ወይም የሃሰተኛ መረጃ ስርጭት ወንጀሉ የተፈጸመው ከአምስት ሺ በላይ ተከታይ ባለው የማህበራዊ ሚድያ ገጽ ከሆነ ወይም በብሮድካስት አገልግሎት ወይም በየጊዜው በሚወጣ የህትመት ውጤት ከሆነ ቅጣቱ አስከ ሶስት አመት የሚደርስ ቀላል እስራት ወይም ከብር 100,000 ያልበለጠ መቀጮ እንደሚሆን እና ሃሰተኛ መረጃ በመሰራጨቱ ምክንያት በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥቃት የተፈጸመ ወይም የተሞከረ ከሆነ፣ ሁከት ውይም ግጭት የተከሰተ እንደሆነ ቅጣቱ እስከ አምስት አመት ሊሚደርስ የሚችል ጽኑ እስራት ሊሆን ይችላል፡፡

## ልዩ ሁኔታ

አዋጁ ከላይ በተቀመጠው መልኩ የጥላቻ ንግግር እና የሀሰት መረጃን አስመልክቶ ክልከላዎችን እና ቅጣቶችን ያስቀመጠ ቢሆንም ፡ በ አንቀፅ 6 ስር ደግሞ በተቃራኒው አንድ ንግግር እንደ ጥላቻ ንግግር ወይም እንደ ሃሰት መረጃ ተወስዶ ማሰራጨት የማይከለከልባቸውን አጋጣሚዎች በዝርዝር አስቀምጧል፡፡ በመጀመሪያነት ያስቀመጠው የትምህርታዊ ወይም ሳይንሳዊ ምርምርን ሲሆን ፡ በትምህርታዊ ወይም ሳይንሳዊ ምርምር ስራ ጋር በተገናኘ ፡ የጥላቻ ንግግሩ ወይም የሀሰት መረጃው የዚሁ አካል ከሆነ ፡ ለትምህርታዊ ነፃነት ሲባል ፡ እንዲህ ያሉ ሆኔታዎች እንደማይከለከሉ ህጉ ያስገነዝበናል ፡፡ በሁለተኝነት ደግሞ የዜና ዘገባ፤ ትንታኔ ወይም የፖለቲካ ትችት አካል እንደሆነ፤ የጥላቻ ንግግሩ ወይም የሀሰት መረጃው ፡ ማሰራጨት እንደማይከለከል በግልፅ ተቀምጧል፡ ፡ በመቀጠልም የኪነጥበበ ፣ ትወና ወይም መሰል የስነጥበበ ውጤት እና የሃይማኖታ አስተምህሮት አካል እንደሆነ አንድ ንግግር እንደ ጥላቻ ንግግር ወይም እንደ ሃሰት መረጃ ተወስዶ ማሰራጨት እንደማይከለከል ህጉ በልዩ ሁኔታ ያስቀመጣቸው ሁኔታዎች ናቸው ፡፡

የተቋማትና የአገልግሎት ሰጪዎች ሀላፊነት

በመጨረሻም ህጉ ተቋማት ላይ እና አገልግሎት ሰጪዎች ላይ ሀላፊነት ያስቀምጣል፡ በመሆኑም ማንኛውም የማህበራዊ ሚዲያ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት የጥላቻ ንግግርና የሃሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመቆጣጠርና ለመግታት ጥረት ማድረግ እንዳለበትና ፡ የጥላቻ ንግግርን ወይም የሃሰተኛ መረጃ ስርጭትን የተመለከተ ጥቆማ ሲደርሰው በፍጥነት ይህን መሰል መልዕክቶችን ወይም ንግግሮችን ከአግልግሎት አውታሩ ሊያስወግድ እንደሚገባ ህጉ ያስገነዝባል ፡፡

## ማጠቃለያ

አሁን አሁን በሀገራችን እዚህም እዚያም አልፎ አልፎ እየተስተዋሉ የመጡትን ግጭቶች እና የሰላም መደፍረሶች በተዘዋዋሪም ቢሆን ከ ጥላቻ ንግግር እና ሀሰተኛ መረጃ ጋር ተያያዥነት እንዳላቸው ይታመናል ፡ ፡ በተለይም በሀገራችን ከእለት ወደ እለት የማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚው እየጨመረ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ ፡ ከማህበራዊ ሚዲያ የሚነሱትን የጥላቻ ንግግሮች እና የሀሰት መረጃዎችን ለመቆጣጠር አልማ አዋጅ ማፅደቋ የሚበረታታ ቢሆንም ፡ ህጉ ተግባራዊ በሚደረግበት ወቅት ፡ የ ዜጎች ሀሳብን በነፃነት የመያዝና የመግለፅ መብትን ያማከለ መሆን አለበት፡፡ ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሀሳቡን የመግለጽ ህገ መንግስታዊ ነፃነቱን በማያጣብብ መልኩ ይህ አዋጅ ቢተገበር መልካም ነው እላለሁ አመሰግናለሁ፡፡ ■

# ‹‹ጊዜውን ጠብቆ የኢትዮጵያዊ አንድነት ስሜት መጎልበቱ አይቀርም››

## አቶ ሙሉጌታ አረጋዊ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ፋኩልቲ መምህርና የሕግ ባለሙያ የሆኑት አቶ ሙሉጌታ አረጋዊ ተወልደው ያደጉት በትግራይ መቀሌ ነው፡፡ ለቤተሰቦቻቸው ሦስተኛ ልጅ የሆኑት አቶ ሙሉጌታ በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የፍልስፍና የ4ኛ ዓመት ተማሪ በነበሩበት ወቅት፤ "የወያኔ አባል ነህ" በሚል ደርግ አስሯቸው እንደነበር ይናገራሉ፡፡ የትግራይ ተወላጆችን በዚህ መንገድ ማሰር ደንብ በነበረበት ወቅት ስምንት ያህል ዓመታትን በማረሚያ ቤት እንደቆዩ የሚገልጹት አቶ ሙሉጌታ፣ ከእስር ሲወጡ ጀምረውት የነበረው የፍልስፍና ትምህርት ክፍል ተዘግቶ እንደጠበቃቸው ያስታውሳሉ፡፡

ከዛ በኋላ ፊታቸውን ወደ ሕግ ዓለም በማዞር በዘርፉ የመጀመርያ ዲግሪያቸውን ሲቀበሉ ችለዋል፡፡ እ.ኤ.አ በ1996 ወደ አሜሪካ አቅንተውም በተመሳሳይ ሙያ ማስተርሳቸውን ሠርተዋል፡፡ በአሜሪካን አገር የጥብቅና ፍቃድ በማውጣት በጠበቃነት ረዘም ላለ ጊዜ የሰሩት አቶ ሙሉጌታ ከስድስት ዓመት በፊት ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የሕግ ፋኩልቲ በመምህርነት እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡

በኢትዮጵያ ፖለቲካ ጉዳይ ዙሪያ በሚሰጧቸው በሳል አስተያየቶች፣ ባላቸው አገራዊ የአንድነት ስሜት የሚታወቁት መምህርና የሕግ ባለሙያ አቶ ሙሉጌታ አረጋዊን፣ በአገራችን አጠቃላይ የፖለቲካ ትኩሳትና ችግሮች እንዲሁም ተዛማጅ ጉዳዮች ዙሪያ ከግዮን ጋዜጠኞች ሮቤል ምትኩና ኄኖክ ገለታው ጋር ያደረጉት ቆይታ ኹለተኛ ክፍል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ መልካም ቆይታ!

**ግዮን፡- አንዳንድ የትግራይ ብሔርተኞችና አክቲቪቶች ከፀሀይ በታች መፈጠር ያለበት ነገር ሁሉ ተፈጥሮ የምስራቅ አፍሪካ ላንድስኬፕ መቀየር መቻል ይኖርበታል፡፡ ጥግ ድረስ ሄደን ኤርትራና ትግራይን በአዲሱ ትውልድ አጣምረን አገር የመመስረት ድረስ ጥረት ማድረግ አለብን ሲሉ ፍለላጎታቸውን ያስተጋባሉ፡፡ ይህን ነገር ሰምተውት ከሆነ የግል አስተያየትዎን ቢሰጡበት ?**

አቶ ሙሉጌታ፡- ትግራይ ውስጥም ሆነ ሌላው ክልል አሁን ብሔርተኝነት ጥግ ድረስ ሄዷል፡፡ በጣም አስፈሪ ገፅታ በብሔርተኝነት ዙሪያ እየታየ ነው፡፡ ለምሳሌ ትግራይ ውስጥ አሁን ላይ ስለኢትዮጵያ አንድነት መጠየቅ አትችልም፡፡ ከተማ ውስጥ አንድ ካፌ ወይም መዝናኛ ሥፍራ ውስጥ ገብተህ "የምን አንድነት ነው?" ብሎ ወጣቱ ይጮህብሃል፡፡

እኔ ይህ መሆኑ አይገርመኝም፡፡ ትግራይ ክልል መሆኑ በራሱ ትንሽ ቢገርምም በሁሉም ክልል ዘንድ ግን ብሔርተኝነቱ የከፋ ሆኗል፡፡ 45 ዓመት ሙሉ በትግራይ ውስጥ ህዝቡን በብቸኝነት የተቆጣጠረ ይሄ ድርጅት ደግሞ ላለፉት 28 ዓመታት አጠቃላይ ኢትዮጵያን ሲገዛ የነበረ፣ በዚህ ዓመታት የአገዛዝ ሪከርዱ



ለትግራይ ሕዝብ ይሄን ሠርቻለሁ ብሎ የሚያሳየው ምንም ዓይነት ሪከርድ የሌለው ሆኖ ዛሬም "ተቆርቋሪ ነኝ" ሲል እስኪ ምን ለሕዝቡ አደረግክለት? ብለህ መጠየቅ እንኳ አትችልም፡፡

ትግራይ ውስጥ በዛ ሁሉ የትግራይ ልጆች የህይወት መስዋዕትነት በተገኘው ድል ህወሓት እንደ መንግስት መንገድ፣ ት/ቤት ከመሥራት ውጪ ሌላው ቢቀር የህዝቡን ዴሞክራሲያዊ መብት ከማስከበር አኳያ እንኳን ምን አደረገ? ብለህ መጠየቅ እንደ ክህደት ነው የሚቆጠረው፡፡ እንኳን እዛ ሆነህ አዲስ አበባ ወይም ከኢትዮጵያ ውጭ ሆነህ "ላለው ነገር ሁሉ ተጠያቂ ህወሓት እኮ ነው" ብትል እንደ ፀረ ትግራይና ከሀዲ ነው የሚመለከቱህ፡፡

የትግራይ ብሔርተኝነት እንቅስቃሴን ቻሌንጅ ስታደርግ ብዙዎች ደስ አይላቸውም፡፡ "ጎበዝ በብሔርተኝነት ሰክረናል፣ ማሰብ አቁመናል፣ ይሄ አካሄድ ልክ አይደለም፤ ዘላቂ ጥቅማችንን ያስጠበቀ አይደለም" ብለህ የምትነጋገርበት የመግባቢያ ክርክር ወይም የመወያየት ስሜት አሁን ትግራይ ውስጥ ፈፅሞ የለም፡፡ ጭፍን ድጋፍ ነው የሚስተዋለው፡፡ እንዲህ ዓይነት ነገር በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ዓለም ላይም በግልፅ ይስተዋላል፡፡ የዶናልድ ትራምፕ ደጋፊዎች የፈለገ በማስረጃ የተደገፈ የፕሬዝዳንቱን ጥፋት ብታቀርብላቸው ፈፅሞ አይሰሙህም፡፡ "ትራምፕ ልክ ነው" የሚሉት፡፡

ለዓመታት ሲሰራበት የቆየው የብሔርተኝነት ስሜት ለተወሰነ ጊዜ አብሮን ይቆያል ምክንያታዊነት ስለሌለው ግን ጊዜውን ጠብቆ ደግሞ መርገቡና የኢትዮጵያዊ አንድነት ስሜት መጎልበቱ አይቀርም፡፡ አሁን ከኤርትራ ጋራ የሚስተጋባውም ነገር ከዚህ ነጥብ ጋር መያያዝ ነው ያለበት እንጂ ትግራይ ውስጥ የተለየ ነገር ኖሮ አይደለም፡፡ በተለያዩ ክልሎች ውስጥም እየተስተጋባ ያለው እኮ የብሔርተኝነት ፖለቲካው ነው፡፡ መሪዎች ነን የሚሉት ራሱ "አሸንፈናቸዋል፣ ሰብረናቸውል" ሲሉ በማድመጥ ላይ መሆናችንን መርሳት የለብንም፡፡ እንዲህ ዓይነቱን አባባል የህዝቡን ብሔርተኝነት ለማርገብ ነው የምትጠቀመው፡፡ ይሄ አካሄድ ደግሞ ለጊዜውም ቢሆን በፖለቲካ አድቫንቴጅ አለው፤ ብሔርተኝነት ዛሬ የፖለቲካ ካርድ ሆኗል፡፡ ያንን መንገድ ተጠቅመህ ያለህን ወደ ሥልጣን የምታመጣበት ሁኔታ እየጎለበተ ነው ያለው፡፡

**ግዮን፡- በተለያዩ የአገሪቱ ክልሎች ውስጥ በሚፈጠሩ ግጭቶች፣ ስደትና መፈናቀሎች ዙሪያ የህወሓት እጅ አለበት የሚሉ ወገኖች ይበዛሉ፡፡ እርስዎ በዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

አቶ ሙሉጌታ፡- እንደምታውቀው እኔ ጠበቃ ነኝ፤ ሕግ ነው የተማርኩት፡፡ በመሆኑም እንደዚህ ዓይነት ወሬ አይመቸኝም፤ ይሄ ጉዳይ ከብዙዎች ጋርም ያጨቃጭቁኛል፡፡ እኔ የማምነው በማስረጃ ነው፡፡

እንዲህ ዓይነት ርዕስ ላይ ሁሌም ጥያቄ ነው የምጠይቀው፡፡ በሆነ ሥፍራ ግጭት ተነስቶ አንድ ሰው ከሞተና የህወሓት እጅ አለበት ከተባለ እንዴት አወቅህ ነው የምለው? ህወሓት ብቻ ስለሆነ ይሄን ጉዳይ ዶ/ር ዐቢይ ነው ያደረገው ከተባለ ማስረጃህ ምንድን ነው? ብዬ ነው የምጠይቀው፡፡

እንዲህ ዓይነቱ ነገር ለእኔ አሉባልታ ነው፡፡ መንግሥት በተገቢው መንገድ ለህዝብ ትክክለኛ መረጃ በፍጥነት ስለማይለቅ ወይም ስለማያሰራጭ ነው እንዲህ ዓይነት ነገር የሚፈጠረው፡፡ የፖለቲካ ድርጅቶችም ራሳቸው ትክክለኛ መረጃ እየሠጡ አይደለም፡፡ ሚዲያዎችም ራሳችሁ በቂ የሆነ መረጃ በፍጥነት እየሰጣችሁ አይደለም፡፡ ህዝብ ትክክለኛ በማስረጃ የተደገፈ መረጃ ካላገኘ በመላምት ይንቀሳቀሳል፡፡

አንዳንዴ ህወሓት ነው ይሄን ያደረገው የሚባለውን ነገር ስትሰማ እንደዚህ ማድረግ ከቻለ ታዲያ ለምንድ ነው መቀሌ የሚቀመጠው? ትላለህ፡፡ ብዙ ነገር ነው ይሄ ድርጅት አደረገ ሲባል የምትሰማው፤ ስለዚህ ያን ያህል እነዚ ሰዎች ማድረግ መቻላቸውን የማውቅበት ምንም መንገድ የለም፡፡

**ግዮን፡- በቅርቡ ፕ/ት ኢሳይያስ አፈወርቂ ከኤርትራ ቴሌቪዥን ጋር ባደረጉት ቆይታ ደጋግመው ኢትዮጵያን ሲያነሱ ተደምጠዋል፡፡ እርሳቸው ቀደም ሲል ከነበራቸው ባህሪ አንፃር የአሁኑ "ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ" ማለታቸው በአገሪቱ ጉዳይ ጣልቃ ገብነትን ያሳያል የሚሉ አሉ?**

አቶ ሙሉጌታ፡- ሌላው የአገራችን

ችግር ይሄ ነው፤ እውነቱን ንገረኝ ካልከኝ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል ምን እየተደረገ እንደሆነ አላውቅም። በጣም ተቀራርበናል፣ ጥሩ መንፈስ ተፈጥሯል፤ መጀመሪያ አካባቢ ህዝብ ለህዝብ እንደልብ ይገናኝ ነበር፤ አሁን ግን አይገናኝም። መግቢያዎች በሙሉ ስለተዘጉ አሁን ሁሉ ነገር በአየር ብቻ ሆኗል።

ፕ/ት ኢሳይያስም የፈለግነውን ነገር አላገኘንም ብለዋል? የድንበር ችግሩም አልተፈታም ነው ያሉት። ለምንድን ነው ያልተፈታው የሚለውን ግን አብራተው አይነግሩህም። ዶ/ር ዐቢይም እየተንቀሳቀሱ አይደለም። በአጠቃላይ በኤርትራ ጉዳይ ያለው ነገር ከባድ ቢሆንም፣ መሪዎች ሲገናኙና ሲወያዩ ለምን ተገናኙ፣ ምን ተነጋገሩ የሚለው በዝርዝር መገለፅ አለበት፡ ፡ ተፈራረሙ ሲባል ትሰማለህ ምን ምን ጉዳይ ላይ እንደተፈራረሙ ግን ኢትዮጵያውያን እስካሁን ድረስ አናውቅም።

በቅርቡ ፕሬዚዳንት ኢሳይያስ ከተናገሩት ውስጥ በጣም የገረመኝ “አትዮጵያ ውስጥ የሚካሄደውን ነገር ዝም ብለን የምናየው አይደለም፤ ንቁ ተሳታፊ እንሆናለን” የሚለው ነው። በአንድ በኩል ፕ/ቱ ኢትዮጵያ ሉዓላዊ አገር እንደሆነች፣ በሌላ በኩል ደግሞ የእሳቸውን እገዛና ተሳትፎ የሚያስፈልጋት እንደሆነች አስመስለው ያቀርባሉ። ይሄ ነገር ልክ አሁን አንተ እንዳነሳህልኝ በኢትዮጵያ ጉዳይ የኤርትራ ጣልቃ ገብነት አለ የሚለው የሚያጠያይቅ ነው።

እንዲህ ዓይነት ነገሮችን ዶ/ር ዐቢይ መመለስ አለባቸው። ፕ/ት ኢሳይያስ ምን ዓይነት ሚና ነው ያላቸው ኢትዮጵያ ውስጥ? የድንበር ጉዳዩስ ምን ላይ ደረሰ? ከኤርትራ ጋርስ ምንድ ነው እየታሰበ ያለው? የሚለውን ህዝብ በግልፅና በተብራራ መልኩ ሊያውቀው ይገባል።

ሌላው በኤርትራና በትግራይ ፖለቲከኞች ማለትም በፕ/ት ኢሳይያስ አፈወርቂ ድርጅትና በዶ/ር ደብፂዮን ድርጅት ህወሓት መካከል ያለው አለመግባባት ራሱ ትልቅ ችግር ነው፡ ፡ ለረዥም ጊዜ የሚተዋወቁ ኃይሎች ናቸው፡ ፡ ሁለቱ ድርጅቶች እንደሚታወቀው አንዳንዴ የእነሱ ፀብና ቅራኔ ከድርጅት አልፎ ወደ ግለሰቦች ጉዳይ ሲሄድ ታያለህ። የሁለቱን አገራት ጉዳይ ለረዥም ጊዜ ሲወስን የነበረው የመለስና የኢሳይያስ ግንኙነት ነው።

ዶ/ር ዐቢይ ወደ ስልጣን ሲመጡ የኤርትራ መንግሥት ተነስቶ አካኪ ዘራፍ አለ ጨዋታው አለቀ በሚል ዓይነት። የኤርትራና የኢትዮጵያ ጉዳይ የግለሰቦች ጨዋታ ሆኖ ስታየው የሚያሳዝን ነገር ነው። ሁለት መሪዎች የሚገናኙበት ምክንያት ምንድን ነው? ልክ እንደ ጓደኛ በቀጠሮ የሆነ ዊኬንድ ላይ “ለምን ሶደሬ አንሄድም?” ዓይነት የሚይዙት ፕሮግራም ዓይነት ይመስላል። ለዚህ ነው እያንዳንዱን አገራዊ ግንኙነት በተመለከተ የመረጃ ነፃነት አስፈላጊ ነው የምለው።

**ግዮን፡- ከኢትዮጵያ የጂኦ ፖለቲካ ጉዳይ አንዱ የዓባይ ግድብ እንደመሆኑ መጠን፣ በአሜሪካና በዓለም ባንክ አደራዳሪነት ኢትዮጵያ ከግብፅና ከሱዳን ጋር በምታደርገው ውይይት ላይ ጥቅሟን የሚያሳጡ ተጽዕኖዎች እየተደረገበት ነው ይባላል እርስዎ ምን ታዘቡ?**

አቶ ሙሉጌታ፡- በዚህም ላይ መንግሥት እንደሌሎቹ ጉዳዮች ዝርዝር የድርድር ነጥቦቹን ለህዝብ ግልፅ አድርጎ ባላስቀመጠበት ሁኔታ እንዲህ ነው ብዬ መናገር ይከብደኛል። እኔ በዓባይ ዙሪያ ተስፋ ብቻ ነው የምፈልገው።

ለምሳሌ ውሃው እንዴት ይሞላ? የሚለው አያስጨንቀኝም። እሱ በሁለተኛ ደረጃ ልታስበው የምትችለው ነገር ነው። በሰባት ዓመት ይሞላ በሳምንት ዓመት ቢባል እሱ ብዙ ችግር የሚያመጣ ይመስለኛል። ነገር ግን ማኔጅመንቱ ላይ የግብፅ ፍቃድ የሚያስፈልግ ከሆነ፣ ኢትዮጵያ አንድ ነገር ማድረግ ከፈለገች ግብፅ መፍቀድ አለባት የሚል ወዳጃዊ (ፍሬንድሊ) ግንኙነት ቢኖር ጥሩ ነው።

በዋናነት ግብፆች እንዲጎዱ አይደለም የሚፈለገው፤ ግን የግድቡ ባለቤት እንደመሆናቸው መጠን የወደፊቱ ስትራቴጂንክ ፍላጎት ኢትዮጵያን በማይጎዳ መልኩ መሆን አለበት። ልክ የአልጀርሱን ስምምነት ዓይነት ስህተት እንዳይደገም እንደ ዜጋ ጸሎት አደርጋለሁ።

ግዮን፡- ብሔርና ሀይማኖት ተኮር ጥቃቶች፣ እንዲሁም የተለያዩ ግጭቶች አገሪቷን እየተፈታተኗት ነውና እንደ ህግ ባለሙያነትዎ ምን መደረግ አለበት ይላሉ?

አቶ ሙልጌታ፡- ሁለት ነገር ነው ያለው፣ የፖለቲካና የህግ ጥያቄ። ዛሬ ኢትዮጵያ ወስጥ የህግ ጥያቄው ገሸሽ ብሎ የፖለቲካ ጥያቄ ነው እየገፋ ያለው። ይሄ የሆነው ደግሞ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ተቃርኖ ውስጥ ያለች በመሆኑ ነው። ለዚህ ነው ኢትዮጵያ እየደማች ነው የምለው። አንድ ድርጅት (ኢህአዴግ) እንደፈለገው ሲገዛ በመቆየቱ የእሱ ፖለቲካ ውጤት ነው የዛሬውን ችግር የወለደው። ኢህአዴግ በማይገፋ ነገር ነው ብዙ ሲገፋ የቆየው። በሚያስማማና በሚያቀራርበን ጊዜ ላይ ሳይሆን የምንለያይበት ነገር ላይ ነው የተለያዩ ድርጅቶች ጊዜያቸውን የሚያጠፉት።ይኽ ፖለቲካ ሕዝቡ ላይ እየወረደ ሄዶ ከብሔርተኝነት አልፎ ወደ ሀይማኖታዊ ጥቃት እንዲሸጋገር ዓይነተኛ ሚና ተጫውቷል።

እንዲህ ባለ መልኩ አገሪቱ እየደማች ነው። አንድ ሰው ደም መድማት ከጀመረ “ድንገተኛ” ተብሎ ህክምና ሲወስድ የመጀመሪያው የሐኪሙ ስራ የሚፈስ ደሙን ማስቆም ነው። ስለዚህ አሁን እዚህ አገር ማድረግ ያለብን የሚፈሰውን ደም ማስቆም ነው። ሰው ይሞታል፣ ይሰደዳል፣ ይፈናቀላል፡ ፡ እንደ ልቡ ለመንቀሳቀስ ይሰጋል፤ በሥርዓቱ አለመተማመን ደግሞ የፖለቲካ ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚ ችግርና ስጋትን ይፈጥራል፡ ፡ ለዚህ ደግሞ መፍትሄው በከንቱ እየፈሰሰ ያለውን ደም ማስቆም ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ ህግ ለሚያስፈልገው የህግ ማዕቀፍ በማውጣት፤ በህግ ቀዳዳው የማይደፈንና የማይሻሻል ከሆነ ደግሞ የፖለቲካ መፍትሔ መስጠት ይገባል።

አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ችግር በመጀመሪያ ደረጃ የህግ ሳይሆን የፖለቲካ ችግር ነው። ዘጠኝ ክልሎች ብትንትናቸው ወጥቷል፤ ጭራሽ ልዩ ኃይል የሚባል ጦር አደራጅተው ልክ መከላከያ ሠራዊት የሚታጠቀው ዓይነት መሳሪያ ታጥቀው እንደፈለጉ ሲፈነጩ ታያለህ። በቅርቡ ትግራይ ውስጥ የተመለከትኩት እንዲዚህ ዓይነት ኃይል ነው። እዚህ አገር እውነት አንድ መንግስት ብቻ ነው ያለው? የምትልበት ሁኔታ ላይ ደርሰናል።

ይሄን ዓይነቱን ችግር በህግ ልትፈታው አትችልም። ለምሣሌ ዶ/ር ዐቢይ ትግራይ ውስጥ ባለው መንግስት የሆነ ነገር እንዲተገበር ቢያዙና ህወሓት ያንን አልፈፅምም ቢል ምንድን ነው የምታደርገው? እሱ ነገር እስከ ዛሬ አልተመለሰም። የፖለቲካ ቀውስ ስለገፋ ሀጉ በመደበኛ ሁኔታ እየሰራ ስላልሆነ የጉልበት ስራ ይመጣል ማለት ነው። የህግ ዓላማ ጉልበትን ማስቀረት ነው። ጉልበት እየበዛ ሲሄድ የህግ መፍትሔ ሳይሆን የፖለቲካ መፍትሄ መፈለግ ትጀምራለህ ማለት ነው።

ስለዚህ በኢትዮጵያ መሬት ውስጥ ያሉ የተለያዩ ኃይሎች፣ ማዕከላዊ መንግሥትም ሆነ የክልል መንግሥታት ፣ በዛ ውስጥ ያሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ሊሆኑ ይችላሉ ያለው የፖለቲካ ችግር ነው ከተባለ አንድ ላይ ተገናኝተው በመነጋገር መፍታት ይችላሉ። የህግ ችግር ከሆነ በፍ/ቤት የሚፈታ ነው። ግን ችግሩ እሱ አይደለም። ቤተ ክርስቲያናትና መስጊዶች ይቃጠላሉ፣ እዛ ወስጥ የተለያዩ አካላት ተሳትፎ አለ። ይሄን በህግ መፍትሄ ልታቆመው እንደማትችል መመልከት ይቻላል፡ ፡ ጉዳዩን በፖለቲካ መፍትሄ ለመቋጨት ደግሞ መነጋገር የግድ ይላል።

**ግዮን፡- የኢትዮጵያ የደህንነት ኃይል በአሁኑ ሰዓት በእጅጉ የሳሳ ነው የሚሉ ወገኖች አገሪቱን አልሸባብን ጨምሮ ለሌሎች የጥፋት ኃይሎች ተጋላጭ ሊያደርጋት ይችላል በሚል ይተቻሉ። ይሄን ግምት ውስጥ በመክተት የአገሪቱን የፀጥታና የደህንነት ኃይል መተማመን ይቻላል?**


አቶ ሙሉጌታ፡- እኔ በበኩሌ ደህንነቱም ሆነ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ዶ/ር ዐቢይ ሥልጣን በያዙ በ20ኛው ቀን ነው እንዲቀየር የተደረገው። መጀመሪያ የገመትኩት ደህንነቱና መከላከያውን ቀስ በቀስ የሚቀይሩት ነበር የመሰለኝ፣ ቀስ ብሎ መስተካከል እንዳለበትም በወቅቱ በአንድ ቃለ መጠይቅ ላይ ገልጫለሁ፤ እነ ጌታቸው አሰፋ ሳይባረሩ በፊት።

ግን ከባድ ስህተት ነው የተሰራው፡ ፡ በርግጥ የኢትዮጵያ ደህንነት ከባድ የሆነ የሰብዓዊ መብት ጥሠት ችግርና ጥፋት ነበረበት። በርግጥ ይሄ የደህንነት ቢሮው ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የኢህአዴግም ችግር ነው። በሌላ በኩል ግን ስታየው ኢትዮጵያን ከብዙ ነገር ታድጓት ቆይቷል። እንደነኬኒያ የአልሸባብ መጫወቻ አልሆነችም፤ ኢትዮጵያ፡ ፡ ከዚህ አንፃር ደህና የተጠናከረ መንግሥት ነበር ማለት እችላለሁ፤ እሱ ቀስ በቀስ ትራንስፎርምድ ቢሆን ኖሮ ችግር አይፈጠርም ነበር።

ካስታወስክ ጌታቸው አሰፋና ጀነራል ሳሞራ በአንድ ቀን ነበር የተነሱት። በነገራችን ላይ ህወሓቶችንም በጣም ያስደነገጣቸው አንዱ ጉዳይ እሱ ይመስለኛል። በአንድ ጊዜ በጣም ይተማመኑበት የነበረውን ተቋም ሲያጡ ሽሽቱን ነው የገፉበት። ጌታቸው አሰፋ ከደህንነቱ መ/ቤት ምስረታ ጀምሮ የነበረ እንደመሆኑ መጠን እንደ እሱ ዓይነት ሰዎች ሲነሱ የሚጎድል ነገር ይኖራል። እሱ የሚፈጥረውን ክፍተት አሟልተህ እንደ አዲስ መጀመር ሊኖርብህ የሚገባውን ባለማድረግህ ምክንያት የተፈጠረውን ችግር ነው አሁን እያየን ያለነው።

በባህር ዳር እና በደምቢዶሎ የተፈጠሩት ችግሮች የሚያሳዩንም የደህንነት ችግሮች የሰፉ መሆናቸውን ነው። ይሄንን የደህንነቱን ተቋም ቀደሞ ወደነበረበት ጠንካራ አቋም ለመመለስ ኃይለኛ መረባረብ እንደ አገር የሚጠይቅም ይመስለኛል።

**ግዮን፡- እናመሰግናለን።**





ፍቃዱ ልመንህ - ሀያሲ.

# የአርቲስቶቻችን ጠቃሚ ንግግሮች የሀገራችን የፊልም ኢንደስትሪ እንዲያድግ የቀረቡ ጥቆማዎች

ሰላም ለእናንተ ይሁን!

በፊልምና በቴአትር ስራዎቻችን ሳይ የግዴለሽነትና ከኛ በላይ ለአሳር የሚል አመለካከት የበዛ ስለመሰለኝ ‹‹እየተስተዋለ ይሰራ›› ለማለት ያህል ሂስ ወደመስጠቱ የተለመደ ተግባሬ ተመልሻለሁ፡፡ ከሚቀጥለው ዕትም ጀምሮ በስራዎች ላይ ሂሳዊ ዳሰሳ አቀርብላችኋለሁ፡፡ ለዚህ ዕትም ግን ‹‹የአቡጄዲ ግርግር›› ከተሰኘው መጽሐፌ ላይ ይህንን ሀሳብ መርጩላችኋለሁ፡፡ መልካም ንባብ፡፡

በተለያዩ መፅሔቶች ላይ እንግዳ ሁነው የተጋበዙ ባለሙያዎች በተሰጣቸው የቃለ መጠይቅ እድል በፊልም ዙሪያ እየሆነ ያለውን፣ የሆነውን፣ እንዲሆን የሚፈልገውን... ጠቁመው ነበር፡፡
በተናጠል ሀሳባቸውን ሲያቀርቡ ባለመለወጣችን ነገሮችን አፅንኦት ለመስጠት በጅምላ አሰባስቤ አቅርቤላችኋለሁ፡፡ በተለያየ ወቅት ለንባብ የበቁ የቁም ነገር ስብስቦች ይተገበሩ ዘንድ ሁላችንም በየተሰማራንበት ዘርፍ አስተዋፅኦ እናድርግ!

መተካካት ያስፈልጋል
‹‹ዘላለም እኛ ብቻ ስራውን በሞኖፖል እንያዝ እያሉ አዳዲስ የኪነጥበብ ሰዎችን ሽፍኖና ተስፋ አስቆርጦ ራስን ማኩፈስ ተገቢ አይደለም፤ የሙያ ብቃት ማረጋገጫም አይደለም፡፡ ....መተካካት መልመድ አለብን፣ በየዘመኑ አዳዲስ ሙያተኞች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ አምነን መቀበል ይኖርብናል፡፡... የተወሰነ ጊዜ ትሰራለህ በኋላ ካንተ የተሻለና ተገቢው ሙያተኛ ሲመጣ ቦታውን ለቀህ እድሜህ የሚፈቅደውን ነገር ትሰራለህ››
ዘሪሁን አስማማው
ኢቦኒ መፅሔት 4ኛ ዓመት ቁጥር 42 ሰኔ 2003 ዓ.ም

መንግስት አብሮን ቢሆን
‹‹የፊልም ኢንዱስትሪው እያደገ ነውና ደስ ያሰኛል፡፡ ይህ እንዲሆን እየጣሩና የበኩላቸውን እየተወጡ ላሉ ሁሉ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ መንግስትም ለዚህ ዘርፍ ትኩረት ቢሰጥና የራሱን ሚና ቢጫወት መልካም ነው፡፡ ያሉትን ማነቆዎች በማስወገድ የፊልሙ ኢንደስትሪ እንዲበረታታ ማድረግ ይገባዋልና መንግስትም አብሮን ቢሆን የሚል መልዕክት አለኝ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም ከነስህተታችን ተቀብሎን አብሮን ከመሆን ያልቦዘነ ተመልካች አለን፡፡ ይህ ያበረታታል፤ ስለዚህ ይህን ተመልካች ልናመሰግነው ይገባል፡፡ ጥሩ ስራም ይዘንለት ልንቀርብም ይገባል››
ቶማስ ጌታቸው
አርሂቡ ቅፅ 1 ቁጥር 8 የካቲት 2003 ዓ.ም

እኔን ካላረካኝ አልሰራም
‹‹ህሊናዬ የማይፈቅደውን ሥራ ብሰራ አርቴፊሻል ነው የሚሆነው፡፡ ስራ ስለሆነ መስራት ብቻ ሳይሆን የምሰራው ስራ መጀመሪያ እኔን አርክቶኝ ማለፍ አለበት፡፡ እኔን ሊያስደስተኝ ካልቻለ ማንም ይደሰታል ብዬ አልገምትም፤... ስለዚህ ከምሞትበት ይልቅ በምኖርበት መንገድ ነው መሄድ ያለብኝ››
ውብዓለም አለባቸው
ዳና መፅሔት ቅፅ 1 ቁጥር 8 ሚያዚያ 1997 ዓ.ም

በየክፍለከተማው ሲኒማ ቤት
‹‹በአዲስ አበባ በየክፍለ ከተማው አንድ አንድ ሲኒማ ቤት ቢኖር መልካም ነው፡፡ ሲኒማ ቤቶች በዚህ መጠን ሲበዙ ፊልሞቻችን በአንድ ወር ታይተው ይወርዱና ወደ ዲቪዲ ይሰራጫሉ፡፡ የዚያን ጊዜ ፕሮዲውሰሮች አዲስ ፊልም ወደማምረት ይገባሉ፡፡ ...እንዲህ ከሆነ ፕሮዲውሰሩ በአጭር ጊዜ ገንዘቡን ከመመለስ አልፎ አትራፊ ይሆናል››
ኪሩቤል አስፋው
ዕንቁ መፅሔት 4ኛ አመት ቁጥር 044 ሚያዚያ 2003 ዓ.ም

ሰዎችን ስለማድመጥ
‹‹ጀማሪ ነህ ማለት አትችልም ማለት አይደለም፡፡ ስትሰራ አካባቢህ ማድመጥ አለብ፤ ዳይሬክት የሚያደርግ ሰው ልበሙሉነቱ እንዳለ ሆኖ መሸወድ የሌለበት ነገር ሰዎችን ማዳመጥ መቻል አለበት፡፡ ዳይሬክተር ሁሌም ለመማር ዝግጁ መሆን አለበት››
ሄኖክ አየለ
ሮያል መፅሔት ቅፅ 4 ቁጥር 45 ሰኔ 2002 ዓ.ም

በሞኖፖል ስለመያዝ
‹‹የሀገራችን ፊልሞች ፈጠራ ላይ የሚያተኩሩ አይመስሉኝም፡፡ የታሪክ አወቃቀር ላይ ብዙም ልዩነት የላቸውም፡፡ ያም የሖነበት ምክንያት የሆኑ ሰዎች ያንን ቦታ ነክሰው ይዘውታል፡፡ አዲስ ጉዳይ ላይ እንስራ ማለትን ይፈራሉ፡፡ እነሱ ብቻ የሚያውቁ ስለሚመስላቸው የእነሱ ያልሆነ አዲስ ሀሳብን ማስተናገድ ያስፈራቸዋል››
አንዱአለም ጌታቸው (ፈላስፋው)
ላይፍ መፅሔት 7ኛ አመት ቁጥር 77 ነሐሴ 2003 ዓ.ም

ስለ አንሜተሮች

‹‹በኛ ሀገርም ቢሆን በጣም አሪፍ ነገር ሊሰሩ የሚችሉ አንሜተሮች አሉ፡፡ ግን ያን ችሎታ የማይጠቀሙት የሚረዳቸው ህብረተሰብ ያለ አይመስለኝም፡፡ ...ስክሪፕት ለመፃፍና አኒሜት ለማድረግ በቂ ሀይል አይጠፋም››
አዲያም ሽመልስ
ሔርሜላ መፅሔት ቅፅ 1 ቁጥር 03 የካቲት 2000 ዓ.ም

ስለ ፊልም ሰሪዎች ጉራ
‹‹በኢትዮጵያ ፊልም ሰሪዎች ነን የሚሉ ወጣቶች ጉረኞች ናቸው፡፡ ጉራና ሲኒማ ደግሞ አብሮ አይሄድም፡፡ እኔ ጉረኛን ሰው አርት አይቀርበውም ነው የምለው፡፡ መጥተው ሲያገኙህ አስቀድመው ኢትዮጵያ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ፊልም ሰርቻለሁ ነው የሚሉኝ፡፡....በፊልም ሰሪዎች መካከል መናቅ አለ››
ፕሮፌሰር ሀይሌ ገሪማ
ሮዝ መፅሔት ቅፅ2 ቁጥር 25 ህዳር 2001 ዓ.ም

ስለፕሮሞሽንና ማርኬቲንግ
‹‹...አንድ ፊልም ተሰርቶ ካለቀ በኋላ የፕሮሞሽን ስራውን የሚሰራው ዳይሬክተሩ ወይንም ፕሮዲውሰሩ ነው፤ ስለዚህ ጥሩ ፊልም ሰርተን ለሳሙናና ለሌሎች ቁሳቁሶች በምንጠቀምበት የማስተዋወቅ ስትራቴጂ ነው እየተመራን ያለነው፡፡ ስለዚህ ባለሙያዎች ፊልማችንን ካጠናቀቅን በኋላ ማርኬቲንጉን ሊሰራልን የሚችል ባለሙያ ያስፈልገናል››
ዮናስ ብርሃነ መዋ
ዕንቁ መፅሔት ቅፅ 4 ቁጥር 46 ሰኔ 2003 ዓ.ም

የመጥፎና የጥሩ ታሪክ ውጤት
‹‹ማንኛውንም ስራ ስሰራ ታሪክ መስራትን አላማ አድርጌ አይደለም፡፡ ስኖር የሚያስደስተኝን ነገር መስራት እንዳለብኝ አምናለሁ፡፡ ውስጤን ያስደሰተው ነገር ደግሞ ታሪክ መሆኑ አይቀርም፡፡ መጥፎ ሲሆንም የዛኑ ያህል በታሪክ መወቀስ አለ››
ጌትነት እንየው
ጠብታ መፅሔት ቅፅ 1 ቁጥር 01

ፊልም እንደተመላካቹ ነው
‹‹መሳቅ የሚወዱ ተመልካቾች ይህንን ፊልም ሲመለከቱ ‹‹ውይ! ይሄ ፊልም›› ሊሉ ይችላሉ፡፡ ያ ማለት የእነሱ ምርጫ ነው እንጂ የፊልም ሴክተሩ የዚህ አይነት ፊልሞችን መስራት የለበትም ማለት አይደለም፡፡ ሲኒማ ቤቶችም ለእንደዚህ አይነት ፊልሞች ጊዜ መመደብ አለባቸው፡፡ በአጠቃላይ የተመልካች እይታ ይለያያል››
ደሳለኝ ሀይሉ
ኢቦኒ መፅሔት 5ኛ ዓመት ቁጥር 59 ሐምሌ 2004 ዓ.ም
ከመውደቅ መነሳት
‹‹ሁሉን ነገር ተጠንቅቀህ ሰርተህ ምናልባት ጨርሻለሁ ብለህ ካቀረብክ በኋላ ልታስተካክለው የማትችለው ስህተት ልታገኝ ትችላለህ፡፡ መውደቅ ከሌለ መቆም አይቻልም፡፡ ከፊትህ የሚወድቅ ሠው ከሌለ ላለመውደቅ አትጠነቀቅም››
ኩራባቸው ደነቀ
ጠብታ መፅሔት ቅፅ 1 ቁጥር 01

ለመረጃ ቅርብ እንሁን
‹‹ማንበብ ሙሉ ሰው ያደርጋል፡፡ ለአርቲስቶች ብቻ አይደለም ማንም በየትኛውም ሙያ ውስጥ ያለ ሰው ማንበብ ይኖርበታል፡፡ ምንም ነገር ሳይመርጡ ማንበብ ብቁና ሙሉ ሰው ያደርጋል፡፡ ስለማነብ ምንም ብጠየቅ አላፍርም - እመልሳለሁ፡፡ ማንበብ የሁላችንም ሆቢ ይሁን! ለመረጃ ቅርብ እንሁን!
ኮሜዲያን ደረጄ ሀይሌ
አርሂቡ መፅሔት ቅፅ 2 ቁጥር 22 ሚያዚያ 2004 ዓ.ም ■


# አንደበት



"ይሄ አሁን እየተደረገ ያለው ለውጥ ከዘውድ ሥርዓት ወደ ደርግ፣ ከደርግ ወደ ኢህአዴግ ካደረግናቸው ሽግግሮች በባህሪው የተለየ ነው፡ ፡ የፖለቲካ ሽግግር ባህሪውም ይለያል፤ የሲቪል ሰርቪሱ ሽግግር ላይም ይለያል፡፡ ቀደም ብሎ የነበሩት ሁለቱ ሽግግሮች ማለትም የደርግም ሆነ የኢህአዴግ አፍርሶ በመስራት ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ይሄኛው ግን ከውስጥ የመነጨ ለውጥ ነው፡፡ የሕዝብ ከፍተኛ ትግል የተካተተበት ነው፡፡ በነገራችን ላይ ሁሉም ለውጦች በሕዝብ ተሳትፎ ነው የመጡት፡፡ እኔ እንደ አንድ የሕዝብ አስተዳደር ባለሙያ ሁኔታውን ስረዳው፣ ለውጦቹ በሙሉ በሕዝብ ተሳትፎ የታጀቡ ብቻ ሳይሆኑ ሕዝብ ከፍተኛ ዋጋ የከፈለባቸው ናቸው፡፡ አሁንም ባለው ለውጥ የሕዝብ ተጋድሎ ዋናውን ድርሻ ይይዛል፡ ፡ ይሄ ለውጥ ባህሪው የተለየ ነው በምንልበት ጊዜ፣ ሥርዓቱን አፍርሶ በመስራት ሳይሆን፣ የነበረውን ስርዓት ችግሮች በማረም፣ የነበረውን በጎ በማስቀጠል ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይሄ ለውጥ በዚህ መልኩ ቢመራም፣ በኢህአዴግ ሥርዓት 27 ዓመት የፖለቲካ አባል ሆኖ የነበረ ሲቪል ሰርቫንት ብዙ ነው፡፡ ስለዚህ በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ የዚህ ዓይነት የፖለቲካ ዝምድና የነበረው ሲቪል ሰርቫንት ለውጡን በሙሉ ልቡ እኩል ተቀብሏል ወይ ? የሲቪል ሰርቪሱ አንዱ ፈተናው ይሄ ነው"

ዶ/ር ፈንታ ማንደፍሮ /የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር/

አዲስ አድማስ ጋዜጣ የካቲት 7 ቀን 2012 ዓ.ም



"ሌላውን እንተወውና ሰሞኑን የምንሰማው የኮሮና ቫይረስ ትልቅ ፈተና ነው የሚሆንብን፡፡ የቫይረሱ መስፋፋት ሊተሰብ የማይችል ጫና ያመጣል ተብሎ ነው የሚገመተው፡፡ በዓለም ገበያ በርካታ ሥራዎች አሁን ላይ ቆመዋል፡፡ በተለይ አሁን ከቻይና ጋር ያሉ የንግድ ልውውቶች፣ በአገር ውስጥ ላሉ የቻይና ኩባንያዎች ጥሬ እቃ የሚያቀርቡ ኩባንያዎች እንቅስቃሴ እየተዳከመ ነው የመጣው፡፡ በዚህ ደግሞ አገሪቱ ወደ ውጭ የምትልከው ምርት ይቀንሳል፡፡ አሁን ያሉት አንዳንድ ችግሮች ከእኛም ቁጥጥር ውጭ የሆኑ ናቸው፡ ፡ አብዛኞዎቹ የአውሮፓ አገሮች ዕድገታቸው ችግር ገጥሞት በፈተና ውስጥ ነው ያሉት፡፡ እኛ ደግሞ ቀድሞውንም የአሜሪካ ገበያ ጨምሮ በአውሮፓ ገበያ ላይ ብዙም አይደለንም፡፡ ብዙው መዳረሻችን የእስያ አገር ናቸው፡፡ ስለዚህ የውጭ ንግዳችን መዳከሙ አይቀሬ ነው፡፡ በዚህ ደግሞ በምንፈልገው መጠን ዶላር ማግኘት አንችልም፡፡ ያም ከፊታችን የተደቀነ ትልቁ ፈተናችን ነው፡፡ በዚያ ላይ እኛ በምንወዳደርበት የግብርና ምርት ብዙ ተወዳዳሪዎች አሉበት፡፡"

አቶ ክቡር ገና /የምጣኔ ሀብት ባለሙያ/

ሲራራ ጋዜጣ የካቲት 7 ቀን 2012



"በኢትዮጵያና ኤርትራ መካከል የወረደው ሰላም ትልቅ ክስተት ነው፡፡ እንደሚታወቀው ለ20 ዓመታት የዘለቀውን መፋጠጥ ፈረንጆ እንደሚሉት 'no war no peace' ማለት ጦርነትም ሆነ ሰላም የሌለበትን ሁኔታ የለወጠ ክስተት ነው፡፡ በምድር ላይ እንደዚህ ዓይነት መጥፎ ነገር የለምለለ 20 ዓመት የተቃጠለ ጊዜ ማለት ነው፡፡ ሁለቱም ሀገራት ያጠፉን ሀብት ለልማት ቢጠቀሙበት ኢኮኖሚያቸውን ትልቅ ደረጃ ማድረስ ይችሉ ነበር፡፡ እንደሚታወቀው የዛሬ 2 ዓመት ገደማ ኢትዮጵያ ውስጥ ያልተጠበቀ ሪፎርም ተካሄደ፡፡ ዶ/ር ዐቢይ አህመድ ጠ/ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ፡፡ ይህንን ለውጥ ተከትሎ በአንዳንድ የአከባቢው ሀገሮች ሽምጋይነት ወደ ሰላማዊ መንገድ እንዲሄድ ተደርጓል፡፡ እዚህ ላይ ሳውዲ አረቢያና የተባበሩት አረብ ኢምሬቶች ትልቅ ሚና የተጫወቱ ይመስለኛል፡፡ ይህ የሰላም ስምምነት ለኢትዮጵያና ኤርትራ ብቻ ሳይሆን ለመላው አፍሪካ ቀንድ ቀጠና፣ ከዛም አልፎ ለመካከለኛው ምስራቅ ትልቅ አንደምታ ይኖረዋል፡፡ በአካባው ሰላምና መረጋጋትን ለዘለቄታው ሊያሰፍን ይችላል፡፡ ሰላም ካለ ደግሞ የኢኮኖሚ ዕድገት ይኖራል፡፡ ሰላምና መረጋጋት ካለ የፖለቲካ መረጋጋት እንዲሁ ሊፈጠር ይችላል"

ፕሮፌሰር ተስፋዬ ታፈሰ /የአፍሪካ ጥናት መምህርና ተመራማሪ/

አዲስ ልሳን ጋዜጣ የካቲት 5 ቀን 2012 ዓ.ም



"ወያኔ አዲስ አበባ እስኪገባ ድረስ በሙያዬ አገልግያለሁ፡፡ ከገባ በኋላ ወያኔ እኔን ይዞ በዐቃቤ ህግ ግርማ ዋቅጅራ አማካኝነት ዓለም በቃኝ እስር ቤት ውስጥ ለ10 ዓመት ያህል ያለደምወዜና ያለጡረታ አበል አቆዩኝ፡፡ በዚያ ወቅት ቤተሰቤ የገቢ ምንጭ ተዘግቶበት ሲንገላታ ቆይቷል፡፡ ከዚ በኋላ ነው ነፃነቴን ያገኘሁት፡፡ ከእስር ቤት ከወጣሁ በኋላ እኔን ጨፍጫፊና የጨፍጫፊ ርዝራዥ እያሉ ይፎክሩብኝ ነበር፡ ፡ ግርማ ዋቅጅራ ጨፍጫፊ ባለበት አንደበቱ፣ "ምንም ወንጀል የለበትም" የሚል ፅሁፍ ሰጥቶ ተለቀቅኩኝ፡፡ በእስር ወቅት ጠባቂዎቹ ተርራዥ እያሉኝ እንዳልነበር፣ የሰጡሁትን ምስክርነት ሰምተው ጫማዬ ላይ እየወደቁ ሀሳባቸውን መቀየራቸውን ነግረውኛል፡፡ ከእስር ከተለቀቅኩ በኋላ፣ "አንስራ እንስራ" ብባልም መንግስት ጋር አልገባሁም"

ብ/ጄ ታደሰ ተ/ኃይማኖት

ኢትዮጲስ ጋዜጣ የካቲት 8 ቀን 2012 ዓ.ም



"ብዙ ጊዜ ወረርሽኝ ሲመጣ ነው የጤና ስርዓታችንን የምናየው፡፡ ይህ ግን መሆን የለበትም፡፡ ወረርሽኝ በማንኛውም ጊዜ ይመጣል፡፡ ይኼ ችግር በእርግጠኝነት ነገ ይጠፋል፡፡ ይህ ማለት ግን ወረርሽኝ ሌላ ጊዜ አይመጣም ማለት አይደለም፡፡ ስለዚህ ምግዜም ወረርሽኝ ታሳቢ ተደርጎ መሰራት አለበት፡ ፡ የጤና ዘርፉን ማጠናከር ማለት በቀጥታ ለወረርሽኝ የሚያበቃውን ሁኔታ ማጠናከር፣ ያንን ሊሸከም የሚችል ብቃት መፍጠር ማለት ነው፡፡ ለጤና ዘርፉ የሚመደበውም በጀት እዚህ ላይ ታሳቢ መደረግ መቻል አለበት፡፡ ኢትጵያ ለአንድ ሰው የምታወጣው የጤና ወጪ በዓመት ወደ 23 ዶላር ነው፡፡ ይህ ከዓለም አቀፉ አማካይ ጋር ሲገናኝ አይቻልም፡፡ የአፍሪካን አማካይ እንኳን ብናየው የኢትዮጵያ በእጅጉ ዝቅ ያለ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ችግሮችን ለመሸፈን ከባድ ነው፡፡ ስለዚህ በተቻ መጠን ለጤና የምንመድበው በጀት ላይ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ተገቢው በጀትም መመደብ አለበት፡፡ ይህ ሲሆን መሠረተ ልማቶችና አቅም ይገነባሉ፡፡ አደጋ በሚመጣበት ወቅት ለመመለስ የሚኖረውን ሩጫ ይቀንሳል፡፡ ለጤና በተለይ ለአደጋና ለቅድመ ዝግጅት የሚመደበው በጀት ዳግም መታየት አለበት፡፡ ድንገት ለሚከሰቱ ወረርሽኞች መንግሥት ምንግዜም መጠባበቂያ በጀት አለው፡፡ መጠባበቂያ በጀቱን በምናቀርበው ዕቅድ መሠረት የሚመደብ ነው፡፡"

ኤባ አባተ /የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር/

ሪፖርተር ጋዜጣ የካቲት 8 ቀን 2012 ዓ.ም



"ከጥቂት ሳምንታት በፊት ከነዳጅ ፍለጋና ማውጣት ጋር በተያያዘ ከአፍሪካ ኅብረት የኃይል መምሪያ ጋር ስብሰባ ነበረን፡፡ በአፍሪካ የነዳጅ ፍለጋ እየተስፋፋ፣ ከሞሮኮ፣ ሊብያ እና ግብጽ ከመሳሰሉ ሰሜን አፍሪካ አገራት ወደ ምዕራብ አፍሪካ (ናይጀሪያ) እንዲሁም ቀጥሎ ወደ ደቡብ አፍሪካ፣ አንጎላ፣ ዩጋንዳ እና ሱዳን እየተስፋፋ ነው፡፡ ኬንያም በቅርቡ የነዳጅ ድፍድፍ አግኝታለች፡፡ ይህም ከኢትዮጵያ ቅርብ በሆነው የኦሞ ወንዝ ዳር ላይ ነው፡፡ ታንዛንያ፣ ኬንያ እና ደቡብ ሱዳንም ነዳጅ አግኝተዋል፣ ይህ በኢትዮጵያም ሊሆን የሚችል ነው፡፡ ይሁንና በእነዚህ አገራት የነዳጅ አጠቃቀም አሁንም አስቸጋሪ ነው፡፡ በቀደመው ጊዜ ናይጄሪያ ነዳጅን ወደ አሜሪካ እና አውሮፓ ትልክ ነበር፡፡ ሆኖም ይህን ያልተጣራ ነዳጅ አሜሪካ ማስገባት ስታቆም ናይጄሪያ ትልቅ ገቢያ አጥታለች፡፡ ለአፍሪካ አገራት ድፍድፍ ነዳጅን ወደ ውጪ አገራት መላክ አዋጭ አይደለም፡፡ ናይጄሪያም ያንን ነዳጅ ወደ መካከለናው ምሥራቅ ለመላክ ተገዳለች፡፡ ያም ሆኖ የመካከለኛው ምስራቅ ገበያም ምቹ አልነበረም፣ ገበያው ቀድሞ ያደገ ስለሆነ፡ ፡ ስለዚህ እንደ ናይጄሪያ ያሉ ነዳጅ ላይ ጥገኛ የሆኑ የአፍሪካ አገራት፣ በዚህ ምክንያት እየወደቁ ነው"

አቶ ታደሰ ጥላሁን /የኖክ ማደያ ዋና ሥራ አስፈፃሚ/

አዲስ ማለዳ ጋዜጣ የካቲት 7 ቀን 2012 ዓ.ም

# ጠ/ሚኒስትር ዐብይ የብሉይ ኪዳንን ሕግ ይጠቀሙበት



ደረጀ ዘውዴ

ሰውዬው ሁል ጊዜ ወንጌልን ብቻ እየተማረ ሲኖር ሌሎች ያጠቁት ነበር፡፡ የተማረው አዲስ ኪዳን ግራ ጉንጭህን ሲመቱህ ቀኝህን ስጠው የሚል ስለነበር ሁል ጊዜ መደብደብ ኑሮው ሆነ፡፡ እጀ ጠባብህን ለወሰደብህ መደረቢያህን ጨምርለት ስለሚል ሁልጊዜ መዘረፍ ስራው ሆነ፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ግን ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስን ሲያገላብጥ የብሉይ ኪዳንን የኦሪቱን ሕግ ማንበብ ጀመረ፡፡ "የገደለ ይገደል ፤ጥርስ ያወለቀ ጥርሱ ይውለቅ" ወዘተ….. የሚለውን አነበበ፡፡ ቃሉ የመጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን አረጋገጠና ወደ ስራው ሲሄድ እንደተለመደው ደብዳቢዎቹ እና ዘራፊዎቹ የተለመደውን ጥፊ አቀመሱት፡፡ እሱ ግን ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ግራ ጉንጩን ከመስጠት ይልቅ በጥፊ የመታውን ሰው ጉንጭ መልሶ በጥፊ አቀረናው፡፡ ሌላውም በቡጢ ሲመታው እሱም መልሶ አንጀት በሚያርስ ቡጢ ጠለዘው፡፡ አጥቂዎቹ ደንግጠው "ምን ነካህ የእግዚአብሔር ሰው አልነበርክም" ብለው ፈረጠጡ፡፡ ቡጢ የቀመሰው ሰው ሊደግመው ሲል "እባክህ አትድገመኝ በቀደም የወሰድኩብህን እመልሳለው" አለው ሰውዬውም ሁኔታው አስደንቆት እንዲህ አለ "ወይ አዲስ ኪዳን ብሉይ ኪዳን ባይኖርልኝ ኖሮ አስገድለሽኝ ነበር"፡፡

ከዚያ በኃላ ሰውዬው በሰፈሩ ተፈርቶና ተከብሮ ኖረ፡፡ ይህ ለመነሻ ያቀረብኩት ታሪክ በገሃዱ ዓለም የሚፈጸም እውነተኛ ተግባር ሲሆን ዛሬም ሀገራችን ኢትዮጵያ ያለችበትን ሁኔታ የሚገልጽ ይመስለኛል፡፡ መንግስት ሆደ ሰፊ ሆኖ ክፋትን በክፋት ከማሸነፍ ይልቅ ለክፎች እና ለተንኮለኞች በጎ መስራት እና አውቀው በድፍረት ሳያውቁ በስህተት ክፋትና ተንኮልን ወንጀልና ዝርፊያን ስራቸው ያደረጉት አጥፊዎችን ለማስተማር እና ለመመለስ የሄደበት መንገድና አያያዝ አዲስ አስተሳሰብ እንደ መንግስት ተገቢ ቢሆንም ተጎጂ የሆነው ሕዝብ ግን ወንጀለኞች ተገቢዉን ቅጣት ለምን አይሰጣቸውም? በማለት ያማርራል፡፡ የቀደሙት መንግሥታት የሄዱበትን መንገድ እና አያያዝ በማወዳደርም በመንግስት ላይ ቅሬታ ሲያሰሙ ይስተዋላል ፡፡

ስለሆነም ጠቅላይ ሚኒስተር ዐብይ አህመድ ከተለመደው የሀገራችን አካሄድ ወጣ በማለት አዲስ አስተሳሰብ እና ለውጥ ለማምጣት በያዙት የፍቅርና ይቅርታን መንገድ "ከቂም በቀልና ከክፋት ወጥተን በቅንነት ሰርተን ሰዉ ሁሉ ሳይበላለጥ ያለማዳላት በትጋት ከሰራን ልንለወጥና ልናድግ እንችላለን" የሚል እምነት እና ተስፋ በመያዝ እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ይሁን እንጅ በምድርም ሆነ በሰማይ በግለሰብም



ሆነ በቤተሰብ በሀገርም ሆነ በአለማቀፍ ማህበረሰብ ዘንድ ሊከበር የሚገባዉና የምንተዳደርበት ህግ ከሌለ ለመኖር እንቸገራለን ፡፡ ስለሆነም መብትና ግዴታ ሳይነጣጠሉ በእኩልነት በየትኛዉም ስፍራና ቦታ ሊከበሩ ይገባል፡፡ የዚህ ዋና አስከባሪ ሀይል ደግሞ መንግሥት መሆኑ ግድ ነዉ፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አህመድ ግን የአዲስ ኪዳንን መርሆዎች ላይ ብቻ ያተኮሩ ይመስላል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትራችን ያመጡልን "የመደመር ፍልስፍና" በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ቀድሞም ቢሆን መደመር በህብረተሰባችን ዘንድ የነበረን እሴት ሀገራዊ በሆነ መልኩ ያቀረቡበት ሲሆን ለምሳሌ፡- እድር፣ እቁብ ፣ ጉዛ(ደቦ) የመሳሰሉት ማህበራዊ እሴቶቻችን የመደመር እሳቤዎች ውጤት ናቸው፡፡ ሀዘን እና ደስታችንን በጋራ የምናወጣበት እድሮቻችን የኢኮኖሚየዊ ችግሮቻችንን ተባብረን የምንቀርፍባቸው ሥርዓቶች የመደመር አካሎች ናቸው፡፡ እነዚህን በጎ እሴቶቻችንን በሰፊው በማሳደግ እና በማበልጸግ ሀገራችንን እና ህዝቧን ለማሳደግ እና ለማበልጸግ የመደመርን ፍልስፍና ማቅረባቸው የሚደነቅ ሲሆን፣ እኛም ይህንን የተቀደሰ ዓላማ በበጎ በማየት ለመለወጥ መትጋት ይኖርብናል፡፡ ነገር ግን አሁን ባለዉ የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ፍቅርንና ይቅርታን ብቻ የሚያውጀውን አዲስ ኪዳንን መከተሉ የሚያዋጣ አይመስለኝም የብሉይ ኪዳንን ሕግጋት ከአዲስ ኪዳን ጋር ሊተገብሩ ይገባል፡፡ ካልሆነ ተንኮለኞች እና ሴረኞች እየገነኑ የሕዝቡን ምሬትና ለቅሶ እየበዛ ሲሄድ የለውጡ ጉዞ መደናቀፉ አይቀርም፡፡

የብሉይ ኪዳን ሕጎች ለግፈኞች እና ለወንጀለኞች መፍትሔ የሚሰጥ ሌላውንም የሚያስተምር ቁርጠኛ ሕግ ነው፡፡ ይህንን ሕግ ሙሴ ሲያወጣ በህዝቡ ውስጥ ሰላምን በመንሳት ለእስራኤል ሕዝብ ትልቅ ፈተና ሆነው ይበጠብጡ የነበሩ ወንጀለኞች እና ግፈኞች እየተበራከቱ በመምጣታቸው ሕዝቡም በመማረሩ ሙሴም የእስራኤልን ሕዝብ በተገቢው መንገድ መርቶ ወደ ቅድስት ሀገር የሚያደርገውን ጉዞ የሚያደናቅፍ መሆኑን በመረዳቱ ነው፡፡ በመተግበርም ለዓላማው መሳካት ቁርጠኛ እርምጃዎችን በመውሰድ የነጻ መውጣት ጉዞውን አስቀጥሎ በመጨረሻ ለማሳካት ችሏል ፡፡ ዛሬም ሀገራችንና ሕዝባችን ያለፈውን ሥርዓት አንገፍግፎት ታግሎ ከጣለ በኋላ ለመበልፀግ እና ለማደግ ትልቅ ራዕይ እና ተስፋ ይዞ የተነሳ ቢሆንም ይህ ራዕይ እንዳይሳካ ዛሬም ሀገርና ሕዝብን የሚያምሱ የጥፋት መልክተኞች ቀን ከሌሊት በመስራት ላይ ይገኛሉ ፡፡ በነዚህ የጥፋት ኃይሎች ብዙ ወገኖቻችን ተጎድተዋል ፤ የሀገር ኢኮኖሚ ተጎድቷል ፤ ብዙ ሕዝብ በፍርሃት እና በሰቀቀን ለመኖር ተገዷል ፤ የብዙ ዘመናት ልፋትና ድካም የፈሰሰበት የዜጎች ጥሪት እየተቀማና እየተዘረፈ ወድሟል ፡፡ ከሀገራችን ባህልና ወግ የወጡ እጅግ አፀያፊ ተግባራትን በየቦታው ማየት የተለመደም ሆኗል፡፡ ይህንን የተሸናፊዎች አስተሳሰብ እና ተግባር እንደ ጀግንነት የሚያወድሱ ሚዲያዎች እና ቡድኖች ያለእፍረት በየአደባባዩ ሲናገሩ መስማት አታክቷል፡፡ እነዚህን ቡድኖች እና ግለሰቦች "ሀይ" የሚላቸው ሲጠፋ ሕዝባችን ተስፋ የመቁረጥ እና ለተሸናፊዎች የመገዛት ዝንባሌዎች እያሳየም ይመስላል፡፡

ስለሆነም ጠቅላይ ሚኒስተር ዶክተር ዐብይ አህመድ የብሉይ ኪዳንን ሕጎች የመተግበሪያ ጊዜዎት አሁን መሆኑን ይረዱሉ፡፡ ያለበለዚያ ሀገርዎ እና ሕዝቦትን በሁለንተናዊ መልኩ ነፃ ለማውጣት እና ለማሳደግ ቃል የገቡትን እንዲሁም እርስዎን አምኖ ከፍተኛ ድጋፍ የሰጥዎትን ህዝብ አመኔታ የሚያሳጣ ከመሆኑም በላይ ከፍታ ላይ የሚያወጣ አምላክ ነውና ሁሉንም መልክ ማስያዝ ካልቻሉ የተሰጥዎትን አደራ ለማሳካት እክል ይገጥሞዎቷል፡፡ ስለሆነም ክብርነትዎ በዚህ ወሳኝ ሰዓት እንደ ሙሴ ቁርጠኛ በመሆን የአዲስ ኪዳንን ሕግ ከብሉይ ኪዳን ሕግ ጋር አጣምረው በመተግበር እንደሰውዬው እራስዎንም ሆነ ሀገርና እና ሕዝብን አስከብረው የመምራት ግዴታ ያለብዎት መሆኑን ልብ ሊሉት ይገባል፡፡

ቸር ይግጠመን!

# መንግሥትና ሕዝብ በ"እኛ ዘመን"



ቀጸላ ክፍሌ

ሀብታሙ አለባቸው "ታላቁ ተቃርኖ" በተሰኘው ጥናታዊ መጽሐፉ አራት የሥነ መንግሥት አወቃቀር ዓይነቶች እንዳሉ ይጠቁማል፡፡ ይኼውም "ጠንካራ መንግሥት እና ደካማ ሕዝብ" ፤ "ደካማ ሕዝብ እና ጠንካራ መንግሥት" ፤ "ደካማ መንግሥት እና ደካማ ሕዝብ" እንዲሁም "ጠንካራ ሕዝብ እና ጠንካራ መንግሥት" በሚል ነበር የመደበው፡፡

ሀብታሙ በዚህ አጠቃሎው የኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግሥት በየትኛው የሥነ መንግሥት አወቃቀር ሥር ሊካተት እንደሚችል አልጠቆመም፡፡ ሆኖም ግን ይህን ጥናታዊ መጽሐፍ ያነበበ ሰው "እውን የኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግሥት ምድቡ ከየትኛው ነው?" የሚል ጥያቄ በልቡ ማጫሩ አይቀሬ ነው፡፡

ከዚህ አንጻር የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥንካሬ ለመፈተሽ ያለፈውን የዘመናት አብሮነት ማየቱ ከተቻለም ጠልቆ መመርመሩ መልካም ነው፡፡ ይህ ሕዝብ በርካታ ዘመናትን ከፖለቲካዊ ጠገግ በዘለለ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስርን አዳብሮ የኖረ ስለመሆኑ ብዙ ማሳያዎችን ማቅረብ ይቻላል፡፡ ከመልሶ አንድነት (reunification) በፊት በዘመነ መሳፍንትም ሆነ ከዚያ ቀደም ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ትስስሮች ስለመኖራቸው የቋንቋ ውርርን አንዱና ዓብይ ማሳያ አድርጎ ማቅረብ ይቻላል፡፡ በኢትዮጵያ ከሚነገሩ ሰማንያ በላይ ቋንቋች ውስጥ አብዛኞቹ ሃያ በመቶ በሚሆነው የቃል ክፍላቸው ተመሳስሎሽ ይስተዋልባቸዋል፡፡ በተለይ የኢትዮጵያን ቋንቋ በጥልቀት ያጠኑት እነ ቸሩሊ ሳይቀሩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ያላቸውን ከፍተኛ ቃላዊና ሰዋሰዋዊ ምስስሎሽ ሳይገልጹ አላለፉም፡፡ ለምሳሌ በአማርኛና በጉራጌ ቋንቋዎች መካከል ያለው የአወቃቀርና የቃላት ውርርስ፤ ዝም ብሎ የመጣ ሳይሆን ህዝቦች ባላቸው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስር ሳቢያ አንዱ በአንዱ ላይ የፈጠረው ተጽዕኖ ውጤቶች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል በአማርኛና በኦሮምኛ ቋንቋ መካከል ያለው የቃላት ውርርስና ሰዋስዋዊ የአወቃቀር አንድነት ከፍ ሲል ከተጠቀሰው ተጽዕኖ ተነጥሎ የሚታይ አይደለም፡፡ በተለይ የአማርኛና የኦሮምኛ ቋንቋን ምስስሎሽ በተመለከተ የፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ "የአማራና የኦሮሞ እውነተኛው የዘር ምንጭ" የሚለውን መጽሐፍ ማንበብ ሰፊ መረዳት ይለግሳል፡፡ በሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች መካከል የሚታየው ሃቅም ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡

ሌላው በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚታየው አብሮነት የባህል ተጋሮት ወይም ምስስሎሽ ነው፡፡ ይህ በግልጽ እንደሚታወቀው ሁሉም የሀገሪቱ ህዝቦች ለማለት በሚያስደፍር መልኩ ተቀራራቢ የሆነ የአመጋገብ ፣ የአለባበስና መሰል ባህላዊ ክንውኖች ያላቸው ለመሆናቸው ማስረጃ ሆኖ የሚቀርብ ነው፡፡ ለምሳሌ በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል የሚገኝ አንድ ግለሰብ ከጥጥ የተሰራውን ሸማ ለብሶ መውጣት ብርቅ አይሆንበትም፡፡ ምክንያቱም በየትኛውም የሀገሪቱ ግዛት ውስጥ ይህ ባህላዊ ልብስ የወል መገለጫ ስለሆነ ነው፡፡ በሌላ በኩል የአመጋገብ ሥርዓትም እንዲሁ አንዱ ማሳያ ሲሆን በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል ውስጥ የየትኛውም ዕምነት ተከታዮች የሚመገቧቸው የእንስሳት ተዋጽኦ የሆኑ ሥጋ ተኮር ምግቦች ተመሳሳይ ናቸዉ፡፡ ለምሳሌ ኬንያ ወይም ሱዳን ውስጥ ያለችግር የሚበሉት የአዕዋፍ ዝርያዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ግን ከዶሮና ከቆቅ ውጪ ንክች አይደርጉም፡፡ ይህ ለምን ሆነ የሚል ጠያቂ ካለ መልሱ ያው "በአብሮነት የገነባነውና ይዘን የመጣነው ታሪካችን ስለሆነ ነው" የሚል ይሆናል፡፡ ሕዝባችን በማህበራዊ ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚያዊ ትስስሩም ከዚህ የተለየ መልክና ባህሪ የለውም፡፡ ለምሳሌ ጅማና ከፋ ያመረተውን ልዩ ቡና ድፍን ሀገሪቱ ሲጠጣ፣ ጎጃም ያመረተው ማርና ጤፍም እንዲሁ በድፍን ኢትዮጵያ ሲዳረስ የነበረው ገና ዘመናዊት ኢትዮጵያ ሳትፈጠርና የዘመነ የንግድ ሥረዓት ሳይፈጠር ነው፡፡

ሌላው ሊነሳ የሚገባው ነጥብ በፖለቲካው ዘርፍ ያለው የሕዝብ አብሮነት ነው፡፡ በፖለቲካው ዘርፍ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያለው አንድነት ከፍ ሲል ከተጠቀሱት ብዙም የራቀ አይደለም፡፡ ለምሳሌ በተለያዩ ወቅቶች ሀገሪቱ ለጠላት ወረራ ስትጋለጥ ህዝቡ በሕብረት በመቆም ለዘመናት ክብሩን አስጠብቆ መቆየት ችሏል፡፡ ለዚህም ከጥንታዊው የፋርስ፣ የሮማና የቱርክ ወረራ ጀምሮ እስከ ትላንቱ አድዋ ድረስ ያለውን ጀብዳዊ ተግባር ማስታወስ በቂ ነው፡፡

በአጠቃላይ ከፍ ሲል ተዘርዝረው ካየናቸው የአብሮነትና የአንድነት ታሪኮች በመነሳት በየትኛውም ዘመን የኢትዮጵያ ሕዝብ በሥነ መንግሥት አጥኚዎች "ጠንካራ ሕዝብ" ከሚባሉት መሃል እንደሚመደብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በአንጻሩ ግን በተለያዩ ወቅቶች ጠንካራ ላልነው ሕዝባችን ጥንካሬና ድክመት የቀላቀለባቸው መንግሥታት እንደነበሩ መናገር ይቻላል፡፡ የመንግሥት ጥንካሬና ድክመት ከሚለይባቸው መመዘኛዎች መካከል ጥቂቶቹ ደግሞ፡- የውጭ ጉዳይና የሀገር ውስጥ ፖሊሲ አቀራረጽና አፈጻጸም ፤ በማንኛውም መልኩ በሀገር ውስጥም ይሁን ከውጭ በሚነሱ የሀገር ሉዓላዊነትን የሚፈታተኑ ጥያቄዎች ዙሪያ የሚያሳየው አቋም እንዲሁም ሕግ የማስከበርና የዜጎችን መብት በመጠበቅ ዙሪያ ያለው የኃይል የበላይነት ይጠቀሳሉ፡፡ በነዚህ መመዘኛዎች መሰረት ኢትዮጵያ በታሪኳ በርካታ ጠንካራ መንግሥታት እንደገጠሟት በግርድፉ ጠቁሞ ማለፍ ይቻላል፡፡ ከዘመነ መሳፍንት በፊት ያሉት ቀርቶ በዘመናዊት የኢትዮጵያ ታሪክ እንኳ የነበሩት ሥርዓቶች ቢታዩ በብዙ መልኩ ጠንካራ መንግሥታት ተከስተው እንደነበር መካድ አይቻልም፡፡ የአጼ ቴዎድሮስ፣ የአጼ ዮሐንስና የአጼ ምኒልክ ጎልተው የሚወጡና በቀላሉ የማይደፈር መንግሥትን ለመፍጠር የሄዱበትን ርቀት ማስታወስ በቂ ነው፡፡ ነገሥታቱን ሁሉ ሊባል በሚችል ደረጃ የሚያመሳስላቸው ነገር ቢኖን ለሀገሪቱ ሉዓላዊ ጥንካሬ በሃያላኑ ዓለማት ጭምር ተፈትነው ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ መሆናቸው ነው፡፡ እዚህ ጋር ውስጣዊ ተቃርኗቸውን ለመፍታት የሔዱበት መንገድ ግን ልዩነት እንደነበረው መዘንጋት አይጠበቅብንም፡፡

በርካታ ምሁራን እንደሚስማሙበት አጼ ቴዎድሮስ ውስጣዊ ችግሮችን በኃይል ለመፍታት ቢሞክሩም፣ ለውጭ ኃይሎች ግን ስጋት መሆናቸው እሙን ነው፡፡ (በዘመኑ አለ የተባለው የእንግሊዝ ሰራዊት ለአንድ አፍሪካዊ ንጉሥ መቅደላ ድረስ መምጣቱን ያስታውሷል)

አጼ ዮሐንስም ውስጣዊ ተቃርኖን ለመፍታትና የሀገር አንድነትን ለማምጣት "አንድ ሃይማኖት አንድ ሀገር" ብለው መነሳታቸው ኋላ ላይ ዳፋ ቢሆንባቸውም በወቅቱ ግን በመሰላቸው መንገድ ሀገራቸውን በመገንባት በውጭ ኃይሎች የማትደፈር መሆኗን ለማሳየት ሞክረዋል፡፡

በአንጻሩ አጼ ምኒሊክ ያለፉ ነገሥታትን ድክመት ከግምት በማስገባት በዛሬው አጠራር ህብረብሔራዊነትን ያነገበች ዘመናዊት ሀገርን ገንብተው ለተከታታይ ትውልድ ማውረስ ችለዋል፡፡ አልፎም አድዋ ላይ የማይነጥፈውን ታላቅ ገድል በመሥራታቸው እንደ ንጉሥ በዓለም ዘንድ ከፍተኛ ክብርና ሞገስንመ እንደ መንግሥት ደግሞ የኢትዮጵያን ጠንካራ ሥነ መንግሥት ማሳያ ሆኗል፡፡

ቀጥሎ የመጣው የልጅ እያሱ መንግሥትም ቢሆን ምንም እንኳ የሥልጣን ዕድሜው አጭር ቢሆንም፣ ጠንካራ አደረጃጀት ለመፍጠር ያለመና ቀደምት የአባቶችን ይዞታ ለመመለስ ሲታትር በውስጥ ሴራ ተንኮታኩቶ ያለጊዜው የተቀጨ አገዛዝ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ግን ዙሪያዋን ከበዋት በነበሩት ቅኝ ገዢዎችም ሆነ በምዕራባውያን ዘንድ የተናቀ መንግሥት እንዳልነበር መግለጽ ይቻላል፡፡

ሌላው ገናና የነበረውና ረጅም ዓመታትን የኢትዮጵያ መንግሥት ሆኖ የቆየው የአጼ ኃ/ስላሴ ሥርዓተ ማኅበር ነው፡፡ ይህ ዘመን ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ደምቃ የታየችበትና የተከበረችበት ነበር፡፡ በጊዜው ከአጼ ምኒልክ የቀጠለው ዘመናዊነት በሀገሪቱ ላይ በገሀድ የተገለጠበት ወቅት ነበር፡፡ ስለዚህ በድምሩ የአጼ ኃ/ስላሴ ዘመነ መንግሥት በውጭም በውስጥም ፖሊሲው የተቀባይነት ደረጃው ከፍ ያለና ጠንካራ መንግሥት ስለመሆኑ በበርካቶች ዘንድ እሙንነትን ያተረፈ ነው፡፡

የመጨረሻዎቹ የደርግና የ[ቀዳማዊ]ኢህአዴግ ሥርዓቶችም ቢሆኑ አንባገነንነት ቁርጥ ያለ መለያቸው ቢሆንም በውጭም በውስጥም ጉዳይ ላይ ያላቸው አቋም ግን የአንድ ጠንካራ መንግሥት ባህሪ ነው ብሎ ማስቀመጥ ይቻላል(ምንም እንኳ ውስጣዊ ምዕክልናቸው በአንድነት እና በልዩነት ፖለቲካ የተቀነበበ ቢሆንም)፡፡

በአጠቃላይ በዘመናዊት ኢትዮጵያ ታሪክ እስካሁን ከታዩት መንግሥታት ውስጥ የኮ/ል ዐቢይ አሕመድ መንግሥት ፍጹም ደካማ ነገር ግን በጠንካራ ሕዝብ ትከሻ ላይ የተጫነ ስለመሆኑ ያለፉትን ሁለት ዓመታት ዞሮ ማየት በቂ ነው፡፡ በክልሎች ላይ ካለው የቁጥጥር ማነስ፣ ከኤርትራ ጋር ባለው መርህ አልባ ግንኙነት፣ የበርካታ ሊብራል መንግሥታት በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ባለቤት መሆን፣ በሕዳሴው ግድብና በዓባይ ውሃ ላይ ያለው የላላ አቋምና አካሄድ፣ ወዘተ… ማሳያ ተደርገው ሊቆጠሩ የሚችሉ ናቸው፡፡ ■



ብሩክ መኮንን

# የስምጥ ሸለቆ መብረቆች





ከ83 ዓመት በፊት በዚህ ሳምንት ሀገራችን በግፍ የወረረው የፋሽስት ኢጣልያ ጦር ሚያዚያ 27 ቀን 1928 አዲስ አበባንና አብዛኛውን የሰሜኑን ኢትዮጵያ ክፍል ተቆጣጠረ እንጂ ለወራት ወደ ደቡቡ የሀገራችን ክፍል ለመዝለቅ አልቻለም ነበር።

ለዚህ ደሞ ምክንያ ብዙዎች "የስምጥ ሸለቆ መብረቆች" በሚል ስያሜ የሰጧቸው በደቡብ ጦር ግንባር የኢትዮጵያን ጦር ይመሩ የነበሩ ከ83 ዓመት በፊት በዚህ ሰሞን ከማያልፈው አለም የሚያልፈው ታሪክ ሰርተው ያለፉ ጀግኖች በፈፀሙት ተጋድሎ እንደሆነ ይነገራል።

ከማይጨው ሽንፈት በኋላ ንጉሰነገስቱ በሀገራቸውና በሕዝባቸው ላይ የተፈፀመውን ግፍና በደል ለሊግ ኦፍ ኔሽን ለማሳወቅ በሚል ምክንት ቤተሰባቸውን ይዘው ወደ እንግሊዝ ከተሰደዱ በኋላ እምቢ ለሀገሬ እምቢ ለነፃነቴ ያለውን ተዋጊ ጦር እየመሩ ይፋለሙ የነበሩ ኢትዮጵያውያን የጦር አዛዦች ለኢጣሊያ የራስ ምታት ሆነው ነበር የከረሙት።

የሥምጥ ሸለቆ መብረቆች የተባሉት ራስ ደስታ ዳምጠው ደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪ ደጃዝማች በየነ መርዕድ ደጃዝማች በዛብህ ስለሺና ፊታውራሪ ሽመልስ ሀብቴ ናቸው።

የስምጥሸለቆዎቹመብረቆችኢትዮጵያውያን የጦር አበጋዞች ከነሰራዊታቸው በሠላም እጃቸውን ለኢጣልያ እንዲሰጡ የኢጣልያ የጦር አዛዦች ልመና ማስጠንቀቂያ ዛቻ የተቀላቀለባቸው ደብዳቤዎች በተደጋጋሚ ቢሰዱላቸውም ሁሉም በአንድ ድምፅ ይህ የማይሞከር ነው የሚል ምላሽ በመስጠት ከጠላት ጦር ጋራ መፋለማቸውን ቀጥለው ነበር።

በሕዳር ወር 1929 የመጀመሪያ ሳምንት መገባደጃ ከስምጥ ሸለቆ መብረቆቹ አንዱ ደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪ የተመራ ጦር ወደ መኃል ሀገር ለመዝለቅ የነቃነቀ የኢጣልያ ጦር ጋራ ውጊያ ገጥሞ ከአንድ መቶ በላይ የኢጣልያ ወታደሮችን አንድ ጄነራል ገደሎ በጥቃቱ ለማምለት በአካባቢው ባለ ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ገብቶ የተሸሸገ ለኢጣል ያደረ የባንዳ ጦርን የገባበ ገብቶ በመምታት ከፍተኛ ጉዳት አድርሶ ነበር።

በኢትዮጵያውያኑ ተዋጊዎች ክፉኛ የተመታው የኢጣልያ ጦር አዛዥ ጄነራል ጀሎዞ "የተፈሪ ኬላን በር ጥሼ ወደመሐል ሀገር ወደ ይርጋለም ማለፍ አልቻልኩም ስለዚህ የተረፉኝን ወታደሮች ይገፔ ወደ ኋላ ማፈግፈግ ግድ ሆኖብኛል" ሲል ለበላይ አዛዦቹ መርልክት ለማስተላፍ ተገዶ ነበር።

ይኼው መልዕክት የደረሳቸው የኢጣልያ ጦር አዛዞች በአየር ኃይሉ በመታገዝ ለማፈግፈግ ለተገደደው ጦራቸው ተጨማሪ ጦር ስንቅና ትጥቅ በማቅረብ በቀናት ውስጥ ተደራጅቶ ወደ ይርጋለም እንዳያልፍ የብረት አጥር የሆነበት የኢትዮጵያውኑ ተዋጊዎች ላይ መልሶ ማጥቃት እንዲሰነዘር አደረጉ።

የስምጥ ሸለቆ መብረቆቹ እነደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪ መልሶ ማጥቃት በከፈተባቸው የኢጣልያ ጦር ጋራ ለአራት ተከታታይ ቀናት የዘለቀ እልህ አስጨራሽ ፍልሚያ አድርገው በጠላት ጦር ላይ ከፍተኛ ጉዳት ቢያደርሱም በገጠማቸው የስንቅና ትጥቅ እጥረት ምክንያት ሊቀዳት የተቃረቡት ድል ከእጃቸው ወጣ በዚያው ሰሞን ከስምጥ ሸለቆ መብረቆቹ አንዱ ራስ ደስታ ዳምጠው የሚያዙት ጦር ከነጋሌ ጀምሮ ደሎ ድረስ ያለውን አከባቢ ለመቆጣጠር 400 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለውን ርቀት በእግሩ ለመጓዝ ተገዶ ነበር።

በራስ ደስታ ዳምጠው የሚመራው ጦር 400 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለውን ጉዞ በሚያደርግበት ጊዜ ለአውሮፕላን ጥቃት የተጋለጠ ስለነበረ የፋሽስት የጦር አውሮፕላን ቦንብ እየተደበደበ ነበር፡፡ ከጥቃቱ የተረፈው ጦርም በኢትዮጵያና በሱማሊያ ድንበር ላይ ደርሶ ተሠለፈ።

የዚህ የራስ ደስታ ዳምጠው የሚመራው ጦር እንቅስቃሴ መረጃ የደረሰው ማርሻል ባድሊዮ በቴሌግራም ቁጥር 1897 ላሩዶልፈ ግራዚያኒ " የኢትዮጵያ ጦር ዋና ኃይል ወደ እናንተ መጓዝ ጀመረ። በእጅህ የሚገኘውን ማንኛውንም አይነት መሳሪያ በቦብንብና በመርዝ ሁሉ መዋጋት አለብህ ከዚህ ኃይል ሌላ የሚያጠቃህ ያለ አይመስለኝም፡፡ እርግጠኛ ነኝ እንደ እኔ ከሆነ ብታስብበት የሚከፋ አይመስለኝም።" የሚል መልዕክት ሰደደለት።

ከሕዳር 1929 ጀምሮ ለአንዱ ወር በሩዶልፎ ግራዚያኒ የሚታዘዘው የኢጣልያ ጦር ጀሎ ገብቶ ጦሩን ሊጠናክር ቀርቶ ዝግጅቱን ከጨረሰ በኋላ ወደፊት በመግባት ጥር 1 ቀን 1929 ሻንቆ በተባለ ስፍራ ከስምጥ ሸለቆ መብረቆቹ አንዱ ከሆኑት ደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪ የሚታዘዝ ጦር ጋራ ውጊያ ገጠመ።

በተደረገው ውጊያ ኢትዮጵያውያኑ በጠላት



እግረኛ ጦር ላይ ከፍተኛ ጉዳት ቢያደርሱም የጠላት አውሮፕላን የሚያዘንበውን ቦንብና መርዝ ግን ለመቋቋም ባለመቻላቸው አርቤጎን በመልቀቅ ወደ ባሌ በማፈግፈግ ላይ እያለም ከጠላት ጦር ጋራ መፋለሙን አላቆሙም ነበር፡፡

ከሶስት ቀናት በኋላ ጥር 4 ቀን 1929 "የስምጥ ሸለቆዎቹ መብረቆች" የሚመሩት ጦር የመጀመሪያውን ታላቅ ውጊየ ገናሌ ዶሪ ላይ ተካሄደ፡፡

በዚያን ቀን ውጊያ የኢጣልያ ጦር በምድር በታንክና በዘመናዊ ጦር መሳሪያ ከሚያደርገው ፍልሚያ በተጨማሪ አንድ ሺኅ ሰባት መቶ ኪሎ የሚመንዝዝን ቦንብና የመርዝ ጋዝ በኢትዮጵያ ጦር ላይ አዘነቡበት፡፡

በገናሌ ዶሪ የተካሄደው ከባድ መስዋዕትነት በተከፈለበት በዚህ ፍልሚያ በፅናት የተዋጋው የኢትዮጵያ ጦር ወደተለያዩ አቅጣጫዎች ለማፈግፈግ ቢገደድም በአከባቢው ከመሸገው የኢጣልያ ጦር ጋራ መፋለሙን ለቀናት ቀጥሎ ነበር፡፡

በወቅቱ የኢጣልያ ጦር የኢትዮጵያ ጦር ውሃ እንዳያገኝ የጉድጓድ ውሃና ወንዝ ካለበት ቦታ እየመሸገ ስለተቀመጠ የኢትዮጵያ ሠራዊት ውሃ እንዳያገኝ አደረገው፡፡

የኢትዮጵያ ሠራዊት ውሃ ለመቅዳትና ለመጠጣት ሲጠጋ በስፍራው የመሸገው የኢጣልያ ጦር በመትረየስ ይፈጀው ጀመር ግድያው ሰውን ብቻ ሳይሆን እንስሳትም ውሃ ሲጠጡ ይገደሉ ነበር፡፡ ከላይ ደግሞ የኢጣልያ አየር ኃይል አውሮፕላኖች በመመላለስ በመርዝ ጭስ ይፈጁት ነበር፡፡

ጥር 20 ቀን 1929 ራስ ደስታ ዳምጠው፣ ደጃዝማች ገብረማርያም ጋር ደጃዝማች በየነ መርዕድ ደጃዝማች በዛብህ ስለሺ እና ፊታውራ ሽመልስ ሀብቴ ጦራቸውን በማቀዳጀት የስምጥ ሸለቆው መብረቆች በጋራ መድፎቻቸውን ጠምደው ከኢጣልያ ጦር ጋራ ከባድ ፍልሚያ አደረጉ፡፡

ከስምጥ ሸለቆ መብረቆች አንደኛው ደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪ ቀደም ባለው ውጊያ ላይ በጥይት ተመተው ቁስሉ አመርቅዞ እየጠዘጠዘ እያሰቃያቸውም ሕመሙም ተቋቁመው መትረየሳቸውን እያንፋቀቁ ሲዋጉ ዋሉ፡፡

በእለቱ ውጊያ በጠላት ጦር ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶ የጠላት ጦር የመሸገባቸው ዋና ዋና ምሽጎችን እንዲለቅ በመገደዱ ኢትዮጵያውያን ተዋጊዎች ገብተውበት የነበረውን የውጊያ ቀለበት ሰብረው እንዲወጡ ማድረግ የታቸለ ሲሆን በዚህም በወገን ጦር ላይ ሊደርስ የነበረው ጉዳት እንዲቀንስ አድርገዋል፡፡

በስምጥ ሸለቆዎቹ መብረቆቹ የሚመራው የኢትዮጵያ ጦር በርካታ ድሎችን ቢያስመዘግብም የፋሺስት ኢጣልያ የጦር አውሮፕላኖች የሚያዘንብቡትን ቦንብና የመርዝ ጋዝ ጭስ መቋቋም ስለተሳነው አከባቢው ለቆ ወደ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ለማፈግፈግ ተገደደ፡፡

በማፈግፈግ ላይ ያለው ስንቁን የጨረሰው የስምጥ ሸለቆ መብረቆቹ የሚታዘዘው ጦር ለቀናት በዱር በገደሉ እየተሸሎከሎከ ወደ ምዕራብ ሸዋ ለመድረስ እየተጓዘ እያለም ከጠላት ጦር ጋራ መፋለሙን አላቆመም ነበር፡፡

የካቲት 10 ቀን 1929 ዓ.ም ወደ ቡታጅራ በሚወስደው መንገድ አቅራቢያ ሠፈር የነበረ የኢጣልያ ጦር ላይ በደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪ የሚመራው ጦር በከፈተው ማጥቃት ከፍተኛ ጉዳት አደረሰ፡፡

ይህ በስምጥ ሸለቆ መብረቆች የተቀናጀ ማጥቃት ስትራቴጂ ያልተጠበቀ የሆኑበትና ከባድ ጉዳት የደረሰበት የኢጣልያ ጦር በእልህ ለበቀል በመነሳት በወሰደው መልሶ ማጥቃት እርምጃ የስምጥ ሸለቆው መብረቆች ጦር ጋራ ከባድ ፍልሚያ ተደረገ ፡፡

የጠላት ጦር ያለ የሌለ ኃይሉን በመጠቀም በከፈተው ማጥቃት ኢትዮጵያዊያ ተዋጊዎች ሊቋቋሙት አልቻሉም፡፡

የኃይል አሰላለፉን በሚገባ ያጤኑት የስምጥ ሸለቆዎቹ መብረቆች ከተረፋቸው አነስተኛ ኃይል ጋራ ወደተያየ አቅጣጫ ማፈግፈግ ወሰኑ፡፡

ራስ ደስታ ዳምጠው ከጥቂት ተከታዮቻቸውና ወታደሮቻቸው ጋራ ወደ መስቃን አቀኑ፡፡

ደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪን አጅቦ ቀኝ አዝማች ኦርጋ ጋሪ ሻለቃ በቀለ ወያ፣ ቀኝአዝማች በየነ ጉደታ ቀሪው ጦር ወደ ማረቆ አቅጣጫ ለመሸሽ ተገደደ፡፡

ቁስላቸው ያልጠገገላቸው በአደዋ በሰገሌ ጦር ላይ የተፋለሙት የስምጥ ሸለቆ መብረቆቹ አንዱ ደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪ ጦራቸራ እግር በእግር እየተከታተለ ለመደምሰስ የሚጣደፈው የኢጣልያ ቶር ጎጌቲ ገብርኤል ከብቦ አላሳልፍ አላቸው፡፡

ደጃዝማች ገብረማርያም አነስተኛ ቁጥር ያለው ተዋጊዎቻቸውን በማስተባበር ጠላትን ጦር እየመከቱ ሚልኮ ማርያም ደረሱ፡፡

የኢጣልያ ጦር ለኢጣልያ ያደሩ ባንዶች የተጠናከረ እንቅስቃሴን ያስተዋሉት ጀግናው የ63 ዓመቱ ደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪ ቤተሰቦቻውን ወደ አገምጃ እንዲሄዱ ካደረጉ በኋላ ለተከታዮቻቸው

"ዛሬ ሰርጌ ነው በውድ አገራችን ኢትዮጵያና ለሰንደቅ አላማችን ግዳጄን ፈፅሜ ሕይወቴን አሳልፋሁ፡፡ ከዚሁ እልፍ አልልም የመጨረሻ ትግሌ ዛሬ የሚጠናቀቅ ይመስለኛል፡፡

ሩጫዬን አበቃለሁ ጠላት እጄን አይጨብጥም እንደማየው ጠላት ዙሪያችንን ከብቦናል፡፡ በዛሬው ቀን በምናደርገው የሞት ሽረት ውጊያ መሳተፍ የማትችሉ ከአጠገቤ መለየት ትችላላችሁ፡፡

እኔ የቆሰለው እግሬ ሊያራምደኝ አይችልም ውጊያው እየተጠናከረ መሆኑን ስታውቁ ባመቻችሁ መንገድ ሁሉ ሾልካችሁ እስከወደቃችሁ ድረስ ባገራችሁ ጉራንጉር በወንዞቻሁ ሸለቆዎችና ዱር ገብታችሁ ተዋጉ እግዚአብሔር ይከተላችኋል ብለው ተናገሩ፡፡ ከሚሰናበቱት ጋራ መርቀው ከተለያዩ በኋላ ጉዞው እንዲቀጥል አዘዙ፡፡

የካቲት 13 ቀን 1929 ረፋድ ላይ ጀምሮ መንገድ ላይ አድፍጦ ሲጠብቃቸው ከነበረው የኢጣልያ ጦር ጋር ለሰዓታት በጀግንነት ሲዋጉ ከቆዩ በኃላ በጥይት ተመተው ወደቁ ከስምጥ ሸለቆ መብረቆች አንዱ ደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪ አባንጥቅ!

ሌሎቹ የስምጥ ሸለቆ መብረቆች ወደ መስቃን ከዚያም ወደ አገምጃ አቅጣጫ ማፈግፈጋውን ቀጥለው ነበር፡፡

በተለይ ሁለቱ የአፄ ኃይለስላሴ ልጆች ባለቤቶች ራስ ደስታ ዳምጠው ደጃዝማች በየነ መርዕድ ፊታውራ ሽመልስ ሀብቴ ተከታዮቻው በሀሩር በውሃ ጥም እየተሰቃዩ እንደጋይ የተባለ ስፍራ እንደደረሱ ለኢጣልያ ባደሩ ባንዳዎች በፋሽስት ጦር ባልደረቦች ትብብር ተማርከው ራስ ደስታ ዳምጠው ከዛፉ ላይ፡፡ የፊጢኝ ታስረው በጥይት ተደብድበው ሲገደሉ ሁለቱ ደጃዝማቾችም በጥይት ተደብድበው የካቲት 16 ቀን 1929 የዛሬ 83 ዓመት ለሀገራቸው ለነፃነታቸው ሲሉ ተሰው፡፡

የስምጥ ሸለቆዎቹ መብረቆች በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ምንም ዓይነት የዕዝ ሰንሰለት በሌለበት ስንቅና ትጥቅ የሚያቀርብ የደጀን ኃይል ሳይኖር ለሀገራቸው ነፃነት ሉዓላዊነት የሰሩትን ታሪክ ለማስታወስ በዚህ በመዲናችን በ1949 ሊሴ ገብረማርያም ትምህርት ቤት ለደጃዝማች ገብረማርያም ጋሪ ስም ተሰይሞላቸዋል፡፡

ለሌሎቹ የስምጥ ሸለቆ መብረቆች ለራስ ደስታ ዳምጠው ራስ ደስታ ዳምጠው ሆስፒታል ለዳጃዝማች በየነ መርዕድ በየነ መርዕድ ትምህርት ቤት ሽመልስ ሀብቴ ትምህርት ቤት በስማቸው ተሰይሞላቸው በታሪክ ፊት ለዘላለም ሕያው እንዲሆኑ ተደርገዋል፡፡ ዘላለማዊ ክብር ለስምጥ ሸለቆ መብረቆች ይሁን! ■

# የ25 ዓመቱ የሜሪጆይ ጉዞና ውጣ ውረድ

በሙሉጌታ አክሊሉ

ሲስተር ዘቢደር ዘውዴ የሜሪጆይ መስራችና ሥራ አስኪያጅ ናቸው፡፡ የሜሪጆይ ጥንስስ ከ25 ዓመት በፊት ነው፡፡ በ100 ልጆች የጀመረውና ዛሬ በ10 ከተሞች 42 ሺህ ሕፃናት፣ 10 ሺህ እናቶች፣ 4 ሺህ ወጣቶችንና 4 ሺህ በጎ ፍቃደኞችንና ከHIV ቫይረስ ጋር የሚኖሩ 500 ሰዎችን እየረዳ ይገኛል፡፡ ፍቃድ ካገኘ 25 ዓመታትን ያስቆጠረው ሜሪጆይ ከወጣቶች ማዕከል፣ ከቤተ መፃህፍትና ከክሊኒኮች እንዲሁም ከት/ቤቶች በተለያየ አገልግሎት ላይ የተሰማሩ ከ1.5 ሚሊዮን ሰው በላይ የሜሪጆይ አገልግሎት ተጠቃሚ አድርጓል፡፡

ሜሪጆይ በአንድ ቀበሌ የጀመረውን ሥራ ዛሬ ላይ በ122 ወረዳና ቀበሌዎች ውስጥ በ10 ከተማ ላይ እየሰራ ይገኛል፡፡ በወ/ሮ ሲ/ር ዘቢደር ተጠንስሶ 170 የሚሆኑ ቋሚ ሰራተኞች ያሉትና እያደገ የመጣ ድርጅት ነው፡፡ ሜሪጆይን ለመመስረት እንደመሪ ሥራ አስኪያጅዋ ሲስተር ዘቢደር ገለጻ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ጀምሮ ብዙ መናገር ባለመቻላቸው የሚሰሩት በአስተርጓሚ ነበር፡፡ ትምህርታቸውም በነርሲንግ ዲፕሎማ መሆኑን ያስታውሳሉ፡፡ ፈረንጆች በጎ አድራጎቱን ከጎበኙ በኂላ ለ8 ዓመታት በመላላክ ከዲፕሎማ እስከ ማስተርስ በፕሪስተን ዩኒቨርሲቲ ተምረው በመመረቅ አጠናቀዋል፡፡ በልምድ ደረጃም አሜሪካ፣ ፔሩ፣ ቦሊቪያ፣ ባንግዳላዬሽ፣ ሕንድ፣ ኤዥያ አገራት በመላክና ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በመሆን ልምድ እንዲወስዱ ድጋፍ በማድረግ በርካታ ድርጅቶች አሁን ላሉበት ደረጃ አስተዋኦ አድርገዋል፡፡ የእርሳቸውና የድርጅቱን አቅምም ገንብተዋል፡፡ ሜሪጆይ በተለይ ከአጠቃላይ የቦርድ ጉባኤና በጣም ግብረገብ ያላቸው ሰራተኞቻችው ትልቅ አስተዋፅኦ ማድረጋቸውን ሲስተር ዘቢደር ይናገራሉ፡፡

‹‹በኢትዮጵያ አዲስ አበባ ትልቁን ሥራ በ6 ክፍለ ከተሞች ላይ የሚሰራው ሜሪጆይ፣ ቢሾፍቱ ላይ ከ “Stele RMI” የተባለ ሕፃናት ላይ የሚሰራ የቢዝነስ ድርጅቶች ጋር 23 ለሚጠጉ ሕፃናቶች ት/ቤት ሰርተው 700 የሚጠጉ ሕፃናትን እየረዳ ይገኛል፡፡ ደቡብ ላይ 10 ከተማዎች ከUSAID Cordade የሚባል ድርጅት ‹ኢትዮጵያዊያን ለኢትዮጵያዊያ› ከተሰኙ ግለሰቦችና ከመንግሥትና የቢዝነስ ካምፓኒ ጋር የምንሰራው ሥራ አለ›› ብለዋል፡፡ ሜሪጆይ ትልቁ አዋሳ ላይ በኢትዮጵያውያን ብቻ ድጋፍ የተገነባው የአረጋውያን ማዕከሉም ተጠቃሽ ነው፡፡ ዲላ፣ ይርጋለም፣ አዋሣ ከተማ፣ አርባምንጭ፣ ሶዶ(ወላይታ)፣ ቡታጅራ፣ ሚዛን ተፈሪ፣ ሀዲያ(ሆሳዕና) ዱራሜ እያለ 10 ከተሞች ላይ እየሰሩ ነው፡፡

የሜሪጆይ ራዕይ “ከድህነት ነፃ የሆነ ብቁ ዜጋ አፍርቶ ማየት ነው” የሚል ነው፡፡ ተልዕኮዋቸው ደግሞ “የተቀነባበረ ልማት ለችግር የተጋለጡ ሰዎች ጋር መስራትና የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት” ላይ ነው፡፡ ስኬታቸው ደግሞ ከችግሩ አኳያ አናሳ ቢሆንም የሚከበሩበት ሥራ ኢትዮጵያውያን እንዲሰሩና ‹‹ዛሬ እኔ ያገባኛል›› የሚለውን ስሜት በመዝራቱ ላይ ትልቅ ሥራን ሰርተዋል፡፡ የዚህም ውጤት ነው የአረጋዊያኑ ማዕከሉ በኢትዮጵያዊነት ብቻ እንዲረዳ ያደረጉት፡፡ በየዓመቱ ከ10 ሚሊዮን ብር በላይ ከኢትዮጵያ የሚያሰባስቡበት መንገድ ትልቁ ስኬታቸው እንደሆነ ነው ያወቅነው፡፡ ምክንያቱም ‹‹ሁሌም የፈረንጆችን ብቻ እጅ ከማየት፣ እኛም ኢትዮጵያዊያኖች መስጠት እንችላለን›› የሚለውን ሥራ በመስራታቸው ከሜሪጆይ ጋር ተፈራርመው እስከ 1.5 ሚሊዮን ብር የሚሰጧቸው የውጭ አገር ካምፓኒዎች ተፈጥረዋል፡፡



የአሰራር ተሳትፎዋቸው ግልፅነትን ያማከለ ሲሆን፣ ምን ያህል ገንዘብ ከእርዳታ ድርጅቶች እና ከኢትዮጵያዊያኖች አገኛችሁ ሲባሉ On line ሲስተማቸውን ማየትና መረዳት ይችላል፡፡ ግልፅነትና ተጠያቂነት ትልቁ መርሃቸው ነው፡፡ ሕብረተሰቡን ከህፃናቱ ጀምሮ እስከ አዋቂው ያሳተፈ የባለድርሻ አካላቶችን ከድርጅቶች፣ መንግሥታዊ፣ መንግስታዊ ካልሆኑት ጋር አብረው እንዲሆኑ አድርገው በጋራ እየሰሩ ለውጥ እያመጡ ነው፡፡ አጋሮቻቸው ትልቁን ገንዘብ እየሰጣቸው የሚገኘው USAID የአሜሪካን መንግሥት 42 ሺህ ሕፃናትን የሚረዳውን የሴቶች የማህፀን በር ካንሰር ላይ እየሰሩ ይገኛል፡፡ Cordade International xena Save the children ኖርዌይ፣ የUN ኤጀንሲ ደግሞ UNFP የሚባል ድርጅትና IOM ሀዲያ ከስደት ተመላሾች ላይ ትልቅ ሥራን አብረው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ ሌሎች ዋና አጋሮቻቸው በቀጣይነት የሕፃናቱንና የአዛውንቶቹን ሕይወት የሚቀይሩ ኢትዮጵያዊያን የቢዝነስ ካምፓኒና፣ የመንግስት ሴክተሮች ከአንድ ልጅ ጀምሮ እስከ 250 ልጆች ስፖንሰር ያደረጉ እንደ እነ Stile RM፣ ኖህ ሪል ስቴት፣ አቢሲኒያ ግሬት፣ ሚኒስትሪ ፓርኪንግና CGF የመሳሰሉ በጣም ብዙ ልጆችን የሚረዱ አጋሮች እንዳሏቸው አውቀናል፡፡

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድጋፍ ሰጪዎች ኢትዮጵያን እየተው ወደ ሌላ አገር እየረዱ ስለሚገኙ (የመን፣ ሊቢያ.) ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እኛ ራሳችንን የምንችልበትን ሥራ ለመስራት ትልቅ እንቅስቃሴ ለማድረግ የገንዘብ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል፡፡ 25ኛ ዓመት ፈቃድ ያገኙበትን ጊዜ በማሰብ ያከናወኗቸው ተግባራት ከአረጋዊያንና ከህፃናቱ ጋር በዮድ አቢሲኒያ፣ በቶቶት ባህላዊ ምግብ አዳራሽ፣ በስካይ ላይት ሆቴል ነፃ አዳራሽ ሰጥቷቸው ከታዋቂ ሰዎቻቸው ጋር እነ ሎሬት የትነበርሽ ንጉሴ፣ ዶ/ር ወዳጄነህ፣ መጋቢ ሀዲስ እሸቱ፣ ከምሁራን አቶ ፋንታሁን ዋቄ በጎነት መስረፅ እንዳለበት በማመን ቅስቀሳዎችን ሰርተዋል፡፡ አዋሣ ላይ ከእነዚሁ ሰዎች የተወሰኑትን በመያዝ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ እንደሰሩ የማህበሩ መሥራችና ስራ አስኪያጅ ሲስተር ዘቢደር አጫውተውናል፡፡

ሲ/ር ዘቢደር ለኢትዮጵያ ህዝብ ሜሪጆይን በመወከል ያስተላለፉት መልዕክት ‹‹በሁሉም መንገድ ያገባኛል የሚለውን አቋምና ሥሜት እንዲኖርና የተበራከተውን የጎዳና ተዳዳሪነትና HIVን በጋራ እንድንከላከል፣ ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናት በጣም እየበዙ በመሆኑ የዜጎችና ‹የአዛውንት የሀገራችን ጉዳይ ያገባናል› ብለን ድጋፍ እንድናደርግ፣ የሀይማኖት አባቶች ከተለመደው ወጣ ብለው ምዕመኑን ከየቤቱ ወጥቶ የተቸገሩ አረጋዊያንና ህፃናትን ጉብኝት እያደረገ ቢረዳ›› በማለት ለእያንዳንዳችን ከአደራ ጭምር መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

ሲ/ር ዘቢደር ዘውዴ በጤና ችግር ነበር ወደ ሜሪጆይ አመጣጣቸው፡፡ የራሳቸው ክሊኒክ የዛሬ 28 ዓመት ነበራቸው፡፡ 3 ወላጆች በአንድ ወር ውስጥ ስለሞቱና እርሳቸውም እህታቸው ምጥ ይዟት ማዋለድ ባለመቻላቸው ማዋለጃውን እስኮ ገብርኤል ክሊኒክን አቋቋሙ፣ ከዚያም አፍንጫቸው ውስጥ ዕጢ በመብቀሉ ዕጢው መዳን ስላልተቻለው በሀይማኖታቸው የኦርቶዶክስ ዕምነት ተከታይ ስነበሩ ፀበልና ዕምነት በመውሰድ በ6ወር ውስጥ ስለተፈወሱ የራሳቸውን ክሊኒክ ወደሜሪጆይ ሜሪ (ማርያም) ጆይ (ደስታ) በማለት ቀይረው አገልግሎት መስጠት ጀመሩ፡፡ስለ ማዘር ትሬዛ ተማሪ እያለች ስለምትሰማ ቀይ መስቀልን እያገለገለች የምትሰማው “ፍቅርችሁ ድንበር የለሽ ይሁን” የሚል ስለነበረ ሜሪጆይም “የሰው ልጅ ማንኛውም አገር ሄደን ሥንሰራ በሀይማኖት፣ በጎሳ፣ በፖለቲካ ልዩነት ሳናደርግ ድጋፍ እናደርጋለን›› የሚል ስለነበር ነው አጀማመሩ፡፡

በ25 ዓመት ውስጥ ድጋፍ ላደረጉ የማህበረሰብ ክፍሎች ትልቅ ምስጋና አቅርበው ‹‹ሜሪጆይ ዛሬ ላይ የደረሰው በእናንተ ድጋፍ ስለሆነ ስለሆነ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ በተለይ በተለይ የሜሪጆይ አመራሮች፣ ቦርዱን፣ አጠቃላይ ጉባኤውን፣ ጊዜያቸውን መስዋዕት በማድረግ የአመት ዕረፍት ሳይወስዱ ትልቅ ስራ በመስራት እዚህ ላደረሱት ለሜሪጆይ ሰራተኞችና ለንግዱ ህብረተሰብና የአረጋዊያን ማህበሩ ሲመሰረት ትልቅ መስዋዕትነትን ለከፈሉ ለኪነ-ጥበብ ሰዎችና ለመገናኛ ብዙሃን በየቤቱ ሄደው ትልቅ ሥራ ለሰሩ ሁሉ በቀጥታም በተዘዋዋሪም ለመንግሥት አካላትና ለደገፉን ሁሉም ሥጋታቸውን አቅርበዋል፡፡ ሲ/ር ዘቢደር ዘውዴ እኛም ሥራቸውን አድን ቀን ደጋፊዎቻቸውን አመስግነን ተሰናብተናል፡፡■

# ግድቡ ተቆርቋሪ መንግሥትን ይሻል !



አክሎግ ቢራራ (ዶ/ር)

እነዚህ የተባበሩት መንግሥታት መሪዎች ያቀርቧቸው ማስጠንቀቂያዎች ትክክል ናቸው። ወደፊት ብቻ ሳይሆን፣ ዛሬ ባለንበት ዓለም በተፈጥሮ ኃብት የይገባኛልነት ምክንያት በየአካባቢው ግጭቶች ይካሄዳሉ። የዓለም ሕዝብ ቁጥርና ፍላጎት እየጨመረና እየተለወጠ ሲሄድ ግጭቶችም እየተባባሱ ይሄዳሉ። ይህ አስጊ ሁኔታ በሃገራችን ከማንነት ጥያቄ ጋር እየተቆራኘ ለፖለቲካ ልሂቃን፣ ለአክራሪ ብሄርተኞች፣ ለጽንፈኞች፣ ለእስልምና ኃይማኖት አክራሪዎችና ለኢትዮጵያ የውጭ ጠላቶች ቀስቃሽና መጋቢ ሆኗል። የውክልናው ጦርነት በኢትዮጵያ ላይ ከመቸውም ጊዜ በባሰ እየተካሄደ ነው። የማንነትን ጥያቄ እየዘለጠጡ ለሥልጣንና ለግል/ለቡድን ጥቅም የሚያውሉ ኃይሎች ያልተገነዘቡት ሃቅ፣ ቆምንለት ለሚሉትም ሕዝብ አጥፊ መሆኑን ነው።

ኢትዮጵያ የተከበበች አገር መሆኗን ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ በድህረገጾች አሳስቤ ነበር። እንደ ዛሬ ግን ለአገሬ ሰግቸ አላውቅም። ወገኖቸ እንደ በግ እየታረዱ፣ እህቶቸ እየተነጠቁ፣ የአገሬ አንጡራ ኃብት እየተነጠቁ ሳይ ከስጋት በላይ ስጋት አደረብኝ። ሌላ አገር እንፍጠር፣ እንገንጠል ወይንም የራሳችን የበላይነት እናጠንክር ወይንም "ተረኛነታችን ይከበር" ወይንም ወደ ሥልጣን እንመለስ የሚሉ ኃይሎች ኢትዮጵያ የነገዋ ዩጎስላቭያ ወይንም ሩዋንዳ ወይንም የመን ወይንም ሊቢያ ብትሆን ምን ሊያገኙ ነው?

ዛሬ የምንኮራባት ኢትዮጵያ በቀደምትነት የሚያስፈልጋት ክብሯን፣ ግዛታዊ አንድነቷንና ሉዐላዊነቷን የሚያስከብርላት አመራርና መንግሥት ነው። ከፖለቲካ ፉክክርና ከምርጫ በፊት ይህች ታላቅ አገር በራሷ ልጆች ንትርክና የእርስ በእርስ ጦርነት እንዳትጠፋ ማድረግ የሁላችንም፣ በተለይ በድሃው ሕዝብ ድጋፍ የተማርነው ልጆቿ ነው። ይህች አገር ከጠፋች በኋላ ብናለቅስ ፋይዳ የለውም። በማንነት ሆነ በሌላ የግልና የቡድን ዝናና ጥቅም ምክንያት ዛሬ ኢትዮጵያን ወደ ገደል አፋፍ የሚገፏት እብሪተኞች፣ ጠባብ ብሄርተኞች፣ አክራሪ ኃይሎች ያልተገነዘቡትን ክስተት አስቀድሜ ለመናገር እገደዳለሁ።

እነሱንም ሆነ ንጹሁን የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚጠብቃቸው ተከታታይ የእርስ በእርስ ግጭትና እልቂት እንደሚሆን መገመት አለባቸው። እንዴት ከመቶ አስራ አምስት ሚሊየን ሕዝብ ተቆርቋሪ፣ ብልሃተኛ፣ ለነገው ትውልድ የሚያስብ ይጠፋል? ወገን ወገኑን እንደ በግ ሲያርደው እያየን እንዴት እንቅልፍ ይይዘናል? እንዴት በልተን አናድራለን?

የታላቁ የኢትዮጵያ ግድብ ጉዳይ ከእነዚህ ከአገር ውስጥና ከውጭ ጠላቶች ፍላጎት፣ ጥቅምና "የኔ ተራ ነው" ባይነት ጋር ተያይዟል። የዛሬ ሰላሳ አምስት ዓመት የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሃፊ ሆኖ ያገለግል የነበረው ቡትሮስ ቡትሮስ ጋሊ እንዲህ ብሎ እንደነበር አስታውሳለሁ። "በመካከለኛው ምስራቅ ጦርነት የሚካሄደው በውሃ የበላይነት ምክንያት ነው።" ይህ የአረብ ብሄርተኛ የድርጅቱ መሪ ከመሆኑ በፊትና ከሆነ በኋላ ጸረ-ኢትዮጵያ አቋም ነበረው። ሻብያንና ሌሎችን የብሄር እንቅስቃሴዎች ደግፎ ኢትዮጵያ የባህር በሯን እንድታጣ ካደረጉት ባለሥልጣናት መካከል አንዱ ነበር። በዐባይ ወንዝ አጠቃቀም ላይ ጦርነት የማይቀር መሆኑን ቡትሮስ ቡትሮ ጋሊ ያውቅ ነበር።

የአረብ ሊግ የተባለው ድርጅት በኢትዮጵያ ላይ ያካሄደው ተከታታይ ጥቃት አሁንም አልቆመም። ኤርትራ ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል ከጀርባ ሆኖ የሰራው ሴረኛ አንዱ ቡትሮስ ቡትሮስ ጋሊ ሲሆን፣ በድርጅት ደረጃ ሌላው ጫና ያደረገው ስብስብ የአረብ ሊግ ነው። ከህወሓት፣ ከሻብያ እና ከኦነግ ጋር ሆኖ ሁኔታዎችን አመቻችቷል፣ ተመሳጥሯል። ይህ ሴረኛነት አሁንም በአዲስ መልክ ይታያል። በኢትዮጵያ ሰላምና እርጋታ የውሃ ሺታ የሆነበት ዋና ምክንያት፣ አንዱ የአገር ውስጥ የዘውግ ጽንፈኞችና አክራሪዎች ሲሆኑ፣ ሌላው ከጀርባ ሆኖ የገንዘብ፣ የመረጃ፣ የአቅም ግንባታ ድጋፍ የሚሰጡት ግብጽ፣ ኢራንና ተመሳሳይ ኃይሎች ናቸው።

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በዚህ ወር መጨረሻ በአዲስ አበባ ሰለ ሰላም፣ ስለ ደህንነትና ስለብእርጋታ ውይይት ሲያደርግ ለአገራችን ሰላም ከነሱት ኃይሎች መካከል የግብጹ አል ሲሲ የሚያካሂደውን የውክልና ጦርነት እንዲያቆም ሹክ ያለው የኢትዮጵያ ባለሥልጣን ወይንም ሌላ ተቆርቋሪ ያለ አይመስለኝም። የሚነገረው ሌላ የሚሰራው ሌላ ነው።

ቡትሮስ ቡትሮስ ጋሊ "በመካለለኛው ምስራቅ" ጦርነት አይቀርም ብሎ ሲናገር ሰሜን አፍሪካንም ይጨምራል፣ ግብጽን። ግን በቲግሪስ ኤፍራትስ ወንዝ አጠቃቀም ዙሪያ ስመለከተው፣ እስካሁን ድረስ ንትርክ ቢኖርም፣ ተርኪ፣ ኢራክ፣ ሶሪያና ሌሎች አገሮች ወደ ጦርነት አልሄዱም። ተርኪ ብዙ የመብራትና የመስኖ ግድቦችን ሰርታለች። የኔቶ አባል በመሆኗ ብቻ ሳይሆን በዚህች አገር ላይ አረቦች ጦርነት አላወጁም። እስራኤል አስደናቂና የተለየ የውሃ አጠቃቀም ዘዴዎችን ፈጥራ ለሌሎች አገሮች ምሳሌ ሆናለች። በመካከለኛው ምስራቅ፣ ዋናውና ወሳኙ የወንዝ አጠቃቀም ስኬት ምክንያት፣ ተርኪ አገር ወዳድ አመራር፣ ጠንካራና አገር ወዳድ መከላከያ ኃይል ስላላት ነው።

ከአፍሪካ አገሮች በባሰ ሁኔታ የውሓ እጥረት ያለው በመካከለኛው ምስራቅ ነው። የውሓ እጥረት ለጦርነት መንስኤ መሆኑን እየተቀበልኩ፣ ግን ይህ ሁኔታ ብቻውን ጦርነት አይቀሰቅስም። ብዙ አገሮች፣ በአውሮፓ ራይን፣ ሮንና ሌሎች ወንዞች፣ በኤዥያ ሜኮንግ፣ በላቲን አሜሪካ አማዞን፣ በአሜሪካ ሪዮግራንዲ እና በደቡባዊ አፍሪካ ሌሶቶና ደቡብ አፍሪካ ተዋውለው ስራ ላይ ያዋሉት የውሓ አቅርቦትና ፍጆት ውል ወዘተ ያለ ጦርነት ስኬታማ ሆነዋል። ስምምነት፣ ሰጥቶ መቀበልና መቻቻልም ሚና አላቸው። ይህ ከሆነ የአፍሪካ አገሮች የናይል ወንዝ ድርድር አድርገው (Nile Basin Initiative) ወንዙን ለጋራ ጥቅም አናውለው ካሉ በኋላ ግብጽ ለምን አሻፈረኝ አለች? ማንን ተማምና? ምን አይነት የዲፕሎማቲክ ድጋፍ አግኝታና ከማን? በኢትዮጵያ ውስጥ ምን አይነት ክስተት አይታና ተማምና?

የዐባይን ወንዝ በሚመለከት የሚታየው የአገር ውስጥና የዲፖሎማሲ የኃይል አሰላለፍና ጫና ነው። በዚህ ትንተና የማቀርበው በፖለቲካ አመራር ያለውን ጥንካሬና ድክመት ነው (hydro politics and power balance). በአሁኗ ኢትዮጵያ የኃይል አሰላለፉ እና የዲፕሎማሲ ጫናው ፍትሃዊና ሚዛናዊ አይደለም። የሚያደላው ለግብጽ ነው። ኢትዮጵያ በአገር ውስጥ የውክልና ጦርነት እየተካሄደባት ነው። ይህን ክስተት ልንክደው አንችልም። ይህን የሚያደርገው ህወሓት ብቻ አይደለም፣ የኦሮሞ ብሄርተኞችና ጽንፈኞች፣ የእስልምና አክራሪዎች የአንበሳውን ክፍል ይዘውታል።

ኢላማው ምንድን ነው? እኔ ስከታተለውና ስገመግመው ኢትዮጵያን ለማዳከም፣ ቢቻል በሙሉ እንድትበታተን ለማድረግ ነው። ይህ አፍራሽነት የጀመረው ዛሬ አይደለም። ሕገ መንግሥቱ "እኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ" በማለት ፋንታ፣ "እኛ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች" በሚል መሰረታዊ ሃረግ ሲጀምርና ኢትዮጵያን በዘውግና በቋንቋ ሲሸነሽኗት ነው ችግሩ የተፈጠረው። ይኼን የጣሊያኖችን ▶

እቅድ ስራ ላይ ያዋሉት የብሄር ልሂቃን ናቸው። ከጀርባ ሆነው ድጋፍ የሰጡት ግን እነ ኽርማን ኮህን እና አረቦች ናቸው። የዓባይ መዘዝ አለበት ማለት ነው።

ህወሕት መራሹ ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘበት ጀምሮ፣ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የሚሉት እሴቶች እየተወገዱ፣ በግልጽ የሚካሄዱትና እየጠነከሩ እንዲሄዱ የተደረጉት እሴቶች ጠባብ ብሄርተኝነትና ጽንፈኛነት፣ ህወሓት ተወግዶ በተራው "የእኛ፣ ኬኛ" የሚሉት ኃይሎች ስብስቦች ናቸው። ይህ ጠባብ ብሄርተኛነት፣ ጽንፈኛነትና "ኬኛነት" ለማን ያደላል? ለግብጽ ነው የሚያደላው። የውክልና ጦርነት ስር እየሰደደ ሄዷል ማለት ይኼው ነው። እነዚህ የአገር ውስጥ ኃይሎች ለአገርና ለመላው ሕዝብ በመቆም ፋንታ ተወካይ ሆነው ለውጭ ኃይሎች እያገለገሉ ነው። ውክልና ማለት መሳሪያ ይዞ መተኮስና መግደል ብቻ አይደለም። እንደ ኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ያሉትን ተቋማትን ማፍረስ አንዱና ዋናው አካል ነው። የዘውግና የኃይማኖት አክራሪነትን እያስተጋቡ ኢትዮጵያዊነት እና አብሮና ተከባብሮ ይኖር የነበረውን የእስልምናና የክርስትና ወንድማማች ሕዝብ እንዲለያዩ ማድረግና ተቋማት እንዲፈርሱ መጎትጎት ሌላው ስልት ነው።

እርግጥ ነው ግብጽ የውሃ እጥረት እንዳለባት አልክድም፣ ማንም አይክድም። እኔ የምከራከረው ኢትዮጵያ ሉዐላዊነቷ በዓለም ታውቆ በነጻነቷ የቆየች አገር እንደ መሆኗ መጠን፣ የራሷ የሆነውን ዐባይን ገድባ ለራሷ ብሄራዊ ልማት ለመጠቀም ሙሉ መብት አላት ነው። በድርድር ዙሪያ የኢትዮጵያ ሕዝብ በጨለማ እየኖረና እየተራበ ይኑር፣ የግብጽ ሕዝብ ግን የውሃና የምግብ ዋስትናው ይጠበቅ የሚል ሶተኛ አካል ወይንም ኃይል ሊኖር አይችልም።

አሜሪካ ከጎረቤቷ ከሜክሲኮ ጋር የምትጋራው ሪዮግራንዴ አለ፣ ብዙ ግድቦች ስርታ ትጠቀማለች። ተርኪ የቲግሪስ ኤፍራትስን ወንዝ ለኃይል ማመንጫና ለመስኖ ስራ ገድባለች። በአፍሪካ አህጉር በስምምነት ስኬታማ የሆነውና ሊጠቀስ የሚገባው ምሳሌና አማራጭ በሌሶቶና በደቡብ አፍሪካ መካከል የተደረገው ውል ነው። የሌሶቶ ሃይላንድ የውሃ ፕሮጀክት (The Lesotho Highlands Water Project (LHWP) ተብሎ የሚታወቀው ስምምነት፣ በአንድ በኩል ሌሶቶ የኃይል ማመንጫ ግድብ ያለበትን ውሃዋን ለደቡብ አፍሪካ እያቀረበች ደቡብ አፍሪካ ለሌሶቶ ግብር እንድትከፍል ያደረገ ውል ነው።

በውሉ መሰረት ሌሶቶና ደቡብ አፍሪካ በጋራ የሰሩት ድርጅት ብዙ ትልልቅ ግድቦችን የያዘ ሲሆን፣ እነዚህ ግድቦች በመላው ሌሶቶ ቦዮች ተከፍቶላቸው ውሃው ተሰብስቦ ቫል በተባለው በደቡብ አፍሪካ ወንዝ አጠራቃሚነት ለደቡብ አፍሪካ ህብረተሰብ የውሃ አገልግሎት ይሰጣል። በሌሶቶ መጋቢ ከሆኑት ወንዞች መካከል ማሊባማትሶ፣ ማትሶኩ እና ሴንኩ ይገኙበታል። እነዚህ ሁለት የጥቁር አፍሪካ አገሮች በጋራና በመተባበር የፈጠሩት የወንዝ አጠቃቀም ፕሮጀክት በአፍሪካ ከፍተኛ ቦታ የያዘ ነው። ሞዴል ነው።

ይኼን ምሳሌ የጠቀስኩብት መሰረታዊ ምክንያት ከዐባይ ጋር ይመሳሰላል ለማለት ሳይሆን፣ ለሁለት ምክንያቶች ነው።

አንደኛ፣ ፈቃደኛነት ካለ ለኢትዮጵያ ሌላው አማራጭ ግብጽ ከዐባይ ለምታገኘው ውሃ መጠን በስምምነት ኪራይ እንድትከፍል እንዲታሰብበት ለማሳየትና፣

ሁለተኛ፣ በደቡብ አፍሪካና በሌሶቶ መካከል የተደረገው ውል የሚያሳየው በውሉ መሰረት ሌሶቶ በራሷ ክልል ወይንም ወሰን ለሚገኘው ተቋም የሉዐላዊነት መብቷን ለመጠቀም እንደቻለች ለማሳየት ነው። በ 24 October 1986 የተፈረመው ውል አንቀጽ 7 (1) እንዲህ ይላል፣ "The Lesotho Highlands Development Authority shall have the responsibility for the implementation, operation and maintenance of that part of the Project situated in the Kingdom of Lesotho, in accordance with the provisions of this Treaty and shall be vested with all powers necessary for the discharge of such responsibilities. የሌሶቶ ልማት ባለሥልጣን በሌሶቶ ለሚገኘው የውሃ ፕሮጀክት የስራ አፈጻጸም ሂደት ደህንነት፣ ጥገናና ሃላፊነት ሙሉ ስልጣን ይኖረዋል" ይላል።

በተመሳሳይ፣ የታላቁ የኢትዮጵያ ግድብ ባለቤት፣ ሉዐላዊነትና ባለሙሉ ስልጣን ኢትዮጵያ እንጅ ግብጽ ልትሆን አትችልም። ኢትዮጵያ በአስዋን ግድብ ላይ እንደማያገባት ሁሉ፣ ግብጽም ሆነ ሌላ ሶስተኛ አካል በታላቁ የኢትዮጵያ ግድብ አስተዳደር፣ ጤናማነት፣ ጥበቃ፣ ጥገናና አመራር ጣልቃ መግባት የለበትም። የኢትዮጵያ መንግሥት መሪዎች ዋና ሃላፊነት ይኼው ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከገቢው አውጥቶ በሰራው ግድብ ላይ ኢትዮጵያ ሉዐላዊ መብት የላትም፣ ግብጽ ወይንም ሌላ ሶስተኛ አካል ያገባዋል የሚል ካለ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት መከራከር ያለበት፣ ይህ አዲስ ክስተት፣ የዓለም መንግሥታት ከሚከተሉት ደንብ፣ ልምድ፣ ውልና ሕግ ውጭ ነው ብሎ ደፋር አቋም መውሰድ አስፈላጊ ነው። ይህን የግብጾችን ተንኮልና ሴራ የሚያስተጋቡ አካላት፣ ዓለም ባንክንና የአሜሪካን መንግሥት ጨምሮ ካሉ በይፋ ለኢትዮጵያና ለመላው የአፍሪካ ሕዝብ በግልጽ ይንገሩን፣ አይሸውዱን። ግልጽነት ይኑር። ሌሶቶ ሉዐላዊ መብቷን ካስከበረች ኢትዮጵያም የማታስከብረበት ምክንያት የለም። ግብጽ በሲዝ ካናል ሉዐላዊነት ተከራክራ መብቷን አስከብራለች። እኛስ?

ዓለም ባንክ፣ የተባበሩት መንግሥታት የልማት ድርጅት፣ የናየል ተፋሰስ አገሮች ድርድርና ውል በስምምነት ወንዙን እንጠቀም ብለው ቃል ከገቡና ተቋም ከፈጠሩ በኋላ ግብጽ እሚበተኛነት አሳይታለች። ግብጽ ከፈርዖኖች ዘመን ጀምራ ኢትዮጵያ ወንዞቿን እንዳትጠቀም ስታስፈራራን ኖራለች። ወረራዎችም አካሂዳለች። ጠ/ሚንስትር መለስ ዜናዊ አንድ ጊዜ ይህን የእብሪተኛነት ባህል እንዲህ በሚል ድፍረት አሰምቶ ነበር። "ኢትዮጵያን ለመውረር የመጣ ግብጻዊ ወደ አገሩ ተመልሶ ታሪኩን የተናገረበት ጊዜ የለም።" ግድቡን በሚመለከት፣ ጠ/ሚንስትር ኃይለማሪያም ደሳለኝም የወሰደው ተመሳሳይ አቋም ነበር። አገርን የሚመራ ማንኛውም ግለሰብ ታማኝነቱ ለኢትዮጵያና ለመላው ሕዝቧ ብቻ ነው፣ ለፓርቲው ወይንም ለዘውጉ ወይንም ለሥልጣኑ አይደለም።

የግድቡ ክርክር የወንዙ ውሃ መቀነስ ብቻ አይደለም። ግድቡ ሲሞላ ለተወሰነ ጊዜ የግብጽ የውሃ መጠን ሊቀንስ ይችላል። ግን መጠኑ ለግብጽ አስጊ እንደማይሆን ጥናቶች ያሳያሉ። ችግሩ ግብጽ አንዲትም ጠብታ እንዲቀንስ ፈቃደኛ አይደለሁም ማለቷ ነው። ይህ ግትር አቋም የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁልጊዜም ቢሆን ረሃብተኛ ሆኖ እንዲማቅቅ፣ በጨለማ እንዲኖር ከመፍረድ ልዩነት የለውም። ደንታ ማሳየት ያለበት ግትሩ የአልሲሲ መንግሥት አይደለም። በሃላፊነት የሚጠየቀው ጠ/ሚንስትር ዶር ዐብይ የሚመራው መንግሥት ነው። በዚህ ዙሪያ ኢትዮጵያን ተጠቂና አጎብዳጅ እንድትሆን ያስገደዷትን ክስተቶች በአጭሩ ላቅርብ፣

ህወሓት የኢትዮጵያን መንግሥት ተቃውሞ መቀሌ መመሸጉና በየአካባቢው ግጭቶችን መቀስቀሱ፣ በቅርቡ ልክ ትግራይ የተለየ አገር በሚመስል ሁኔታ፣ ህወሓት በመቀሌ ያሳየው የመከላከያ ኃይል ትእይንት–ልዩ ልዩ ከባድ መሳሪያዎችን የያዘ—ህወሓት አገር ወዳዱን የትግራይን ሕዝብ ለጦርነት የሚያዘጋጀው ይመስላል።

እንደ ግብጽ ላለ የውጭ ተመልካች በኢትዮጵያ አንድ መንግሥት የለም። ሁለት ወይንም ከሁለት በላይ መንግሥታት አሉ ወደሚል ድምዳሜ ያመራቸዋል። ኢትዮጵያን በቀላሉ ለማንበርከክ ይቻላል ወደሚል የተሳሳተ አቅጣጫ። የኢትዮጵያ የፌደራል መንግሥት በአስቸኳይ ከሚያደርጋቸው ውሳኔዎች መካከል በየክልሉ የተቋቋሙትን ልዩ የጦር ኃይሎችና የመሳሪያ ክምችቶች ብሂራዊ ወይን ኢትዮጵያዊ ማድረግ ነው። ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት አንድ ለአገር ሉዐላዊነትና ግዛታዊ አንድነት ታዛገርና ታማኝ የሆነ የመከላከያ ኃይል ብቻ ነው።

በጃዋር ሞሃመድ ቀስቃሽነት፣ ጠባብ ብሄርተኛውና ጽንፈኛው የቄሮ አካል፣ አክራሪ የእስልምና ኃይማኖት ተከታዮችና ሸኔ ኦነግ የተባለው አሸባሪ እንቅስቃሴ በድሬ ዳዋ፣ በሃረር፣ በአዲስ አበባ፣ በኦሮምያ፣ በቤኒ-ሻንጉል ጉሙዝና በሌሎች ክልሎች የሚያካሂዱት አመጽ እየተባባሰ መሄዱ። ጃዋርንና ጠባብ ብሄርተኞችን ያደፋፈራቸው ክስተት የኢትዮጵያ ፌደራል መንግሥት ለጃዋር ልዩ ክብር በመስጠት ጥበቃ እንዲደረግለት ማድረጉ ነው። ይህ ሁኔታ ብዙ የአረብ አገሮችን፣ ግብጽን ጨምሮ አስደስቷቸዋል። አድልዎ ከፋፋይ አስተሳሰብ ነው።

# በዚህ ሀሳቤ የማይስማማ ወዳጄ አይደለም !



ሙክታር ዑስማን

ኢትዮጵያን የምንል ሰዎች ከኢትዮጵያ የተለየ ጥቅም ስለምናገኝ አይደለም:: ኢትዮጵያ በአንድነቷ እንደታሪኳ ቀና ብላ በአለም ላይ ብትደምቅ ብትበለፅግ ለእኛ የተለየ ድርሻ ይኖረናል ብለን አይደለም:: የሁላችንም ጥቅም ጎልቶ ስለሚታየን ብቻ ነው:: ተዉ አንድ እንሁን፣ ተዉ ቂም በቀል አንፈልፍል፣ ተዉ በኢትዮጵያ ሰማይ ስር ማንም ኢትዮጵያዊ ያሻው ቦታ ላይ ሠርቶ የማፍራት፣ መርጦ የመኖር ነፃነት እና መብቱ ይጠበቅለት ማለታችን ፣ ማረፊያ መውደቂያ ስላጣን አይደለም፣ የአባት የእናት የዘመድ አዝማድ የትውልድ ቦታ አጥተን አይደለም:: አንድ እንሁን አንለያይ ማለት መነሻ የሌለን ወፍዘራሽ ስለሆን አይደለም:: የሀገርና የፖለቲካ ትርጉም ስለገባን ነው:: የዜግነት ፅንሰሀሳብ የሚመሰረተው በሁሉ እኩልነት ላይ መሆኑ ስለገባን ነው:: የእኔ ብሄር ብቻ ያስተዳድር በሚል የሚጀመር ፖለቲካ በየትኛውም መስፈርት ኃላቀር ፖለቲካ መሆኑ ስለገባን ነው::

ኢትዮጵያን ያልን በዚህች ሀገር ከመጎዳት ውጪ ያተረፍነው የለም:: ብሔራችንን ያላልን በሀገራችን ተገፍተናል፣ ባይተዋር ሆነናል፣ ተበደልናል፣ ከንቀትና የቀድሞ ስርዓት በደል ተሸካሚ ከመሆን ውጪ ያተረፍነው የለም:: ተናቅን እንጂ አልተከበርንም:: አጣን እንጂ አላገኘንም::

መታገሳችን እኛ ጀግንነትና ድፍረቱን አጥተን፣ ብሔሬን ያሉት ስለጀገኑም አይደለም:: ብሄርተኝነት መንገድ የሚመጣውን መዓት መተንበይ ስለቻልን ነው:: አለም በብሄርተኝነት የት መቀመቅ እንደገባች፣ ሀገራት እንዴት እንደፈረሱ ስላጠናን፣ ከአዋቂዎች አንደበት ቁጭ ብለን ስለተማርን፣ በግል ከመጠቀምና ለስልጣንና ክብር ከመስገብገብ የሀገርና የህዝብን ሰላምና ቀጣይነት ስለፈለግን ነው::

ጥቂቶች አይደለንም:: በሀገራችን ባይተዋር የሆን ሚልዮኖች ነን:: የሚወክለን ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅት አጥተን የምንብሰለሰል ሚልዮኖች ነን:: ለምን ይህን አቋም መረጥን?

የሀገር ፍቅር በጥቅም ስለማይመዘን ነው:: ትሥሥራችን እያንዳንዱ ቤተሰብ ውስጥ የዘለቀ ስለሆነ ነው:: ሀገር ከመንደር ስለሚሻል ነው:: ሠርተን፣ ለፍተን በላባችን አፍርተን፣ አንገታችንን ቀና አድርገን የምንኖርባት ሰላማዊ ሀገር ለመፍጠር ነው:: ደስታም ስኬትም፣ ዝናም ክብርም፣ ሀብትም ፍቅርም፣ ትዳር ጥሪትም፣ ፅምነት ተስፋም፣ ሰርግ ቀብርም...ሁሉም በሀገር እንደሚያምር ስለገባን ነው:: መስከናችን፣ ዝም ማለታችን ለሀገር የሚበጅ ከሆነ ግዴለም ይሁን ብለን እንጂ እውነት ከኛ ጋ መሆኗን አጥተን አይደለም::

የብሄርተኝነት መንገድ ለሰጥቶ መቀበል የማያመች፣ መነጋገር የሌለበት፣ እኛ እና እነሱ በሚል ግጭት ቀስቃሽ ቁርሾና ጥላቻ በመፈልፈል ህዝብን ከህዝብ ስለሚያጋጭ ነው የምንርቀው:: ብሄርተኝነት ታሪክን እና የድሮ በደልን እየቆሰቆሱ በቂም ማያያዝን እንደርእዮተአለም የሚጠቀም፣ በፍርሃትና በስጋት ህዝብን እያመሰ ድጋፍ የሚሰበስብ የጥቅመኞች መንገድ ስለሆነ ከግል ጥቅም ጥቅም ሀገርን መርጠን ነው የራቅነው::

በብሄር እየተቧደኑ ደም መፋሰስ ያረጀ ያፈጀ፣ ኋላ ቀር፣ እንስሳዊ ባህሪ ስለሆነ ነው የራቅነው:: መጫረስ የኢትዮጵያ ጠላቶች ያቀዱልን እና ማዳከም ማልፈስፈስና አቅመቢስ ማድረግ የፕሮጀክታቸው ግብ ስለሆነ ነው ብሄርተኝነትን የምንጠየፈው:: የብሄር ፅንፈኝነት አሸናፊ የማይኖርበት ሁላችንንም መቀመቅ ይዞን የሚወርድ የጋራ ውድመት መንገድ ስለሆነ ነው የምንርቀው::

ማንም ማንንም ለፍቶ ካቀናው ሀገር፣ ተወልዶ ካደገበት ከተማ፣ ከአባቱ ርስት በዋዛ ሲነቀል ዝም ስለማይል መተላለቅ ደጃችን ላይ መሆኑን ፈርተነው ከልዩነት አንድነትን የምንመርጠው:: ማንም በማንም ላይ የበለጠ ጀግና ስላይደለ የእልህ ፖለቲካ ያዳክመናል ብለን ነው ጎሰኝነትን የራቅነው:: ማንም በየትም ቦታ መኖር መክበርና ወልዶ መሳም አለበት ብለን ስለምናምን ነው የብሄር ፖለቲካ ዘመናዊውን አለም የማይጥን አደገኛ ስለሆነ ነው የማንከተለው::

ይህ ማለት ብዛኻነትን የምንክድ ሆነን አይደለም:: አንድነት ልዩነትን ማሰሪያ አማራጭ የለሽ መፍትሄ እንጂ ጨፍላቂነት እንዳልሆነ እናውቃለን:: አንድነት የልዩነት ማሰሪያ ብርቱና ወርቃማ ገመድ መሆኑን እናውቃለን:: ልዩነት የአንድነት ጌጥ መሆኑን እናውቃለን:: ሀገር በአንድነት ላይ ተመስርታ ልዩነታን ማቀፍ እንዳለባት እናምናለን:: ከልዩነት መነሳት ወደ አንድነት ሳይሆን ወደ የባሰ መከፋፈል እንደሚወስደን ስለገባን ነው አንድነትን የምናስቀድመው እንጂ ልዩነት አይኑር ብለን አይደለም::

በሀይማኖትና በጎሳ የሚለያዩን በችግር ጊዜ ከእኛ ጋ እንደማይሆኑ ስለሚገባን ነው የማንፈልጋቸው:: የግጭትና ሞት ነጋዴ ስለሆኑ ነው የምንርቃቸው:: የሰው ህይወት መጥፋት ስለሚያመን ነወ የማንወዳቸው:: በሞት ስለሚያተርፉ ነው የማንከተላቸው::

ኢትዮጵያን እና ህዝቦችዋን የምናስቀድመው ሁሉ ኢትዮጵያዊ ሰው መሆኑ ተከብሮ፣ እኩል ሆኖ፣ በተከበረችና በበለፀገች ሀገር ላይ ብሄሩ፣ ቋንቋውና ታሪኩ እንደሚከበርና እንደሚበለፅግ ስለምንተልም ነው አንድነትን የምንሻው:: የስርዓት ችግር ስርዓቱን በማረምና በማዘመን ይታረማል ብለን ስለምናምን ነው ወደ ኋላ ከማየት ወደ ፊት እያየን ነገአችንን በመመካከረ በእኩልነትና በነፃነት ላይ ሀገር እንገንባ የምንለው:: ከትናንት ተምረን ነገን እናሻሽል በማለት ነው የትናንቱን ታሪክ መጥፎ መጥፎውን ብቻ ሳይሆን መልካሙንም እንያዝ የምንለው::

እኛ ይህን ነው የምናስበው:: በዚህ እሳቤ ሀገር ያድጋል እንጂ ማንም አይጨፈለቅም:: ማንም አይዋረድም:: የአለም ሀገራት የሚሄዱበትም መንገድ ይህ ነው::

# ኦነጋዊ የታሪክ ስካር

## (ታደለ ገመቹን ታሪክ መርጠህ አትስማ/አታንብብ በሉት!)



ሙሉዓለም ገ/መድህን

የኦሮምኛ ሙዚቃ ተጫዋቹ ታደለ ገመቹ ከቤተልሄም ታፈሰ ጋር ያደረገውን የቆየ ቃለመጠይቅ ዛሬ አየሁት:: ታደለ በቃለመልልሱ "በረራ የሚባል ፊክሽን ተፈጥሯል:: በአማርኛም ሆነ በግዕዝ አንድም የታሪክ ማስረጃ የሌለው ነው" ሲል በደፋር ርግጠኝነት ተናግሯል::

በዝህች አገር አጥር አልባ ሙያ ከሆኑት ውስጥ አንዱ "የታሪክ ጥናት" ነው:: ዘርፉ የብዙዎች ማላገጫ በመሆኑ እንደ ሀገር ኢትዮጵያ "በታሪክ ፖለቲካ" የተቃርኖ ማዕከል ሆናለች:: እንደግለሰብ በየመድረኩ (ዕድሉ ተገኘ በሚል) የታሪክ ጥናትን የሚዳፈሩ አካላት በታሪክ ስካር ናላቸው ዞሯል:: ታደለ የዚህ ሰለባ ሆኖ ታይቶኛል::

የታሪክ ባለሙያ ሳይሆኑ ስለታሪክ ማውራት ይቻላል:: እኔም ይህን ማሳተወሻ ስፅፍ የታሪክ ባለሙያ ሆኘ ሳይሆን ምንጭ ጠቅሼ ነው:: ታደለ ያደረገው ግን አንድም የታሪክ ምንጭ ሳይጠቅስ "በረራ ፊክሽን ነው" ብሏል:: በጨበጣ! ለኔ ይህን ማለት አላዋቂነትን አደባባይ ላይ ማስጣት ነው:: ሲከፋም በዕውቀት ደዌ የመጠቃት ምልክት ነው:: ታደለ ገመቹ የሸዋ ኦሮሞ ነውና ኦነጋው አመለካከት በዚህን ያህል መጠን ይወርረዋል ብዬ ባልገምትም ደዌው ከመጠን በላይ አጥቅቶታል:: "ሰባት ቤቱ ድረስ ሸገር ነው የተወለድኩት ÷ በረራ የሚባል ስያሜ ሰምተን አናውቅም" ያለው ታደለ:- የርሱን ቅድመ አያቶች ቅድመ 16ኛው ክፍለ ዘመን የት መጣነት ባይነግረንም እኛ በተጨበጠ የታሪክ መዝገብ እናውቀዋለን::

አዲስ አበባ የበረራ ዳግም ልደት መገለጫ ነች

አዲስ አበባ የ'በረራ' ዳግም ልደት እንጅ በራሷ "ግኝት" አይደለችም:: የእቴጌ ጣይቱ ስያሜ (አዲስ አበባ) የበረራ ዳግም ማበብ/መፍካት መገለጫ ነው:: (ትርጓሜው በቀጥታ [ጣይቱ ካየችው አበባና ከሰየመችበት ሁኔታ ] ብቻ ሳይሆን ከታሪክ ትርጓሜ አንፃርም ይታያል) እዚህ ላይ የኦሮሞ ታሪክ ፀሃፊዎች ማምታቻ የሆነው "ፊንፊኔ" የኦሮምኛ ቃል አለመሆኑን ÷ ቃሉ አማርኛ ስለመሆኑ የፕ/ር ሀብታሙ ተገኘን ፅሁፍ በድምፅ የተቀየረውን (ናሪየት የተደረገውን) ወደ ገፄ አምጥቼ የማጋራችሁ ይሆናል::

'በረራ' የአዲስ አበባ ዳግም ልደት መገለጫ ነች ሲባል ÷ አዲስ አበባ ዛሬ ባላት ቅርፅ በመካከለኛው ዘመን በረራ ነበረች ማለት አይደለም:: በዛሬዋ አዲስ አበባና አካባቢዋ (ዛሬ ፍርስራሻቸው የቀሩ በአርኬዎሎጅ ግኝት የተረጋገጡ ) የሸዋ ነገሥታት መቀመጫዎች ነበሩ:: ከነዛ አንዷ የአፄ ዳዊት ከተማ የነበረችው በረራ ነች:: የአዲስ አበባ ዳግም ልደት መገለጫ መሠረትም ይሄ ነው::

# <<የአይስላንድ ላአ ጁቬንቱዋድ>> ትዝታ

የተወለድኩት ጥርስ የነቀልኩት ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። ነፍስ ያወቅኩት ከአንደኛ ደረጃ አንስቶ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ብሎም የከፍተኛ ትምህርቴን የተከታተልኩት ባህር ማዶ ነው።
ማንነቴ ምንም አያደርግላችሁም ግን እንደ እኔ ባህር ማዶ ተሻግረው ትምህርታቸውን የተከታተሉ ዛሬ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ሀገራችንን እያገለገሉ ያሉ እውቅ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች የእኔን ታሪክ ይጋራሉ እኔ እኔ ነኝ እነርሱም እኔ ናቸው። ከ41 ዓመት በፊት በኢትዮ ሱማሊያ ጦርነት ወቅት ወላጆቻችንን ያጣን በሺዎች የምንቆጠር ኢትዮጵያውያን ታዳጊዎች ከመላው ሀገሪቱ ተሰባስበን በታጠቅ ጦር ሠፈር ለወራት ሰነበትን። ከዚያም አንድ ቀን ከታጠቅ ጦር ሰፈር በአያሌ አውቶቢሶች ተሳፍረን ከአዲስ አበባ ተነስተን ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ወደ አሰብ ለሶስት ቀናት ተጉዘን አሰብ ደረስን።
አሠብ ወደብ ላይ በምትጠብቀን መርከብ ተሳፍረን ወደ ሁለተኛ ሀገራችን ሶሻሊስት ኩባ ተጓዝን። ከአሰብ የኤደን ባህረሰላጤን አቋርጠን በስዊስ ካናል አድርገን የካናሪን ደሴቶች አልፈን በአትላንቲክ ውቅያኖስ ላይ ሌት ተቀን ለ27 ቀናት በመርከብ ተጉዘንኩባ ደረስን።
ዛሬ ድረስ ኩባ ስንደርስ የተደረገልን ልባዊ ደማቅ አቀባበል በብዙዎቻችን ሕሊና ውስጥ ትላንት እንደተደረገ ይታየናል። ከኩባ ዋና ከተማ ሀቫና በደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ የሚገኘውን 50 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለውን አውራጎዳና በአውቶቢሶች ከተጓዝን በኋላ ለአመታት መኖሪያችን ወደሆነው አይስላንድ ላኦ ጁ ቬንቱዋድ ወይንም የወጣቶች ደሴት ወደምትባለው የኩባ ግዛት ለመጓዝ መለስተኛ መርከብ መሳይ ጀልባዎችን ተሳፍረን ተጓዝን።
አይስላንድ ላኦ ጁቬንቱዋድ ወይንም የወጣቶች ደሴት ስንደርስ ከእኛ ቀድመው በደሴቲቱ መኖር የመጀሩ ከአንጎላ ከሞዛምቢክ ከናሚቢያ የሄዱ ታዳጊዎችና ኩባውያን ሞቅ ያለ አቀባበል አደረጉልን።
በወጣቶች ደሴት በኩባ ሶሻሊስት መንግስት እና ኢትዮጵያውያን ታዳጊዎች የምንማርባቸው ካራማራና መንግስቱ ኃይለማርያም የተባሉ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ታንፀው ነበር የጠበቁን።
ከስደስት ወር በኋላ ተጨማሪ ሰኔ 21 እና ቆሬ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተገንብተው በሁለተኛ ዙር ከኢትዮጵያ ለመጡ ታዳጊዎችን ማስተማር መጀመራቸው አስታውሳለሁ።
በኩባ በነበረን ቆይታ እስከሁለተኛ ደረጃ ድረስ የኢትዮጵያን ታሪክ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ጂአግራፊ የሕብረተሰብ ትምህርት ከኢትዮጵያ በሄዱ መምህራን ሲያስተምሩን ሌሎቹ ትምህርቶች በስፓኒሽ ቋንቋና በኩባ ስርዓተ ትምህርት መሰረት ነበር ስንማር የነበረው ወደ ሁለተኛ ሀገራችን ኩባ ከሔድን የመጀመሪያዎቹ ከስድስት ወራት የስፓኒሽ ቋንቋ መናገር ማንበብና መፃፍ ተማርን። እስከዛሬ ድረስ እንደሕልም የሚታዩኝ በአይስላንደ ላእ ጁቬንቱዋድ እኛ ኢትዮጵያውያን ታዳጊዎች እንኖርባቸው የነበሩት አራት የሴት ታዳጊዎች ስምንት ወንድ ታዳጊዎች እንኖርባቸው የነበሩ የማደሪያ የመመገቢያ ሕንፃዎች የሕክምና መስጫ ክሊኒክና ሁልጊዜ ከደሴቲቱ ነዋሪዎች የምንለይበት የምንሰበስበው ዩኒፎርም የደንብ ልብሳችን ከብዙ ሺህ ኪሎሜር ከሀገራችን ርቀን መተሳሰብና መዋደዳችን ዛሬ በአጋጣሚ መንገድ ላይ ወይ በስራ አጋጣሚ ስንገናኝ እንደገና በትዝታ ባህር ውስጥ ይዘፍቀኛል።
በደሴቲቱ መኖር እንደጀመርን ከትምህርት በተጨማሪ የሕይወት ክህሎታችንን እንድናዳብር የሥራ ፍቅር እንዲኖረን ከትምህርት በኋላ ባለ የእረፍት ጊዜያችን በደሴቲቱ ባሉ የተለያዩ የአትክልትና ፍራፍሬ እርሻዎች ላይ እንድንሰራ ይደርግ ነበር።
በወቅቱ እንደ እኔ ወደ ኩባ የተላክን ኢትዮጵያውያን ታዳጊዎች ከለምለምዋ ከፀሐያማዋ የኩባ የአየር ንብረት ጋራ ለመለማድ ግልፅ እንግዳ ተቀባይ ከሆኑ ስለ አለም አቀፍ አጋርነት በቂ ግንዛቤ ካላቸው ኩባውያን ጋራ ለመግባባትና አብሮ ለመኖር እምብዛም አልተቸገርንም ነበር።
ሁልጊዜ የዕለቱ ትምህርት ከመጀመሩ በፊት የኢትዮጵያን ሕዝብ መዝሙር በመዘመር የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ ሰቅለን ነበር ወደ ክፍል የምንገባው። ትዝ ይለኛል። እዚያ ትምህርት እንደጀመርን ብዙም ሳይቆይ ነበር ሊቀመንበር መንግስቱ ኃ/ማርያም ሊጎበኙን ከፊደል ካስትሮ ጋራ ወደ ደሴታችን መጥተው ነበር። አባባ መንግስቱ! ፈገግታቸው እያንዳንዳችንን እየጨበጡ ገሚሶቻችንን ራሳችንን እየደባበሱ ደህና ናችሁ በደንብ ተማሩ! እያሉ የጠየቁን ያበረታቱን አጋጣሚ አልረሳውም።
እኛ ሲቆጡ እንደጥቁር ግስላ ያስፈራሉ የሚባሉ መንግስቱ ኃ/ማርያም እንደ በረዶ የነጣ ጥርሳቸውን ብልጭ እያደረጉ አንዳንዴ ደሞ ከት ከት ብለው ሲስቁ በአጭር ጊዜ ውስጥ ቋንቋ ለምዶን ከኩባው ፕሬዝዳንት ፊደል ካስትሮ ጋራ በስሜትና ያለምንም ፍርሃት ስናወራ በመገረም ተውጠው በዝምታ እንዴት ሲያዩን እንደነበር ዛሬ ትዝ ሲለኝ ያን ጊዜ ምን ያስቡ እንደነበር ባውቅ እያልኩ የጅል ምኞት እመኛለሁ።
እኔን ጨምሮ ብዙዎቻችን በኩባ በአይስላንድ ላ ጁቤንቱዋድ የኖረን የተማርን ኢትዮጵያውያን ለኩባና ለኩባውያን ልዩ ፍቅር አክብሮት አለን።
ከምንም በላይ ደሞ ለፊደል ካስትሮ ሩዝ ያለን ፍቅር አክብሮት ከፍተኛ ነው። ዛሬም ድረስ ምክንያቱም ገና ከስምንት አመቴ ብዙዎቻችን ልጅነታችን የእሱን ንግግር እየሰማን በቴሌቪዥን እያየን ነው ያደግነው።
ያኔ ፊደል ካስትሮ ንግግር በሚያደርግበት ወቅት ማንም ሰው እርስ በእርሱ እንኳን አያወራም በፀጥታና በፅሞና ሆኖ ንግግሩን እስኪያልቅ ድረስ ያዳምጣል።
ምክንያቱም ፊደል ከሚገባው በላይ ቀልብን የሚስብ የሚወደድ ተናጋሪ ነበር። በአያሌ ጉዳዮች ላይ ሰፊ እውቀት ያለው የማያነብ ሰው ሙሉ ሰው አይደለም የሚል እምነት ያለው አንባቢ ስለሆነ ሰለሞንም ነገር ማውራት ይችል ነበር።
ፊደል የወጣቶች ደሴትን በጣም ይወዳት ነበር በደንገት ወደደሴቲቱ ይመጣና ከእኛ ጋራ ምሳ ወይንም እራት እየበላ በደንብ ብሉ እንጂ ደሞ አንተኛው ወፍረሃል። ስፖርት ስራ እያለ ይቀልድ ነበር ብል ማን ያምነኛል። እውነትም ካስትሮ እጅግ የሚወደድ ስብዕና ያለው ሳቂታ ሰው ነበር። በኩባ ከ13 እስከ 15 ዓመት የኖርን የተማርን ኢትዮጵያውያን ያ ተመልሶ የማይመጣ ልጅነት አይነት በኩባ ያሳለፍነው ጊዜ በሕሊናችን ታትሞ አብሮን እንደሚኖር እርግጠኛ ስለሆንኩ ነው። የራሴን ትዝታ የእናንተም ነው እያልኩ የማካፍላችሁ።
ሁላችሁንም እንደምናስታውሰው ለተለያዩ ወጭዎች የሚያስፈልገን አነስተኛ የኪስ ገንዘብ ይሰጠን ነበር። በደሴቲቱ ላይ ካሉ የእኛ የኢትዮጵያውያን ጨምሮ 61 አዳሪ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የተለያዩ ሀገረ ዜጋ ታዳጊዎች የሚታደሙበት በየሳምንቱ የሚዘጋጁ የሙዚቃ ኮንሰርቶች ፓርቲዎች ካርኒቫሎች ላይ እንታደምነበር።
ታዲያ አልፎ አልፎ ኢትዮጵያውያን እህቶቻችንና ሊጠብሱ ሊያማልሉ ከሚሞክሩ አፍሪካውያን እኩዬዎቻችን ጋ ፀብ እየተፈጠረ ቅልጥ ወዳለ የቡድን ፀብ ድብድብ ተቀይሮ ለቅጣት ተዳርገን እንደነበር እኔ ዛሬ እንደ አዲስ ድርጊት ትኩስ ሆኖ ይታወሰኛል።
በአይስላንድ ላአ ጁቬንቱዋድ ደሴት ስንኖር ጥብቅ የሆነውን የትምህርት ቤታችን ደንብና ስርዓት በመጣስ ወደ ሀቫና እና ወደተለያዩ የኩባ ከተሞች እየሄዱ የሚዝናኑ ትምህርታቸውን የማይከታተሉ ሞገደኛ ታዳጊዎች እኩዮቻችን በፈፀሙት ጥፋት ተደርሶባቸው ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት ሲቀጡ ገሚሶቹ ከጥፋታቸው ባለመታረማቸው በድጋሚ በመገኘታቸው ከትምህርት ቤቱ ተባረው ወደ ሀገር ቤት እንዲመለሱ ተደርገው ነበር።
ከነዚህ ወደ ሀገር ቤት ከተላኩ ጓደኞቻችን መካከል ፆታዊ ግንኙነት ጀምረው ማርገዛቸው ተደርሶበት ትምህርታቸው አቋርጠው ወደ ሀገር ቤት እንዲመለሱ የተደረጉ እህቶቻችን እጣ ፈንታ አሁን ድረስ ያሳዝነኛል ለመሆኑ ከዚያ በኋላ እንዴት ሆነው ይሆን ? ብዬ ራሴን እጠይቃለሁ።
ፊደል ካስትሮ ገና በወጣትነቱ አብዮተኛውን የኩባ ወጣት ለለውጥ ለሶሻሊዝም መርህ ሲያስተባብር በመገኘቱ ለ19 ወራት ታስሮባት የነበረውችው በሕይወቱ ልዩ ትዝታ ባላት በዚያች የወጣቶች ደሴት ያደግን የተማርን ኢትዮጵያውያን ዛሬ በኢትዮጵያና በሁለተኛዋ ሀገራትን መካከል ያለው ወዳጅነት ግንኙነት እንዲጠናከር መገናኛ ድልድይ የመሆን ሚና መጫወት እንዳለብን በፅኑ ከሚያምኑ የኩባ ተማሪዎች ውስጥ አንዱ ነኝ።
የኩባ ሕዝብና መንግስት በኢትዮ ሱማሊያ ጦርነት ወቅት ወላጆቻችንን ያጣነውን በብዙ ሺህ የምንቆጠር ኢትዮጵያውያንን በነፃ አስተምሮ ለቁም ነገር እንድንበቃ በማድረጋቸው የማንከፈለው ውለታ አለብን ብዬ አላበቃም።
ኩባውያን ወታደሮች ዚያድ ባሬ በግፍ በእብሪት ሀገራችንን በወራራ ወቅት ከእኛ ከኢትዮጵያውያን ጋራ ትከሻ ለትከሻ ተደጋግፈው ተፋልመዋል። ምናልባት ትክክለኛውን ቁጥር አላውቀውም እንጂ በመቶዎች የሚጠጉ ኩባውያን ወታደሮች ለኢትዮጵያ ሲሉ ሕይወታቸውን ገብረዋል ዘላለማዊ ክብር ልንሰጣቸው ይገባል።
ብዙዎቻችን የአይስላንድ ላ ጁቬንቱ ዋድ ያደግን የተማርን ኢትዮጵያውያን አንድ የሚያመሳስለን እምነት አቋም ያለን ይመስለኛል። እናንተ ከየት ናችሁ ብንባል ኢትዮጵያዊም ኩባዊም ማንነት ያለን የሁለት ሕዝቦች ቅይጥ ማንነት ባለቤቶች አድርገን ራሳችንን እንደምናይ እርግጠኛ ነኝ።
ዛሬ በብዙዎቻችን በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ላይ ተሰማርተን ሀገራዊ ግዴታችንን እየተወጣን ነው ያለነው። ትምህርታችንን ጨርሰን ወደ ሀገር ቤት የመጣን ሰሞን ምናልባትም ለወራትና ለአመታ በስራ እጦት እንዲሁም ትተነው ከቆየነው ማኅበረሰብ ጋራ ለመቀላቀል ተችግረን ነበረ እናም በነዚያ በችግር ጊዜያት በአይስላንድ ላ ጁቬንቱ ዋድ ያደግን የተማርን ሁላችንም ያገኘነውን እየተካፈለን በፅናት ያንን ችግር አሳልፈን እንደነበረ ሳስታውሰው እንባ ይተናነቀኛል።
በሥራ አጋጣሚ ወደ ተለያዩ የአውሮፓ ሀገራት አሜሪካ ባደረኳቸው ጉዞዎች በስፔን፣ በአሜሪካ በሆላንድ በሌሎች የስካንዴቬያን ሀገሮች በተለያዩ ሙያ የተሰማሩ የተሳካላቸው የአይስላንድ ላጁ ቬንቱዋድ አብረን ያደግን ልጆችን ሳገኝ ለአመታት የተለያየ መንታ ወንድሙን እንዳገኘ የሚያስደስተኝ ጥልቅ የፍቅር መንፈስ ቀስቅሶኝ ነው። ከባህር ማዶ በግዮን በኩል ይህንን ጦማር የሰደድኩት። እናንተስ? ■

# መስዋዕትነቱ ለምን ነበር?

በቀለ ገሠሠ (ዶ/ር)

## መንደርደሪያ፤

ከተገንጣይ ቡድኖች በስተቀር በ50ዎቹና 60ዎቹ የተጀመሩት እልህ አስጨራሽ ትግሎች ታላቅ አገራዊ ራዕይ ነበራቸዉ። እነዚህም በዉድ አገራችን የዲሞክራሲን ሥርዓት ለመገንባት፤ እኩልነት ለማስፈንና ዘለቄታ ያለዉን ዕድገት ለማምጣት ነበር። ይህ ግብ ባለመሳካቱ ምክንያት አንዳንድ ሰዎች የየግላቸዉን ፍላጎት ለማሳካት የተዛባ ትንታኔ ለማቅረብ ይሞክራሉ። በዚህም ላይ ወደኋላ እየተመለከቱ እንዲህ ቢሆን፤ እንዲያ ቢሆን ይሻል ነበር ብሎ መፍረድ ይቀላል። ዋናዉ ነገር ግን በወቅቱ መደረግ የሚገባዉን መልካም ነገር መሞከሩ ላይ ነዉ። በእርግጠኝነት ለመናገር የሚቻለዉ ግን በህዝብ ጎን የተሰለፉት ወጣቶችና መሪዎች ወቅቱ የፈቀደዉ ከፍተኛ ንቃተ ኅሊና የነበራቸዉ፤ ለህዝብ እኩልነትና ለአገር ዕድገት ከፍተኛ ራዕይ የነበራቸዉና ለዚህም የተቀደሰ ዓላማ ከፍተኛ የሕይወት መስዋዕትነት ለመክፈል ቆርጠዉ የተነሱና የከፈሉ ብሩህ ዜጎች መሆናቸዉን ነዉ። የጎሳ አባዜ ያልተጠናወታቸዉ፤ ሃይማኖት ያልከፋፈላቸዉና ዕድሜ ያልገደባቸዉ ንፁሓን ዜጎች ነበሩ። ምንም እንኳን በወቅቱ ብዙ ተሞክሮዎች ባይኖሩም የተደረጉት ሙከራዎችና የተከፈለዉ መስዋዕትነት ለአንድነት፤ ለእኩልነትና ለአገር ግንባታ ነበር። ‘ድር ቢያብር አንበሳ ያስር’ ይላል ያገራችን ሰዉ። ቀላል አባባል አይደለም። በትብብር ነበር አገራችን ነፃነቷን ጠብቃ የቆየችዉ። እንደዚያ ባይሆን ኖሮ በተለያዩ ወቅቶች አንጃብበዉ የመጡብን የተለያዩ የዉጪ ጠላቶች በቀላሉ ድምጥማጣችንና ታሪካችንን ለማጥፋት በቻሉ ነበር። ግን አልቻሉም፤ ለፈጣሪያችን ታላቅ ምስጋና ይግባዉና።በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ብዙ ግንባታዎች ታይተዋል። ነገር ግን የወቅቱ ዋና ጥያቄዎች የሆኑት የመሬት ሥሪትና የዲሞክራሲ ጉዳዮች አልተመለሱም።ሥርዓቱ ከማርጀቱ የተነሳ እነዚህን ጥያቄዎች በአግባቡ ለመመለስ አልቻለም። ቀጥሎ የመጣዉ የወታደር አምባገነን ሥርዓት ሆነ። እርሱ ደግሞ ቀኑን ጠብቆ ሲሄድ ህዝቡን በጎሳና ኃይማኖት ከፋፍሎ የሚገዛ የኢሕአዴግ አምባገነን ቡድን ተቀመጠ። ከ27 ዓመታት ትግል በኋላ እርሱም ተዳከመ። ለዉጥ ሊደረግ ነዉ ሲባል ብዙ ሰዉ ትልቅ ተስፋ አደረገ። ሆኖም ግን ከባድ ችግሮች ይታያሉ። ዛሬ በግፍ የሚፈሰዉ የንፁሐን ደም፤ የሚታገቱት ተማሪዎች (በተለይ ሴቶች)፤ የሚፈናቀለዉ ዜጋና የሚቃጠሉት አቢያተ ክርስቲያናትና መስጊዶች እጅግ በጣም ያሳዝኑኛል። በመሻሻል ምትክ ሁኔታዎች እንደዚህ እየተባባሱ መሄዳቸዉን ስመለከት ሰዉ ሆኜ መፈጠሬን ያስጠላኛል፤ እጅግ በጣም ያሳፍረኛል። ቶሎ መቆም አለባቸዉ። ካለበለዚያ ሰላም አይኖርም። ሰላም ሳይኖር ምርጫም ሆነ ዕድገት በቅጡ ሊሳካ አይችልም።

## ፩ኛ/ የጠንካራ ሽግግር መንግሥት አስፈላጊነት፤

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ማብቂያ ላይ የተጠየቀዉ ትክክለኛ ጥያቄ ወደ ዲሞክራሲ ሊመራ የሚችል የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ምስረታ አስፈላጊነት ነበር። ወታደሩ ግን ይሄን ጥያቄ ከለከለ። ከዚያ በኋላ የተከተለዉን አሰቃቂ እልቂት ታሪክ ቁልጭ አድርጎ አስቀምጦታል። ለ27 ዓመታት ገደማ በወያኔዎቹ ሲመራ የነበረዉ የኢሕአደግ መንግሥት በአገሪቷ ከላይ እስከታች በተቀጣጠለዉ ተቃዉሞ ሲዳከም ለዉጥ ሊመጣ ነዉ ተባለ። ኢሕአደግ ከልቡ ከጥፋቶቹ በመማር ጠንካራና ሁሉ-አቀፍ የሆነ የሽግግር መንግሥት ተቋቁሞና እርቀ ሰላም ወርዶ ወደ ትክክለኛዉ ዲሞክራሲ እናመራለን ብለን ተስፋ አድርገን ነበረ። ይሄ ግን አለመሳካቱ እጅግ በጣም ያሳዝናል። ቢሳካ ኖሮ ዛሬ የምናያቸዉ እጅግ አሰቃቂ ክስተቶች ባልተፈጠሩ ነበር። ከእጃችን የወጣ ወርቃማ ዕድል አድርጌ ነዉ የምቆጥረዉ። አሁንም በእጅጉ ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነዉ ብዬ አምናለሁ።

## ፪ኛ/ ሕገ መንግሥት የማሻሻል አስፈላጊነት

ጎሳና ኃይማኖትን በተመለከተ በአገራችን ዉስጥ ከባድ አለመግባባትና ግጭቶች እየተፈጠሩ ናቸዉ። በቅርቡ ሕዝቡን ከፋፍለዉ ለመግዛት የረጩት መርዝ ነዉ እንጂ በቀደሙት ዘመናት እንደዚህ ዓይነት ግጭቶችና እልቂቶች አላየንም፤ አልሰማንም። አማራዉ፤ ትግሬዉ፤ ኦሮሞዉ፤ ወዘተ የርስ በርስ ጠላትነት አልነበራቸዉም። የጋራ ችግራቸዉ የዲሞክራሲ አስተዳደር እጦት ነዉ (በፊት በባላባታዊ፤ ቀጥሎ በወታደራዊ አምባገነን፤ በኋላ ደግሞ ከፋፍሎ በሚገዛዉ የጎሳ አምባገነንነት ምክንያት)። እንደዚሁም ኦርቶዶክስ ሃይማኖት የማንኛዉም እምነት ጠላት ሆኖ እንደማያዉቅ የአገራችን ታሪክ ቁልጭ አድርጎ አስቀምጦታል፤ እኛም ሕያዉ ምስክሮች ነን። ሕገ መንግሥት በግልፅ ማስቀመጥና ማረጋገጥ ከሚገባቸዉ ዐበይት ነገሮች መካከል የሚከተሉትን የእያንዳንዱን ዜጋ መሰረታዊ ሰብዓዊ መብቶች ይጠይቃል፤

የጎሳን ግጭት ማስወገድ፤

የእያንዳንዱን ሃይማኖት ነፃነት ማክበርና ማስከበር ይሆናሉ።

በዚህም ሂደት ዉስጥ ሁሉም ዜጎች እኩል መሳተፍ ይገባቸዋል።

## ፫ኛ/ አገራዊ ምርጫን በተመለከተ

ከዚያ ሁሉ ረዥምና እልህ አስጨራሽ ትግልና መስዋዕትነትም በኋላ እስከዛሬ ድረስ በአገራችን ዉስጥ ነፃ ምርጫ ተካሂዶ አያዉቅም። በእነኬኒያ፤ ደቡብ አፍሪቃና ጋና ያሉትን የዲሞክራሲ ግንባታዎች ስመለከት የኛ ኋላ ቀርነት እጅግ በጣም ያሳዝነኛል፤ ያስገርመኛል፤ ያሳፍረኛልም።በ97ቱ ምርጫ ትንሽ ለቀቅ ያደረጉ አስመስለዉ ነበር። ድምፅ ቆጠራዉን ግን አጭበርብሮ አምባገነኑ ኢሕአዴግ ራሱ መልሶ ጠቀለለዉ። የአሁኑስ ምርጫ ምን ሊሆን ነዉ? ምርጫ እንዲሳካ መስተካከል የሚገቧቸዉ አንዳንድ ቅድመ ሁኔታዎች አሉ። ተቃዋሚ ድርጅቶች በሁሉም የአገሪቷ ክፍሎች በነፃ መንቀሳቀስና ዓላማቸዉን ለሕዝቡ ለመግለፅ የሚችሉበት ዕድል መኖር አለበት። እስከዞን፤ ወረዳና ቀበሌ ድረስ ነፃ የሆኑ የምርጫ አስፈፃሚ ተቋማት መኖር ይገባቸዋል። ዛሬ እኮ ተማሪዎች እንኳን እየታገቱ መድረሻቸዉ የማይታወቅበት እጅግ አሳዛኝና አስደንጋጭ ሁኔታ ዉስጥ ነዉ ያለነዉ። ታዲያ በዚህ ሁኔታ ነፃ ምርጫ ይካሄዳል ብሎ መጠበቅ ይቻላል ወይ? እንደእኔ አስተያየት ከምርጫዉ በፊት እላይ ባጭሩ የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች ቢስተካከሉ ይሻላል ብዬ አምናለሁ።

## ፬ኛ/ ዘለቄታ ያለዉን ዕድገት ለማምጣት፤

ዘለቄታ የሚኖረዉን አገራዊ ዕድገት ለማምጣት ብዙ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት ይጠበቅባቸዋል። ከእነዚህም መካከል፤ አርሶ ለማምረት ሰላምና እርጋታ ያስፈልጋሉ፤ ሕዝቡ እርስ በርሱ እየተጋጨና እየተፈናቀለ በሰላም አርሶ ማምረት እንደማይችል ግልፅ ነዉ። በዚህም ላይ ደኖቻችን ክፉኛ ተጨፍጭፈዋል፤ አፈሮች ተሸርሽረዋል፤ የአየር ንብረት እየተቃወሰ ይገኛል። የገጠር ገበሬዎች አርሰዉ ምርታቸዉን ለማሳደግ እንዲችሉ ብዙ ሙያዊና መንግሥታዊ ዕርዳታዎች ያስፈልጓቸዋል። ባገር ዉስጥ ሰላምና እርጋታ ሳይኖሩ እነዚህን ድጋፎች ማዳረስ አይቻልም፤ አገር ሊገነቡ የሚችሉ የተማሩ ኃይሎች መሰብሰብና ማሰማራት ከባድ ነዉ። ነግደዉም ለመብላት ዜጎች በአገራቸዉ ውስጥ በነፃ የመንቀሳቀስ ዕድል ያስፈልጋቸዋል፤ ዛሬ እነዚህ ዕድሎች በሰፊዉ አይታዩም። ተምረዉ ለመሥራት ወጣቶች ሰላምና እርጋታ ያስፈልጋቸዋል። በተፃራሪዉ ግን ብዙ የዩኒቬርስቲ ተማሪዎች እየተገደሉና እየታገቱ ይገኛሉ። ወጣቶች በገዛ አገራቸዉ ተምረዉና ተመርቀዉ መሥራት ካልቻሉ ዕጣ ፈንታቸዉ ያዉ የተለመደዉ ስደትና እንግልት ነዉ። ይሄ ችግር ቶሎ መቀረፍ አለበት። ይሄ ካልሆነ አገርስ እንዴት ሊታድግ ትችላለች? የግድብ ሥራዎች ለማሳካት ሰላምና ጠንካራ አንድነት ይጠይቃል። የዉጪ ጠላቶች ራሳችንን እንድንችል አይፈልጉም። ማንንም ሳንጎዳ ወንዞቻችንን እንኳን ገድበንና ተጠቅመን ከችጋርና ከጭለማ እንድንወጣ አይፈልጉም። የአገራችን ነፃነት ተከብሮ እስከዛሬ ድረስ የቆየዉ በአንድነታችንና በእግዚአብሔር ፈቃድ ነዉ። አሁንም ያንን አንድነት መልሰን መገንባት ይኖርብናል። ካለዚያ የታወቁት የዉጪ ታሪካዊ ጠላቶቻችን እየከፋፈሉን ቡችሎች አድርገዉ ያስቀሩናል።

## ፭ኛ/ መደምደሚያ

በቀደሙት ጽሑፎቼ ደጋግሜ ለማስተላለፍ እንደሞከርኩት፤ እንኳንስ አገራዊ ሁከት ተጨምሮበት ይቅርና በሰላምም እንኳን ካለንበት የኋላ ቀርነት ለመላቀቅ ቀላል ሥራ አይሆንም። የዉጪ መንግሥታት የየራሳቸዉን ጥቅም ነዉ የሚያስቀድሙት። እኛ ተባብረን መበርታት ይኖርብናል። ለመሬት ላራሹና ለዲሞክራሲ ግንባታ ያ ትዉልድ የከፈለዉን ከፍተኛ መስዋእትነት ታሪክ ሲያስታዉሰዉ ይኖራል። ከዚያ ሁሉ ጥረትና መስዋዕትነት በኋላ ከአሁኑ የተሻለ ሁኔታ ነበር የጠበቅነዉ። አለመሆኑ እጅግ በጣም ያሳዝናል፤ያሳፍራል። ዛሬ በዉዲቷ አገራችን ላይ ጥቁር ደመና ተጋርጦባታል። ከስህተቶችና ጥፋቶች መማር ይገባናል። አያቶቻችንና ቅድመ አያቶቻችን ደማቸዉን አፍስሰዉ አጥንታቸዉን ከስክሰዉ በነፃነት ያቆዩዋት ቅድስት አገር በሁላችንም ትብብር ህልዉናዋ ተረጋግጦ አብባ ለዘለዓለም እንድትኖር ለማድረግ ኃላፊነቱ የሁላችንም መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል። ዉድ አገራችን ለልጆቻችንና ለሚቀጥሉትም ትዉልዶች መትረፍ ይኖርባታል። ቁጭ ብለን ሁኔታዎች እስከሚባባሱ ድረስ መጠበቅ አይኖርብንም። በዚያች ምድር አንድም ዜጋ በጎሳ ምክንያት መገደል፤ መታገት ወይም መፈናቀል የለበትም። ማንኛዉም ቤተ እምነት መነካት የለበትም። ተያይዞ መጥፋት ለምን ይመረጣል? ለማያዉቁት ማስተማር ነዉ። እያወቁ ሽብር የሚፈጥሩትን ለፍርድ ማቅረብ ነዉ። ሩዋንዳን ከመሳሰሉ የዓለም ታሪኮች መማር ይኖርብናል። ►

# የቅናት ዛር



ኢ/ር ወንድሙ ነጋሽ
(የሥነ አዕምሮ ተመራማሪ)

## ለመኾኑ ቅናት ምንድነው?

ቅናት ተፈጥሯዊ የኾነ የሰው ልጅ ስሜት ነው፡፡ በሰዎች ላይ የምናየው መልካም ነገር በኛ ላይ እንዲኾን ስንመኝ መንፈሳዊ ቅናት እንለዋለን፡፡ የኛ ያልነውን ነገር ሌሎች ሊጋሩን ይችላሉ ብለን ስንሰጋ ደግሞ ቅናት ይሆናል፡፡ የፍቅር አጋራችንን ሌላ ሰው እንዲመኝብን አንፈልግም፤ ይህ እንደኾነ ባሰብን ጊዜ ቅናት ያንዘረዝረናል፡፡ ኾኖም በአንዳንድ ባህል አንድ ወንድ ብዙ ሚስቶችን የማግባት ልምድ ስለሚኖረው በሚስቶች መካከል ያን ያህ ል የተጋነነ መቀናናት ላይታይ ይችላል ፡፡

የቅናት ምንጩ ለራስ ዝቅ ያለ ግምት መኖርና የደኅንነት ስሜት ማጣት ነው፡፡ በእርግጥ ጤናማ ቅናት ግንኙነትን የማደርጀት ሚናን የሚጫወትበት አጋጣሚ አለ፡፡ ለምሳሌ አንድ ወንድ ሚስቱ እንዴትም ብትኾን፣ ከማንም ጋር ብትተኛ፣ ማንም ከንፈሯን ቢስም ምንም ዓይነት ስሜት የማይፈጥርበት ከኾነ ጤናማ ስሜት አይደለም ያለው፡፡ የፍቅር ግንኙነቱ ላይ ጥያቄ የሚያነሱ ሰዎችም አይጠፉም፡፡ ቅናት ጤናማ የሚኾንባቸው አጋጣሚዎች እንዳሉ ሁሉ መጠኑ ያለፈ ቅናት በግንኙነት ላይ ጥላ ሊያጠላ ይችላል፡፡

የአእምሮ ሊቃውንት ይህን መጠን ያለፈ የቅናት ዛር "morbid Jealousy" በማለት ይጠሩታል፡፡ ይህ ዓይነቱ ቅናት በጊዜ ካልታከሙት ሞትን የሚያክል አደጋን ሊያስከትል ይችላል፡፡ በሀገራችን ላይ የሚፈጸሙ ፍጹም አሰቃቂ የጾታ ወንጀሎች በአመዛኙ መነሻቸው ቅናት ለመኾኑ እማኝ መጥራት አያሻም፡፡

ቅናትን ጤናማ የምንለው መቼ ነው?

የቀድሞ ባለቤትህ ካንተ ጋር ባለመግባባት ምክንያት በሰላም ብትለያዩና ኾኖም ከሌላ ወንድ ጋር የተቃና ትዳር መስርታ በፍጹም ምቾትና ተድላ ላይ ኾና ድንገት መንገድ ላይ ብታገኛት ስስ ቅናት አእምሮህ ላይ ሽው ሊልብህ ይችላል፡፡ ይህ የቅናት ስሜት ለምን ተሰማኝ ብለህ ራስህን ማውገዝ አይኖርብህም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ መጠነኛ ስሜት ጤናማ ቅናት እንለዋለን፡፡ በማንም ላይ የሚከሰት በመኾኑ አደጋ የለውም፡፡ ችግር የሚኾነው ይህ ጤናማ ቅናት ከዚህ ከፍ ወዳለ የቅናት ደረጃ ሲያድግ ነው፡፡

እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብህ ይህ የቅናት ስሜት ተራ ስሜት እንዳልኾነ ነው፡፡ የምንወደውን ሰው የሌላ ኾኖ ስ ናየው ያመናል፡፡ ነገር ግን አእም ሯችንን መግራት የሚኖርብን በዚህ ደ ረጃ ነው፡፡ ጤናማ ያልኾነውን የቅናት ዛር የአእምሮ ሊቃውንት በሁለት ከፍለው ይመለከቱታል፡፡ ይኸውም፦

### 1. ስግብግባዊ ቅናት (obsessional Jealousy)

አንድ የቅናት ስንጥር አእምሮ ውስጥ ትሰነቀራለች፡፡ ይቺ ስንጥር ያለ የሌለውን ሀሳብ ሁሉ አግበስብሳ ትመጣለች፡፡ ምንም እንኳ የምትሰነቀር ሀሳብ እንጂ በእውን ያልተከሰተች እንደኾነ ቢታወቅም እሷን ከአእምሮ መንግሎ ማውጣት ግን የማይታሰብ ነው፡፡ ይቺ ቅናት አእምሮ ላይ ከተሰነቀረች ስለሷ ማሰብ ማቆም ፈተና ነው፡፡

ለምሳሌ ሚስትህ ከቀድሞ ፍቅረኛዋ ጋር በድብቅ እየተገናኘች እንደሆነ ካሰብክና ይህ ሀሳብ አንድ ጊዜ ወደ አእምሮ ከገባ ከፍተኛ መረበሽ ይፈጠራል፡፡ ስልኳን በድብቅ መበርበር፤ የተለዋወጠቻቸውን የጽሑፍ መልዕክቶች ማንበብ፣ የደበቀቻቸው ደብዳቤዎችና ፎቶዎች ካሉ መፈተሽ፣ በምትሄድበት ቦታ ሁሉ በድብቅ ኾኖ መከታተል የዕለት ተዕለት ሥራ ሊኾን ይችላል፡፡ በእርግጥ አንተ ይህ ዝም ብሎ የተሰነቀረ ሀሳብ እንደሆነ ውስጥ ዉስጡን ብትረዳም እንኳ ነገሩን ከማሰብና ከማብሰልሰል አትቦዝንም፡፡ በዚህ ፈታኝ ወቅት አይበለውና ባለቤትህ ለቀድሞ ፍቅረኛዋ የ "እንኳን አደረሰህ" የጽሑፍ መልዕክት ልካ ስልኳ ላይ ብታገኝ ይህንን የምትተረጉመው ከርሱ ጋር በድብቅ እየማገጠች እንደሆነ አድርገህ ነው፡፡ ስለሆነም ሳታስበው እርሷ ላይ ከፍተኛ አደጋ የማድረስ ሰይጣናዊ ስሜት ዉስጥ ትገባለህ፡፡ በአገራችን በተደጋጋሚ ባሎች ሚስቶች ላይ አሲድ መድፋት፣ ዐይን ጎልጉሎ ማውጣት፣ በእሳት ማቃጠል፣ በስለት መውጋት ወዘተ አደጋዎችን ለማድረሳቸው አንዱ ምክንያት ስግብግባዊ ቅናት በሚባለው ደዌ በመጠቃታቸው ነው፡፡ የሚገርመው በዚህ ስግብግባዊ በሚባለው የቅናት ዓይነት ስለምንቀናበት ሰው አእምሮ እየፈጠረ የሚያቀርብልን ሀሳብ ፍጹም እውነት እንዳልሆነ ብንጠረጥርም ሀሳቡን ግን በቀላሉ ከአእምሮ መንጭቆ ማዉጣት አንፈልግም ወይም አንችልም፡፡

### 2. እብደታዊ ቅናት (Psychotic/Delusional Jealousy)

በዚህ እብደታዊ የቅናት ዛር የተጠቃ ግለሰብ አእምሮው የፈጠረለትን ማንኛውንም ቅዠት አምኖ ይቀበላል፡፡ በተጨባጭ የሚታይ ማስረጃ ባይኖርም የሆነ ጉዳይ እንዳለ እርግጠኛ ይኾናል፡፡ ለምሳሌ ከላይ በመግቢያችን ላይ የጠቀስነው የኢሳያስ የቅናት ዓይነት ከዚህ ሊመደብ የሚችል ነው፡፡ ኢሳያስ ምንም አንኳ በመጠጥ ኃይል ተገፋፍቶ ቢኾንም የባለቤቱ የውስጥ ሱሪ ላይ የወንድ ፈሳሽ ማየቱን ምሎ ተገዝቶ ይናገራል፡፡ የኾነ እንግዳ ወንድ ወደሚስቱ አቅጣጫ ዞሮ ፈገግታ ካሳየ ባለቤቱ በድብቅ እየወሸመችበት እንደኾነ መቶ በመቶ እርግጠኛ ይኾናል፡፡

ሌላ ከላይ ያልጠቀስነውን የኢሳያስ አጋጣሚ እዚህ ጋር እናንሳ፡፡ ኢሳያስ ዕሁድ ምሽት ቤት እንደገባ ልጆቹን ስሞ ቀና ሲል ሚስቱን ያጣታል፡፡ የት ሄደች ብሎ ሲጠይቅ ማዕድቤት እራት እያበሰለች እንደኾነ ይነገረዋል፡፡ ትንሽ ቆይታ እንደተባለውም ከማዕድቤት ትወጣለች፡፡ በዚህ መሐል የሳሎኑ ስልክ ያቃጭላል፡፡ እርሷ ልታነሳው ስትል "ግዴለም እኔ አነሳዋለሁ፤አንቺ ስራሽን ቀጥይ" ብሎ የስልኩን እጀታ ያነሳል፡፡ "ሀሎ" ሲል ከወዲያኛው የሚመጣ ድምጽ ድንገት ይቋረጣል፡፡ በዚህን ጊዜ አእምሮው ለኢሳያስ ቆንጆ ታሪክ ፈጥሮ ሹክ ይለዋል፤ እንዲህ የሚል-"ባለቤትህ በስልክ ከውሽማዋ ጋር ስትዳራ ነበር፤ ስልኩን የዘጋው አንተ መኾንህን ስላወቀ ነው፡፡…" በእብደታዊ የቅናት ዛር አንድ ጊዜ የተለከፉ ሰዎች መጨረሻቸው ዘብጥያ መውረድ ሊኾን ይችላል፡፡ ፍፁም ሰላም አይሰማቸውም፡፡ ፍጹም ተጠራጣሪዎች ናቸው፡፡ ባለቤታቸውን የምድር ገሀነም ውስጥ ይከታሉ፡፡ እነርሱ በሚፈጥሩት የማይጨበጥ ታሪክ ቤተሰብ ይበጠብጣሉ፡፡ በጊዜ መፍትሄ ካልተበጀ የዚህ ዛር መጨረሻ አያምርም፡፡

### ታዲያ ምን ተሻለ?

በቅናት ዛር የሚሰቃዩ ሰዎች እነርሱ ትክክል እንዳልኾኑ አያስቡም፤ ቢያስቡም ትክክል እንዳልኾኑ ማሰብ አይፈልጉም፡፡ ስለዚህ በሚጠረጥሯቸው ሰዎች አልያም በራሳቸው ላይ ከፍተኛ ጉዳት ለማድረስ ይነሳሳሉ፡፡ ከዚህ ደዌ ለመዳን የግድ ሆስፒታል መግባት ላያስፈልግ ይችላል፡፡ ቀስ በቀስ ራስንና አእምሮን በመግራት በቀላሉ ወደ ጤናማ መስመር መግባት ይቻላል፡፡ ኾኖም ራስ ላይ ወይም ሌሎች ላይ ጉዳት የማድረስ መጥፎ ስሜት ከተስተዋለ ሐኪም መጎብኘቱ ለነገ የሚባል መኾን የለበትም፡፡

### ተመራጩ ሕክምና

በዚህ የቅናት ዛር በሽታ ለሚሰቃዩ ሰዎች እንደ የአስተሳሰብ መግራት ሕክምና (Cognitive Behavioral Therapy) ፍቱን ሕክምና አለ ለማለት ያስችግራል፡፡ ይህ ሕክምና እንዴት እንደምናስብ ብሎም ለምን አንድን የተለየ ባሕሪ እንደምናሳይ የሚያስረዳና ወቅታዊ ችግርን መሰረት አድርጎ አስተሳሰብን የሚገራ የአእምሮ ሕክምና ነው፡፡ በዚህ ዙርያ የበለጠ ግንዛቤ ለማግኘት (የአእምሮ ጉዳይ 2- አስተሳሰብን የመግራት ሕክምና) የሚለውን መጽሐፍ ማንበብ ይመከራል፡፡

መድኃኒቶች

ለዚህ የቅናት ዛር በሽታ የሚሰጡ እንክብሎች አሉ፡፡ ለምሳሌ አንቲዲፕሬሳንት እንክብሎች የቅናቱ ምንጭ ከደብታ ጋር የተያያዘ ከኾነ ዉጤታማ ይሆናሉ፡፡ የቅናት ዛሩ ምንጭ እስኪዞፎርኒያ ወይም ደግሞ እብደታዊ ቅናት ከኾነ አንቲሳይኮቲክ መድኃኒቶች ይበልጥ ዉጤታማ ይኾናሉ፡፡ እነዚህ መድኃኒቶች በእንክብል መልክ የሚሰጡ ቢኾንም በየ3 እና 4 ሳምንታት አንድ ጊዜ ብቻ የሚወሰዱ የመርፌ ሕክምናዎችም እንደ አማራጭ ተቀምጠዋል፡፡

አንዳንድ ጊዜ የቅናት መጠኑ ሌላን ሰው ለመጉዳት የሚዳርግ ከኾነ በሌሎች አገሮች ፖሊስ ታካሚውን ያለርሱ ፍቃድም ቢኾን ወደ ሕክምና ጣቢያ የመውሰድ ግዴታ ይኖርበታል፡፡ በአገራችን ከዚህ ቀደም በስፋት እንደታየው እብደታዊ ቅናትን መሠረት አድርገው የሚመሠረቱ የፖሊስ ጣቢያ ክሶች "ምንም የሚታይ በተጨባጭ የደረሰ ጉዳት የለም" በሚል ቸልተኛ አካሄድ የተነሳ በጊዜው ማቆምና በአጭር መቅጨት እየተቻለ የሰው አካል ጎድሏል፡፡ ይህ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ኾኖ ይሰማኛል፡፡

ወላጆች፣ ቤተሰብና ዘመድ አዝማድ በአንድ ግለሰብ ላይ ይህ ጤናማ ያልኾነ መጠኑ ከፍ ያለ የቅናት ዛር ሲፈጠር ነገሩን ለወሬ ፍጆታ ብቻ ከማዋል መታቀብ ይኖርባቸዋል፡፡ "አበደላት! ሞተላት" የሚሉት ገለጻዎችም ችግሩን አቅልሎ የማየት ዝንባሌዎች ናቸው፡፡ ሴቶችም ቢኾኑ ወንዶች እንደዚያ ሲኾኑላቸው "ስለሚወደኝ ነው እንዲህ የኾነልኝ" ብለው ከማሰብ በዘለለ ለነገሩ ልዩ ትኩረት ቢሰጡ የተሻለ ነው፡፡ ይህ ለሁለቱም ጾታ የሚሰራ ጉዳይ እንደሆነ ልብ ይሏል፡፡

ብዙ ጾታዊ ጥቃቶችን ባለፉት ጥቂት ዓመታት ብቻ ሰምተናል፡፡ በቅናት ተነሳስቶ አባት፣ እናትና ሁለት የቤተሰብ አባላትን የገደሉ ከአንድም ሁለት ሦስት አጋጣሚዎችን በብሔራዊ ቴሌቭዥን ተመልክተናል፡፡ ከነዚህ አጋጠሚዎች ትምህርት ካልወሰድን ግን ማየታችን በራሱ የሚያመጣው ለውጥ የለም፡፡ በእብደታዊም ኾነ በስግብግባዊ ቅናት አንድ ጊዜ የተለከፈ ሰው ተገቢውን ክትትል ካልተደረገለት የሚያደርሰው አደጋ በፍጹም ቀላል ተደርጎ መታሰብ የለበትም፡፡

በመንግስት በኩል እንዲሁም ሴቶች ላይ የሚሰሩ ግብረሰናይ ድርጅቶች ወንዶች እንዲህ ዓይነቱን በቅናት ተነሳስቶ ዛቻና ማስፈራሪያ የጀመሩ ባሎችን በሕግ ክትትል ስር ለማድረግ የሚያስችሉ የሕግ ማዕቀፎች የሚቀረጹበትን ሁኔታ ማመቻቸት ሀገራዊ ሀላፊነትን እንደመወጣት የሚቆጠር ነው፡፡

# ‹‹የአውሮፕላን ነዳጅ ማከማቻ ገበያን ስንቀሳቀል የተለያዩ የአሰራር ችግሮች ገጥመውናል››

## አቶ ሐራጎ ፈለቀ

አቶ ሐራጎ ፈለቀ የ‹‹ታፍ ኦይል›› አጠቃላይ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡ "ታፍ ኦይል"( TAF Oil ) በቅርቡ በኢትዮጵያ አየር መንገድ (በቀድሞው የጉምሩክ ግቢ ውስጥ) ካስገነባው የነዳጅ ማከማቻ ዴፖ ውስጥ አንዱ ሲሆን ምን ዓይነት ሥራዎችን ሰርቶ ዛሬ ላይ እንደደረሰና መሰል ጉዳዮችን ከግዮን መጽሔት ጋዜጠኛ ሙሉጌታ አክሊሉ ተከታዩን ቆይታ አድርገዋል፡፡

**ግዮን፡- ታፍ ኦይል በኢትዮጵያ አየር መንገድ ግቢ ውስጥ የነዳጅ ማከማቻ ካቋቋመ ምን ያህል ጊዜ ሆነው?**

አቶ ሐራጎ፡- ከተቋቋመ አጭር ጊዜ ነው፣ 10 ዓመት ይሆነዋል፡፡ 2ቱን ዓመት ፎርማሊቲዎቹን ለማሟላት የፈጀበት ጊዜ ሲሆን 8ንቱን ዓመት ሥራው ላይ ቆይተናል፡፡ የነዳጅ ኢንዱስትሪውን አስመልክቶ ኩባንያው ጥሩ ዕድገትን አሳይቷል፡፡ 76 ማደያዎችን ገንብተን አገልግሎት እየሰጠን እንገኛለን፡፡ 28 ስቴሽኖች (የነዳጅ ማደያዎች) በግንባታ ላይ ይገኛሉ፡፡ ‹‹በግንባታ ላይ ያለውና ተገንብተው ያለቁ›› የሚለውን መረጃ ስናስቀምጥ ቁጥሩ ዕድገት አለው፡፡ በሌሎች ቦታዎች ደግሞ ሁለት ተጨማሪ የነዳጅ ማከማቻ ዲፖዎች ወደ ሥራ ገብተዋል፡፡

**ግዮን፡- ‹‹ታፍ ኦይል››ን ከአነሳሱንና ዛሬ ላይ የደረሰበትን ቢነግሩን?**

አቶ ሐራጎ፡- ‹‹ታፍ ኦይል›› ኢንዱስትሪው ላይ ከተቀላቀለበት ጊዜ ጀምሮ ከፍተኛ ደረጃ ሊባል የሚችል ዕድገት እያስመዘገበ የመጣ ኩባንያ ነው፡፡ ባለፉት 8 ዓመታት መሰረቱን በመገንባት ያሳለፍንበት ጊዜ ነው፡፡ ልክ እንደ ፒራሚድ የመሰረት ግንባታ ላይ ሰፊ ‹‹ኤሪያ›› እና ጉልበት የሚፈጅ በመሆኑ ያለማቋረጥ እየሰራን እንገኛለን፡፡

**ግዮን፡- ከአነሳሱ የት የት ቦታ ነው የነዳጅ ማከማቻ ዴፖዎችን ያቋቋማችሁት? ከዚያስ ውጪ በተጓዳኝ ምን ዓይነት ሥራዎችን ትሰራላችሁ?**

አቶ ሐራጎ፡- ‹‹ታፍ ኦይል የነዳጅ ማከማቻ ዴፖ›› ያለን ወለንጪቲ እና አየር መንገድ (የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች) ግቢ ውስጥ ነው፡፡ ማደያዎቹ ግን በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ተበትነው (ተራርቀው) ነው የሚገኙት፡፡

**ግዮን፡- ኢንዱስትሪው ውስጥ ለመቀላቀል ያለው ተግዳሮት ምንድን ነው?**

አቶ ሐራጎ፡- በተለይ አቬሽን ውስጥ የአውሮፕላን ነዳጅ የመሙላትና ማከማቻ ገበያን ስንቀላቀል ከመሬት ጥየቃው ጀምሮ፣ አልቆ ዛሬ ላይ ወደ ተግባር እስከምንሰማራ ድረስ ሦስት ዓመት ፈጅቶብናል፡፡ ስለዚህ የመሬት ጥየቃው በቶሎ ቢፈፀምና ሁሉም ነገር በፍጥነት ቢካሄድ ጥሩ ነበር፡፡ ይሁንና የተለያዩ የአሰራር ችግሮች ገጥመውናል፡፡ የአውሮፕላን ነዳጅ ማከማቻ ግንባታ ላይ በተለይ አብዛኛው ዕቃ በውጭ ምንዛሬ የሚገዙ ዕቃዎች ናቸው፣ በአገር ወስጥ የሉም፡፡ የዓለም አቀፍ ደረጃውን ጠብቆ ስለሚሰራ በተቀመጡት የአሰራር ክፍተቶችና የውጭ ምንዛሬን ያለማግኘት መዘግየቶች ገጥመውን ስለነበር በብሔራዊ ባንክና በተለያዩ



የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ቢሮዎች ድጋፍ ተደርጎልን ለማጠናቀቅ ችለናል፡፡

**ግዮን፡- ለምን ያህል ሰራተኞች የሥራ ዕድል ፈጥራችኋል?**

አቶ ሐራጎ፡- አዎ! ይህንን የአቪየሽኑን ብቻ ነጥዬ አጠቃላይ የግንባታ ሥራ ስንሰራ ከ1000 በላይ ሰዎች በተለያዩ የግንባታው ሥራ ላይ በሰራተኝነት ተሳትፈዋል፡፡ በዋናነት ሥራውን ለመስራት ያገኘነው በተራራማና ቆሻሻ መጣያ የነበረ ቦታ ስለነበር (ለ‹‹ዴፖ›› ተብሎ) እስከአሁን ድረስ ተይዞ ወደስራ ያልገባ በመሆኑ ሙሉውን ሥራ ለመስራት ከባድ ካፒታል ይጠይቅ ነበር፡፡ ከዚያ ጋር በተያያዘ የሰው ኃይል አጠቃቀማችንን በሚገባ ተጠቅመንበት ውጤታማ አድርገነዋል፡፡

**ግዮን፡- በሙያው ውስጥ ለምን ያህል ዓመት ቆያችሁ?**

አቶ ሐራጎ፡- በሙያው ውስጥ ለረዥም አመት የቆዩት በኩባንያችን ውስጥ የአምስት ዓመት ፕሬዜዳንታችን አቶ ትንሣኤ አክሊሉ በሥራው ውስጥ የቆዩ ናቸው፡፡ ከቤተሰብ ጀምሮ እየተንከባለለ የመጣ ነው፡፡

**ግዮን፡- ኩባንያችሁ ምን ያህል የነዳጅ ማከማቻ ዴፖ እና የነዳጅ ማከፋፈያ ኬላ ለማቋቋም ዕቅድ አለው?**

አቶ ሐራጎ፡- አሁን ያንን በእጥፉ አሳድገን በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ውስጥ 150 የነዳጅ ማደያዎችን በሀገራችን ላይ ገንብተን ሥራችንን በተሳካ ሁኔታ ለመስራት አቅደናል፡፡

**ግዮን፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግቢ የነዳጅ ማከማቻ ለመገንባትና ወደ ሥራው ለመግባት ያነሳሳችሁ ምንድን ነው?**

አቶ ሐራጎ ፡- የዛሬ 3 ዓመት በተፈጥሮ ጋዝና ነዳጅ በኢንዱስትሪ ዘርፉ የተካሔዱ ስብሰባዎች ላይ የአጋጣሚ ሆኖ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ተወካዮችም ተገኝተው ነበር፡፡ ከፍተኛ የሆነ የአውሮፕላን የነዳጅ አቅርቦት እጥረት መኖሩ እና እጥረቶችም እየተከሰቱ እንደነበር በጊዜው ይገለፅ ነበር፡፡ ችግሩን ለመቅረፍ እንደ አገር በቀል ኩባኒያ ‹‹ምን ዓይነት ድጋፍ እናድርግ?›› በሚል ነው የገባነው፡፡

**ግዮን፡- በአየር መንገድ ግቢ ውስጥ የሚገኘው ይህ የነዳጅ ማከማቻ ዴፖ የሚያከማቸው የነዳጅ መጠን በቀን ምን ያህል ይሆናል? ወደ ገንዘብ ሲተመንስ የክምችቱን ሁኔታ እንዴት ትገልፁታላችሁ?**

አቶ ሐራጎ፡- ይህ የነዳጅ ማከማቻ ዴፖ በሀገራችን ትልቁ የ "ጀት ዋን" (የአውሮፕላን የነዳጅ ማከማቻ ዴፖ) ነው፡፡ የመያዝ አቅሙም ስድስት ሚሊዮን ሊትር የአውሮፕላን ነዳጅን በማንኛውም ጊዜ ማጠራቀም የሚችል ነው፡፡ ዴፖውን ገንብተን ወደ ሥራ ለመግባት ኩባንያችን ከ450 ሚሊየን ብር በላይ ኢንቨስት አድርጎበታል፡፡

**ግዮን፡- ኢትዮጵያ ውስጥ የፔትሮሊየም ነዳጅ ወጥቷል? በኢትዮጵያ የነዳጅ ኢንዱስትሪው ላይ ምን ዓይነት የድርጅታዊ መዋቅር አለ?**

አቶ ሐራጎ፡- አዎ! የፔትሮሊየም ኢንዱስትሪው ላይ ሁለት ዓይነት ድርጅታዊ መዋቅር አለ፡፡ "አፕ ስትሪም ማርኬቲንግ እና ዳውን ስትሪም ማርኬቲንግ" በመባል ይታወቃሉ፡፡ እኛ ያለነው "ዳውን ስትሪም ማርኬቲንግ" በተባለው ላይ ነው፡፡ "አፕ ስትሪም ማርኬቲንግ" የሚባለው ነዳጅ የማውጣት ሥራ ላይ የሚሳተፉ ድርጅቶች ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ "አፕ ስትሪሙ" ላይ ተሳትፎ የሚሰራ ኩባንያ የለም፡፡ "አፕ ስትሪም ማርኬቱ" ትልቅ ካፒታል ይጠይቃል፡፡ የሚፈልገውም በጀት በቢሊየን ዶላር ነው፡፡ ወደፊት "አፕ ስትሪሙ" ላይ ለመግባት ዕቅዱ ይኖረናል፡፡ አሁን ቀድሞ የወጣውን ነዳጅ በየምድቡ ተለይቶ የተቀመጠውን ቤንዚን፣ ናፍጣ፣ ጥቁር ናፍጣ፣ … ተብሎ የተለየውን ለተጠቃሚዎች የማድረስ ሥራው ላይ ነው ትኩረት አድርገን የምንሰራው፡፡

**ግዮን፡- ከነዳጅ ኢንዱስትሪው ዘርፍ ላይ ለአገራችን የሚያስፈልጋት ምንድን ነው?**

አቶ ሐራጎ፡- ሀገራችን ላይ ያለው ትልቁ ተግዳሮት ስራውን ተረድተን የምንሰራበት የትርፍ ህዳግ ላይ ችግር መኖሩ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ከተማው ላይ የምናቀርባቸው ነዳጆችን ስንመለከት በሊትር ኩባንያዎቹና ማደያዎቹ ፣ትራንስፖርተሮቹ እያገኙ ያሉት የትርፍ መጠን በመንግሥት ቁጥጥር በጣም ዝቅተኛ ተደርጎ የተያዘ በመሆኑ ቢዝነሱን "ባያብል" ለማድረግ ያስቸግራል፡፡ ስለዚህ ትልቅ ጥናትና ይሄንንም የሚቀርፍ ሀሳብ በመንግሥት በኩል ይጠበቃል፡፡

**ግዮን፡- መመስገን አለባቸው የምትሉት አካል አለ?**


አቶ ሐራጎ፡- አዎን! የፋይናንስ ተቋማትን፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድን፣ የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ኢንተርፕራይዝን፣ የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅትን፣ የሚኒስትር ቢሮዎችን፣ እንዲሁም ይህንን ከባድ ኢንቨስትመንት በምናቋቁምበት ጊዜ እጅና ጓንት ሆነው የተጉትን የኩባንያችንን ሰራተኞች ማመስገን እፈልጋለን፡፡ ከኩባንያው ጋር በጋራ የሚሰሩ የማደያ ባለቤቶችን ሁሉ ከነሰራተኞቻቸው እንዲሁም የሚዲያ ተቋማትን ማመስገን እንፈልጋለን፡፡

**ግዮን፡- ስለነበረን ቆይታ በእኔና በግዮን መጽሔት ዝግጅት ክፍል ስም አመሰግናለሁ፡፡**

አቶ ሐራጎ፡- እኔም አመሰግናለሁ፡፡ ■


ABYSSINIA
FINE ARTS AND MODELING
አቢሲንያ
የሥነጥበብና የሞዴሊንግ ማሰልጠኛ ተቋም
ሥዕል
-ንድፍና ቀለም ቅብ
ቅርፃቅርፅ
-በጀሶ
-በሲሚንቶ
ሙዚቃ
-ዘመናዊ መሳሪያ
-ኪቦርድ
-ጊታር
MISS INTERNATIONAL ETHIOPIA 2010
ሞዴሊንግ
-ለሴቶችና ለወንዶች
-ካት ዎክ
-ፎቶ አነሳስ
-ሳይኮሎጂ
-ትወና
-ሜክአፕ አጠቃቀም
ባሕላዊ መሳሪያ
-ክራር
-መሰንቆ
-ዘመናዊ ዳንስ
-ባህላዊ ዉዝዋዜ
-ድምፅ አወጣጥ
ለሙሽሮችና ለሚዜዎች እንዲሁም ለቤተሰቦቻቸው፤ በግል መሰልጠን ለሚፈልጉ ውዝዋዜ እና ዳንስ እናሰለጥናለን
ቲአትር
-ትወና/አክቲንግ
-ዕሁፈተውኔት
-ዳይሬክቲንግ
አራት ኪሎ አርባ ደረጃ ከፍ ብሎ ናዝሬት ስኩል ፊት ለፊት
0111 577570 0911 683399
www.abysiniafinearts.com


አዲስ መጽሐፍ
በተለይ:-
- ለሕፃናት
- ለወጣቶች
- ለወላጆች
በስርጭት ላይ!
በሁሉም መጻሕፍት ቤቶች ያገኙታል
ብሉይ ኪዳን ለሕፃናት
የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች
አቡነ ታድሮስ ያዕቆብ ማላቲ
ትርጉም
ዘኤልያስ ወልደ ሚካኤል
አከፋፋይ:- +251 940 34 67 41


በኢኒሼቲቭ አፍሪካ ከስዊድሽ ኤምባሲ ጋር በመተባበር የቀረበ
Initiative africa
የዛሬው ፈተና ቀላል ነበር . . .
እንዴ? እንዴ? የኪናውን ሚልካ ታንከር ሹፌው?!
ኧረ ወየው!! ምናለ ነፍሴ ትምህርት ዜሽን ከምታቃጥዪ ወተት እያከራየሽ ብር ብትሰበስቢ?¡
የኔም እነሰ፤ የክረለዋም በዛ . . . ሁሉም የፈጣሪ ስጦታ ነው! ብቻ ሰውን ማንገጠጥ እንደሚያስከለስ ብታውቂት ጥሩ ይመስለኛል!!
ሥራፊቶች ናችሁ! የናንተም ጊዜ በተረብ ባከነ!
ውዬ ሲለቱ! ኧረ ካንቺም ጸረት ትንሽ ብታበድርሽ ጥሩ ነበር!
ኧ!?
ልባም ሁኚ!
CARTOON BY ROMAN TADESSE